ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በሽክኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች ትንተና

## (በ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

አየሁ አስፋው

ሰኔ 2015 ዓ.ም

ጅማ፤ ኢትዮጵያ

# በሸክኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች ትንተና


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል


ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጲያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል የድህረምረቃ መርሃ ግብር አማርኛን በማስተመር የማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ


በ

አየሁ አስፋው

ዋና አማካሪ

ምህረት ሳዳሞ (ፒ.ኤች.ዲ)

ረ/አማካሪ

ለማ ንጋቱ (ፒ.ኤች.ዲ)


ሰኔ 2015 ዓ.ም

ጅማ፤ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ
የማኅበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በሸክኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች ትንተና (በ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

አየሁ አስፋው

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ------------------------------ ፊርማ -------------------- ቀን -----------------

ፈታኝ ------------------------------- ፊርማ --------------------- ቀን ------------------

ፈታኝ ------------------------------- ፊርማ ---------------------- ቀን -------------------

ሰኔ 2015 ዓ.ም
ጅማ፤ኢትዮጵያ

# ማረጋገጫ

በሸክኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች ትንተና በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር አማርኛን ለማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና ጅማ ዩኒቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ----------------------------------

ፊርማ --------------------------------

ቀን -----------------------------------

## ምስጋና

በመጀመሪያ የጥበብ ሁሉ ባለቤት ለሆነው ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን፡፡በመቀጠል ጥናቱ ተጀምሮ እስከ ሚጠናቀቅ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን ሰጥተው ከትልመ ጥናቱ እስከ አጠቃላይ ረቂቁ ድረስ እርማት በመስጠትና ምክር በመለገስ ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለዋና አማካሪዬ ለዶ/ር ምህረት ሳዳሞ እና ለረዳት አማካሪዬ ለዶ/ር ለማ ንጋቱ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

እንዱሁም ለጥናቱ መረጃዎችን እሰበስብ ዘንድ በቀናነት ለተባበሩኝ ለኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ፣ለዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራንና ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ በሁለት ዓመት የትምህርት ቆይታዬ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ከጎነ በመሆን የሞራል ድጋፍ ላደረገችልኝ ለውድ ባለቤቴ ኤደን ተረፈ፤ማዝናናት፣መንከባከብና ማጫወት ሲገባን በዚህ ስራዬ ምክንያት ጊዜሽን ለተሻማውብሽ ለውድ ልጄ የርና አየሁ (ማማዬ) እንድሁም ኮፒዩተር በመሰጠት ስራዬን ላቀለልክልኝ ለውድ ወንድሜ ጥላዬ ከተማ (ኡጄ) ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡በመጨረሻም ይህን የትምህርት ዕድል በመስጠት እንድማር ላደረገኝ ለቦንጋ የትምህርት ኮሌጅ እና ለጥናቱ ለሚያስፈልገኝ ወጪ መሸፈኛ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አሕፅሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በሸክኛ አፍ ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ የሚያጋጥማቸውን የቋንቋ ችግር ለመፈታት የሚጠቀሙባቸውን ተግባቦታዊ ብልሀቶችን መፈተሸ ነው፡፡ የጥናቱ ተተኳሪዎችም አፋቸውን በሸክኛ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ጥናቱ የተካሄደበት ትምህርት ቤት የተመረጠው በአመቺ ናሙና ነው፡፡ የተለያየ የንግግር ብቃት ያላቸው ተማሪዎች እንዲሳተፍ ለማድረግ የንግግር ብቃት መለኪያ ፈተና ተሰጥቷል፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መርጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት ቃለ መጠይቅ፣ትርጎማ እና የስዕል ገለጻ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ተማሪዎቹ ሶስት ዋና ዋና ተግባራቱን ሲያከናውኑም በድምጽ መቅረጫ መሳሪያ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ወደ ጽሁፍ ተለውጠው ተተንትነዋል፡፡ በተጨማሪም የክፍል ምልከታና ከመምህራን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ በደጋፊ የመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ እንዲሁም የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ የተለያዩ ምሁራን በምርመራቸው ያገኙአቸውን ተግባቦታዊ ብልሀቶች መሰረት በማድረግ ተጠኚዎቹ የተጠቀሙባቸውን ተግባቦታዊ ብልሃቶች በየአይነታቸው ተመድበዋል፡፡ የጥናቱ ግኝትም የሸክኛ አፍ ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የማስወገድ ብልሃቶችን፣ የማካካሻ ብልሀቶችን እና የማዘናጊያ ዋና ዋና ብልሀቶች መገልገላቸውን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡በአጠቃላይ ይህ ጥናት ተግባቦታዊ ብልሀቶች ከችግር ፈቺ ዘዴ አንዱ በመሆናቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ያላቸውን ውስን የቋንቋ ዕውቀት በመጠቀም በቋንቋው እንዲግባቡ ለማድረግ በመማር ማስተማሩ ሂደት የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅትና በመምህራን ስልጠና ወቅት ትኩረት ቢሰጥ የሚል የመፍተሔ ሃሳብ ቀርቧል፡፡*

# ማውጫ

ይዘት ገፅ

ምስጋና ............ i
አሕፅሮተ ጥናት ............ ii
ምዕራፍ አንድ፡-መግቢያ ............ 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ............ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 4
1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ............ 4
1.4. የጥናቱ ዓላማ ............ 5
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ............ 5
1.6. የጥናቱ ወሰን ............ 6
1.7 የጥናቱ ውስንነት ............ 6
ምዕራፍ ሁለት፡-ክለሳ ድርሳናት ............ 7
2.1 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች ............ 7
2.1.1 የንግግር ክሂል ምንነት ............ 7
2.1.2 ንግግር በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ............ 7
2.1.3 ተግባቦታዊ ብልሃቶች እና ተዛማጅ ፅንሰ-ሃሳቦች ............ 9
2.1.4 በተግባቦታዊ ብልሃቶች ላይ የተሰነዘሩ አመለካከቶች ............ 10
2.1.5 የተግባቦታዊ ብልሃቶች ምደባ ............ 14
2.1.6 በተግባቦታዊ ብልሃቶችና በቋንቋ መማር መካከል ያለው ግንኙነት ............ 20
2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ............ 22
ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ ............ 25
3.1 የጥናቱ ንድፍ ............ 25
3.2 የጥናቱ አካላይ ............ 25
3.3 የናሙናዎች አመራረጥ ............ 25
3.3.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ............ 25
3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ............ 26
3.3.3 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ ............ 26
3.3.4 የመምህራን አመራረጥ ............ 27
3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ............ 27
3.5.1 የንግግር ፈተና ............ 27

3.5.2 ቃለ መጠይቅ ........ 27
3.5.3 የክፍል ውስጥ ምልከታ ........ 28
3.6 የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓትና ተግባራት ........ 28
3.6.1 ተግባር አንድ (ቃለመጠይቅ) ........ 29
3.6.2 ተግባር ሁለት (የስዕል ገለፃ) ........ 29
3.6.3 ተግባር ሶስት (ትርጎማ) ........ 30
3.7 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ........ 31
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ ........ 32
4.1 የመረጃዎች ትንተና ........ 32
4.1.1 አፋቸውን በሸክኛ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች የትኞቹ ናቸው? ........ 32
4.1.2. ተማሪዎቹ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች በቋንቋው ያላቸውን ........ 37
ችሎታ ለማሻሻል የሚረዱ ናቸው? ........ 37
4.2. የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ ........ 39
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት ........ 42
5.1 ማጠቃለያ ........ 42
5.2 አስተያየት ........ 43
ዋቢ ፅሑፎች ........ 45
**አባሪ አንድ፡- የንግግር ፈተና** ........ 48
**አባሪ ሁለት፡- የንግግር ፈተናውን ማረሚያ መስፈርቶች** ........ 52
**አባሪ ሶስት ፡- ንግግር ፈተናውን ውጤት ማጠናቀሪያ ቅጾች** ........ 55
**አባሪ አራት፡- ተማሪዎቹ ያከናወኗቸው ተግባራት** ........ 56
**አባሪ አምስት፡- የተማሪዎች ንግግር የፅሁፍ ምዝግቦች ማስታወሻ** ........ 63
**አባሪ ስድስት፡- የክፍል ምልከታ ቅፅ** ........ 78

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 4.1 የተጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶችና የድግግሞሽ መጠን ...............33

ሠንጠረዥ 4. 2 በተግባራት መካከል ጉልህ የአጠቃቀም ልዩነት የታየባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች ..........................................................................................36

# ምዕራፍ አንድ፡-መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚከናወን የሁለትዮሽ ሂደት ነዉ።መልዕክት ማቀበያ የሆነው የንግግር ክሂል ይዳብር ዘንድ መልዕክት መቀበያ የሆነዉ የማዳመጥ ክሂል መዳበር አለበት።የሁለቱ ክሂሎች መዳበር በእጅጉ የተቆራኘ ነዉ (በድሉ1996) እንደ Block(1997) አገላለጽ በክፍል ዉስጥ የንግግር ክሂል በሚቀርብበት ጊዜ ከማዳመጥ ክሂል ጋር ያለዉ ቁርኝትና ቅንጅት ከግምት ዉስጥ መግባት አለበት።አብዛኞቹ ተማሪዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን የሚያጠናቅቁት ጥሩ የንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ ነዉ።ስለዚህ ከትምህርት ቤት በኃላ ባለዉ ህይወታቸዉ ያለምንም ችግር ሀሳባቸዉን በንግግር ለመግለፅ ይቸገራሉ።

በበርካታ ምሁራን እምነት ንግግር አንድ አዲስ ቋንቋን ለመማር የሚያስችል የተሻለ ተፈጥሮአዊ መንገድ ነዉ(Rivers 1989)፡፡ይህ ክሂል በበርካታ የቋንቋ እዉቀት ለመቅሰም የሚያስችል ከመሁኑም ባሻገር ለበርካታ ሰዎች ተስማሚ የቋንቋ መማሪያ መንገድ ነዉ(Bygate 1987)።እንዲሁም ሌሎች ነገሮችን ለመማርም ጠቃሚ መሳሪያ ነዉ(Hallday 1989)።የንግግር ክሂል መዳበር በንባብና ፅህፈት ክሂሎች እድገት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል(Nowacek 1997)።ስለዚህ የንግግር ክሂል በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል።

ህይወት ፈርጀ ብዙ በመሆንዋ በሁለተኛ ቋንቋ መግባባት አስቸጋሪ ነዉ (Dornyei and kormos 1998)፡፡ በንግግር ወቅት ከተናጋሪዉ የሚጠበቀዉ የቋንቋዉን ስርዓት ጠብቆ ቃላትን ማቀናጀት ብቻ ሳይሆን አድማጩ ሊረዳዉ በሚችል መልክ መናገር ጭምር ነዉ (Jones 1993)።ይሁን እንጂ አሰሪዎች የማህበራዊ ደህንነት ባለሙያዎቹና የሠራተኛ አስተዳዳሪዎቹ ያካሄዱቸዉ ቃኚ ጥናቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን ያጠናቀ ራሳቸዉን በወጉ በንግግር መግለፅ እንደሚቸገሩ ያረጋግጣሉ(Brown1984)።

መልዕክትን የመተርጎም ሂደት እና ምላሽ የመስጠት ቅንብር ነዉ።አስፈላጊነቱም መልዕክት፣ሀሳብና መረጃ ከአንዱ ወደ ሌላው ለማስተላለፍ ሲሆን ይህ በተለያዩ የመግባቢያ ዘዴዎች ማለትም በፅሁፍ፣ በአንደበት ፣በምልክት ይተገበራል (Dryanan 2011)።እንደ Conrad &poole (2002) አገላለፅ ደግሞ

ዕለት ተዕለት ጓደኛን ከጓደኛ ቤተሰብ ከቤተሰብ አሰሪ ከሰራተኛ እንዲሁም ለሌሎችም ይተላለፋል አለምም ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተያያዘች ነች።

ተግባቦት ሰዎች መልዕክት ከሚለዋወጡበት ዘዴ አንዱና ዋነኛዉ ነዉ።ይህም ስለሆነ ተግባቦት ከሌለና ከተቋረጠ ግንኙነት ተቋረጠ ማለት ነዉ።ስለሆነም ተግባቦት ስኬታማ በሆነ መልኩ ሊካሄድ የሚገባዉ ሲሆን ክንዉኑ ደግሞ መልዕክት በማስተላለፍና በመቀበል ብሎም መልዕክቱን በመረዳት ደረጃ ነዉ(Griggin 2009)፡፡ተግባቦት በዕለት ተዕለት የሚፈፀም ተግባር ሲሆን በእያንዳንዱ ተግባር ስኬት የሚመዘገብ ከሆነ የተግባቦት ሂደቱ ስኬታማ እንደሆነ ያመለክታል።

ተግባቦታዊ ብልሀትን በተመለከተ Brown(2007) የምንናገረዉ ቋንቋና የተግባቦት ብልሀት እንደምንናገረዉ ርዕሰ ጉዳይ እንደ አድማጫችን እንደሁኔታዉ እንደህይወት ልምዳችንና እንደምናቀርበዉ የንግግር ዓላማ ሊለዋወጥ ይችላል በማለት ይገልፃሉ።

በትክክለኛዉ ማህበራዊ አዉድ በሁለተኛ ቋንቋ መግባባት በአብዛኛዉ በጣም አስቸጋሪ ነዉ። ምክንያቱም በሁለተኛ ቋንቋ መግባባት አዲስ ባህልን ማወቅ የአፍ መፍቻ ቋንቋን ተፅዕኖ መቋቋምና አዳዲስ ስነ ልሳናዊ ስርዓቶችን ማመንጨት መቻል ይጠይቃል።ከ1970ዎቹ ጀምሮ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎቹ ታላሚዉን ቋንቋ በመጠቀም ሲግባቡ አንድን ዕቃ፣ድርጊት፣ ሁኔታ ፅንስ ሀሳብ ወይም ወቅት ለይተዉ መግለፅ ሲሳናቸዉ የገጠማቸዉን የቋንቋ ችግር ለማካካስ በሚጠቀሙባቸዉ ተግባቦታዊ ብልሀቶች ላይ ያተኮሩ ጥናቶች እየተካሄዱ ናቸዉ (Bongaerts and Poulisse 1989.Cook 1993,Dornyei 1995)።የእነዚህ ጥናቶች መሠረታዊ ግብም በቋንቋዉ ትምህርት ዉጤታማ የሆኑ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸዉን ብልሀቶች በመለየት ዉጤታማ ያልሆኑት ተማሪዎች መርዳት ነዉ (Little wood 1984,Wharton 2000)፡፡

በተማሪዎች ብልሀቶች ላይ የተደረጉ የተለያዩ የምርምር ዉጤቶች እንደሚያረጋግጡት ልምድ ያላቸዉና ጎበዝ የቋንቋ ተማሪዎች ከጀማሪ ተማሪዎች ይበልጥ ስርዓታዊ ፣ጠቃሚ፣ችግር ፈቺና ቋንቋን ለመርዳት የሚያስችል ብልሀቶችን ይጠቀማሉ (Mclaughlin 1990,Wenden 1991)፡፡በመሆኑም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በተግባቦት ወቅት የሚጋጥማቸዉን የቋንቋ ችግር ለመፍታት በሚጠቀሙባቸዉ ብልሀቶች ላይ ምርምር ማካሄዱ በዘርፉ ያለዉን ግንዛቤ ከማስፋቱ ባሻገር የተማሪዎቹን ችግር ለመቅረፍ የበኩሉን ፋይዳ ይኖረዋል።

የቋንቋ መማሪያ ብልሀቶች ቋንቋን ለመማር በሚያስችሉ ክንዉኖችና ቴክኒኮች ላይ ስለሚያተኩሩ (Smith1994)ጀማሪዎቹ ተገቢ ብልሀቶችን ለመማር በቋንቋዉ በወጉ መጠቀም የሚችሉ ተማሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ (Mclaughlin1990)፡፡በተጨማሪም Wharton(2000),

Dickinson (1987)ጠቅሰዉ እንደፃፉትና ሌሎችም (Wenden 1991,Brown 1994, Green and Oxford 1995) እንደሚያረጋግጡት ብልሀቶች በተለይ የተማሪዉን በራስ ጥረት የመማር ነፃነት በማጠናከር ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታል፤ምክንያቱም ተገቢ ብልሀቶችን መጠቀም ወይም መልመድ ተማሪዎች ስለራሳቸዉ የመማር ሂደት የበለጠ ሀላፍነት እንደወሰዱ ይረዳቸዋል።

ልሳነ-ብዙ በሆኑ ሀገሮች ዉስጥ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዓይነተኛ ጠቀሜታ አለዉ ። ሁለተኛ ቋንቋ የሚፈለገዉ ወይም በትምህርትነት የሚሰጠዉ ለመደበኛ ቋንቋ ወይም የጋራ መግባቢያ እንዲሆን ታስቦ ነዉ(Wilkins 1972,Stern 1983)። አማርኛም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የስራ ቋንቋ በመሆኑ (ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 1987) ለሀገር ዉስጥ የጋራ መግባቢያነት ሊያገለግል ዘንድ በመላ ሀገሪቱ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት የሚሰጥ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩበት ዓላማ በሀገሪቱ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የተሻለ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ካለዉ ጠቀሜታ አንፃር ነዉ።

የቋንቋ ትምህርት ተቀዳሚ አላማ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ማዳበር ነዉ። ተግባቦታዊ ችሎታ በተግባቦት የሚያስፈልግ እዉቀትና ክሂል ዉስጣዊ ስርዓት ከመሆኑ በተጨማሪ ይህን እዉቀት ለትክክለኛዉ አጋጣሚ መጠቀምን ያመለክታል።

ተግባቦታዊ ብልሀቶች ተናጋሪዉ ማስተላለፍ የፈለገዉን መልዕክት ማስተላለፍ እንዲችል አማራጭ አገላለፆችን በመስጠት በተግባቦትወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ያስወግዳል (Cook1993)።ስለሆነም ተግባቦታዊ ብልሀቶች ተናጋሪዉ መልዕክቱን ለማስተላለፍ አንዳንድ ችግሮች ሲያጋጥሙት የሚጠቀምባቸዉ ስርዓታዊ ቴክኒኮች ናቸዉ (Dornyei-1995)።

ስለዚህ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተግባቦታዊ ብልሀቶችን ማጥናት ተማሪዎቹ ታላሚውን ቋንቋ ሲጠቀሙ ለሚያጋጥማቸው የቋንቋ ችግር የሚጠቀሚቸውን ብልሀቶች በመለየት በመማር ማስተማር ወቅት ጥሩ መስተጋብር ለመፍጠር እንዲሁም መምህራን የማስተማሪያ ዘዴ በመቀየር ተመሪዎች በተግባቦት ወቅት ጥሩ የመማር ማስተማር እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሌሎች ቋንቋ ማለትም በኦሮሚኛ፣በከፊኛ እና በጉመር ቋንቋዎች የተጠኑ ጥናቶች ቢኖሩም በሸክኛ ቋንቋ ዙሪያ የተሰራ ስራ አጢኚው ሊያገን አልቻለም፡፡በዚህ መሠረት የዚህ ጥናት አቅራቢም በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ የሚጠቀሙት ተግባቦታዊ ብልሃቶች

ዙሪያ የተጠና ጥናት ማግኘት ስላልተቻለ ክፍተቱን ለመሙላት በጥልቀት ማጥናት እንዳለበት ተገንዝቧል። ጥናቱ በደቡብ ምዕራብ ክልላዊ መንግስት በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደርጋል። ቀጥሎም ተማሪዎቹ በሚናገሩበት ጊዜ የሚጠቀሙትን ተግባቦታዊ ብልሀቶች ለይቶ በመተንተን አስፈላጊነቱም ተጠቁሟል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት የአጥኚው የስራ ላይ ገጠመኝ ነው። ይኸውም አጥኚው በየኪ ወረዳ ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚያስተምርበት ወቅት ተማሪዎቹ በመማር ማስተማር ሂደት በንግግር ሃሳባቸውን በምገልጹበት ጊዜ ከሚያሳዩት ደካማ ግብረ መልስ በመነሳት በሸክኛ ቋንቋ አፈ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች ላይ ችግር መኖሩን መገንዘብ ችሏል፡፡
በመሆኑም በመሆኑም ተማሪዎቹ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች የትኖቹ ናቸው የሚል ጥያቄ በአዕምሮዉ በመጫሩ ለዚህ ጥናት እንዲነሳሳ ምክንያት ሆኗል፡፡

ስለዚህ ተማሪዎቻቸሀ የሚጠቀሙባቸው የተግባቦት ብልሃት ምንድ ነዉ? ለሚለዉ ጥያቄ መፍትሂ ለመሻት ጥናቱን እንዲያካሂድ አስገድዶታል ።በተጨማሪም አጥኝዉ በሸክኛ አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ በሚጠቀሙባቸው በተግባቦታዊ ብልሀቶች ላይ የተደረገ ጥናት ባለማግኘቱ ጥናቱ ቢካሄድ በዘርፉ ያለውን ችግር ለመፍታት የሚያግዝ በመሆኑ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማድረግ ተነሳስቷል።

## 1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ከላይ የተነሱ ችግሮችን ለመመለስ ይህ ጥናት የሚከተሉትን መሪ ጥያቄዎች የያዘ ነዉ፡፡

- ✓ የሸክኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት በአማርኛ ሲናገሩ የቋንቋ ችግር ሲያጋጥማቸዉ የሚጠቀሙባቸዉ ተግባቦታዊ ብልሀቶች የትኞቹ ናቸዉ?
- ✓ የናሙና ታላሚዎች የሚጠቀሙባቸዉ ተግባቦታዊ ብልሀቶች በቋንቋዉ ያላቸዉን ችሎታ እንዲያሻሽሉ የሚረዱ ናቸዉ?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የሸክኛ አፍ-ፊት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በመጠቀም ሀሳባቸዉን በንግግር ለመግለፅ ሲሞክሩ የሚያጋጥማቸዉን የተግባቦት ችግር ለመፍታት የሚጠቀሙባቸዉን ተግባቦታዊ ብልሀቶች መመርመር ነዉ።በመሆኑም ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

- ✓ የሸክኛ አፍ-ፊት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት በአማርኛ ሲናገሩ የቋንቋ ችግር ሲያጋጥማቸዉ የሚጠቀሙባቸዉን ተግባቦታዊ ብልሀቶች መለየት።
- ✓ የናሙናዉ ታላሚዎች የሚጠቀሙባቸዉ ተግባቦታዊ ብልሀቶች በቋንቋዉ ያላቸዉን ችሎታ እንዲያሻሽሉ የሚረዱ መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ።

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ተማሪዎች በታላሚዉ ቋንቋ የተሳካ ተግባቦት ለማድረግ ሲፈልጉ የሚያጋጥማቸዉን ችግሮች ለመፍታት የሚጠቀሙባቸዉን ተግባቦታዊ ብልሀቶች ለይቶ በማዉጣትና በመተንተን እንዲሁም የቋንቋ መሻሻልና አለመሻሻልን መለየትና መጠቆም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።እነሱም ፡-

- ✓ **ለተማሪዎች**፡-ወደፊት በሚኖራቸው ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ሀሳባቸውን በተገቢው መንገድ እንዲገልጹ ሊያግዛቸው ይችላል፡፡
- ✓ **ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን**፡-ተማሪዎች በራሳቸዉ ጥረት የመማር ችሎታ እንዲያዳብሩ ስኬታማ ተግባቦታዊ ብልሀቶች የሚቀስሙበት ስልት መምህራን እንዲቀይሱ ይረዳል።
- ✓ **ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት**፡-ቋንቋዉን ተምረዉ ዉጤታማ የሆኑ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸዉን ጠቃሚ ተግባቦታዊ ብልሀቶች በመለየት ሀሳባቸዉን በንግግር የመግለፅ ችግር ያለባቸዉን ተማሪዎች ለመርዳት የብልሀት ስልጠና ለመስጠት ያግዛል።
- ✓ **ለመማሪያ መሣሪያ አዘጋጆች**፡- ዉጤታማ ተግባቦታዊ ብልሀቶች በመርሀ ትምህርትና በመማሪያ መፅሀፍ እንዲካተቱ ለስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ፍንጭ ይሰጣል።
- ✓ **ለጥናት አድራጊዎች**፡- በዚህ ርዕስ ሰፊ ጥናት ለሚያደርጉ እንደ መነሻ ይሆናል።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚካሄደዉ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል በሸካ ዞን የኪ ወረዳ በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የሸክኛ አፍ-ፊት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን ከነዚህ ተማሪዎች ቀላል የእጣ ናሙና በመጠቀም ለጥናቱ መረጃ የሚሰጡ ተማሪዎች ተመርጧል፡፡በመቀጠል ለዚህ ጥናት ትክክለኛ መረጃ ለመሰብሰብ ይረዳ ዘንድ የንግግር ፈተና፣ቃለመጠይቅና የክፍል ውስጥ ምልከታን አጥኚው ተጠቅሟል፡፡በአጠቃላይ ጥናቱ ገላጭ የምርምር ዘዴ በመከተል የተከናወነ ሲሆን ተማሪዎቹ ሀሳባቸዉን በንግግር ሲገልፁ የቋንቋ ችግር ሲያጋጥማቸዉ ተግባራዊ በሚያደርጉዋቸዉ ተግባቦታዊ ብልሀቶች ትንተና እና የተለያየ አንፃራዊ የንግግር ብቃት ወይም ተክህኖ ደረጃ ባላቸዉ ተማሪዎች መካከል ያለዉን የተግባቦታዊ ብልሀቶች አጠቃቀም ልዩነት ላይ የተገደበ ነዉ። እንዲሁም በሌላ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን አላካተተም፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

በዚህ ጥናት በስፋት ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን ስንመለከት ይህ ጥናት በሸክኛ አፈ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦት ብልሃቶች ላይ ያተኮረ ከመሆኑ አኳያ የተግዳሮቶች መንስኤ፣የተማሪዎቹ ንፅፅራዊ የንግግር ብቃት እና ፆታ ነክ ተላውጦችን የማይዳስስ በመሆኑ ውስንነት ስለሚኖረው በቀጣዩ በቀሩ ነጥቦች ላይ ሰፋ ባለ መልኩ ጥናት ማካሄድ የተማሪዎቹን የንግግር ብቃት ለማጎልበት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡-ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1 የንግግር ክሂል ምንነት

ንግግር ሀሳብ እንደመጣ ማፍለቅ ሳይሆን ሰው የተመለከተውን፣ስሜት ያፈለቀውን፣ በንባብና በማዳመጥ ያገኘውን ሃሳብ መነሻ በማድረግ በቋንቋ ድምጾች አማካኝነት መልዕክትን ለሌላ ወገን በስርዓት ማስተላለፍ መቻል ሲሆን በማህበራዊ ህይወት ውስጥም የጎላ ሚና ይጫወታል በማለት Celce-Muricia (2000)ይጠቅሳለ፡፡ ንግግር እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ የመግባቢያ መንገድ ነው፡፡በመሆኑም ሰዎች ከመሰሎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የመግባባት ሂደት መልዕክታቸውን በሚያስተላልፍበት ጊዜ ስርዓትን ጠብቀው በብቃትና በጥራት ሊገለገሉበት ይገባል በማለት ተስፋዬ(1981)ይገልፃሉ፡፡ እንደ Marriam.(2015) ገለጻ ንግግር ከማንበብና ከመጻፍ ክሂሎች ቀደም ብሎ የሚለመድ ሲሆን የሰው ልጆች የተለያዩ ክስተቶችንና ክንውኖችን ለመግለጽ የሚገለገልበት መሰረታዊ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ ሰዎች የራሳቸውን ባህልና ማንነት በንግግር አማካኝነት ይገልጻል፡፡ በመሆኑም የንግግር ክሂል የቋንቋው ተጠቃሚ ማህበረሰብ በሚፈቅደው መንገድ የራሱ የሆነ ህግና ሥርዓትን የተከተለ ድምጻዊ መግባቢያ ነው፡፡

### 2.1.2 ንግግር በቋንቋ ትምህርት ውስጥ

ንግግር የቃላዊ ተግባቦት አንዱ ክፍል መሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እንዲያዳብሩቸው ከሚፈለገት የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ንግግር እስከ 1970ዎቹ ድረስ በቋንቋ ትምህርት እምብዛም ትኩረት የሚሰጠው ክሂል አልነበረም ፡፡ ብዙንውን ጊዜ ለፅሀፊት ልዩ ክብር ሲሰጥ የቆየ ሲሆን ንግግር ግን እንደ ተራ ነገር ይቆጠር ነበር (Mc-Donough1983) እንዲያውም የንግግር ቋንቋ፤ቅርፅ፣አልባ ያልተሟላ፣ ትክክለኛ ያልሆነ አጀማመር የሚታይበት፣ተጠየቃዊ መዋቅር የሚጎለው ነው የሚሉ ትችቶች ሲሰነዘሩበት ቆይቷል፡፡ ሆኖም ንግግር የጹሁፍ ቋንቋ ቃላዊ ግልባጭ ሳይሆን ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዱ በርካታ ንዑሳን ክሂሎችን እንዲያዳብሩ የሚጠይቅ ክሂል በመሆኑ (Mc Donough and Shaw 1993) እና ንግግር በመማር ሂደት ካለው ወሳኝ ሚና አንፃር ሲታይ የተሰነሰዘሩት ትችቶች የተዛቡ ናቸው፡፡

Pygate (1987) Mackey(1965)ን ጠቅሶ እንደገለጸው፣ ንግግር ትክክለኛ ድምጾችን ተገቢ የዜማና የቅላፄ ሥርዓታቸውን ጠብቆ ማፍለቅ ብቻ ሳይሆን፣ ትክክለኛ መልዕክት ለማስተላለፍ ቃላትንና እርባታቸውን የቋንቋውን ሥራዓት ጠብቆ በትክክል መምረጥም ነው ይላል፡፡ ይሁን እንጂ በንግግር ሃሳብን ለማስተላላፍ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰው፣ቃላት ማወቅና ማፈለቅ መቻል ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ስለሆነም፣ የቋንቋ ተማሪው ሀሳቡን በንግግር በተሳካ ሁኔታ ማሰተላላፍ ይችል ዘንድ ከትግበራ ግንዛቤያዊ ክሂሎች በተጨማሪ በዕለት-ተዕለት ኑሮ ውስጥ በቋንቋው መጠቀም የሚያስችሉትን መስተጋብራዊ ክሂሎች ማዳበር ይጠበቅበታል ፡፡

በተጨማሪም የንግግር ችሎታ መዳበር በመግባባት ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ ግንኙነት ለመፍጠር ከተሻለ ማህበራዊ ደረጃ ላይ ለማደረስ፣ ራሱን በሙያና በንግድ ተግባር ለማሻሻል ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ንግግር መረጃን ለማሰተላፍና ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር ይረዳል (Brown And yule1983)፡፡ ስለዚህ ንግግር ፍላጎትን ወይም ዓላማን መሰረት ያደርጋል፡፡ በሌላ አባባል የምንናደርገው አንድ የተወሰነ ግብን ለማሳካት ነው፡፡ለንግግር ሃሳብን ወይም አስተያየትን መግለፅ አንድን ነገር ለማከናወን ፍቃደኝነት ላይ መመስረትና ማጠናከር ወዘተ የመሳሰሉት ዓላማዎች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡እነዚህን የንግግር ዓላማዎች ለማሳከት ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ተገቢነት ያላቸውን በርካታ አገላለጾች ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ሆኖም አንድን ቋንቋ በተሟላ ሁኔታ ማስተማር አይቻልም ስለዚህ ተማሪዎች ያላቸውን ውስን የቋንቋ እውቀት በመጠቀም በቋንቋ እንዲግባ ቡ የሚያስችሏቸውን ብልሃቶች ማስተማር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ በቃላዊ ተግባቦት ወቅት ቋንቋውን በወጉ መጠቀም የሚችል ተሳታፊ እንደሆን በመናገርና በማዳመጥ ክሂሎች መሰልጠን ይኖርበታል (Andersen and Lynch1991)፡፡ተከታታይነት ያለው ረዥም ማብራሪያ በቃል መስጠት ለመረጃ ልውውጥ ወይም ለማህበራዊ መስተጋብር ተብሎ ከአንድ ወይም ከአንድ ከበለጡ ሰዎች ጋር ከሚደረግ መስተጋብር ፍፁም የተለየ ነው፡፡ሁሉም አፍ-ፈቶች ቋንቋቸውን ለመስተጋብራዊ አገለግሎት መጠቀም ይችላሉ ነገር ግን ሁሉም የቋንቋው ተናጋሪዎች ለተወሰኑ አድማጮቸ ስለአንደ ርዕሰ ጉዳይ ሳይዘጋጁ የመናገር ችሎታ አይኖራቸውም፡፡ስለዚህ ንግግር ሊማሩትና ሊለማመዱት የሚገባ ክሂል ነው (Nunan1989)፡ ፡

ንግግር ከመማርያ ክፍል ውጭ ሆነ ውስጥ ራስን ከሌሎች ጋር ለመግባባት የሚያስችል መሳርያ በመሆኑ የንግግር ትምህርት ተማሪው የቋንቋውን ንበት፣ጫና እና የድምፅ

አወጣጠ እንዲካን ስለሚረዳ የተማሪውን ስጋት በመቀነስ በራስ የመተማመን ስሜቱን ያጎለብታል (Rivers 1989)::አለበለዚያ አድማጩ ሰለሚሰለች ወይም ትግስት ስለሚያጣ የመግባባቱ ሂደት ሊቋረጥ ይችላል፡፡ስለዚህ ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ተማሪው የሌላውን ንግግር ከሚደገምበት ወይም የተገደበ ምላሽ ከሚሰጥበት ደረጃ የራሱን ሃሳብ በሆነ መንገድ መግለፅ ወደ ሚችልበት ደረጃ መሸጋገር ይኖርበታል(Bayrn 1986)፡፡ይሁን እንጂ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ካለባቸው የቋንቋ ችግር በተጨማሪ በሚናገሩበት ወቅት አፍ-ፈቶች የሚጠቁሙባቸውን አንዳንድ ብልሃቶች እንደማይጠቅሙ በዚህ መስክ የተካሄዱ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

### 2.1.3 ተግባቦታዊ ብልሃቶች እና ተዛማጅ ፅንሰ-ሃሳቦች

ተማሪዎች ቋንቋን በመደበኛ ፕሮግራም ለመማር የሚመጡት በቋንቋ ትምህርታቸው ላይ ወሳኝ የሆኑ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ የራሳቸው ባህርያት (ችሎታዎችን፣ፍላጎቶችን፣የመማር ልማዶችንና ግቦችን) ይዘው ነው(Richards 1985)፡፡ይህ ሃሳብ በመማር ሂደት በተማሪዎች መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ተማሪዎች ለትምህርት ባላቸው ልዩ ችሎታ ለመማር ባላቸው ፍቃደኝነትና በመማርያ ብልሃቶች) ምርጫ ወዘተ ይለያያሉ፡፡

ተግባቦታዊ ችሎታ የሚያካትታቸውን የእውቀትና የክሂል ዘርፎች የሚመለከቱት ተግባራዊ ስነ ልሳን ምሁራን (Larsen-Freeman and long, 1991; Canle, 1983; Bachman, 1990) በመጠኑም ቢሆን የተለያየ አመለካከት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ የCanle (1983) አመለካከት በርካታ ምሁራን (Tarone And Yule, 1989:6; Olshtain and cohen, 1991:154-155; yule, 1996፡197; McDonough, 1996) ይጠቅሳል፡፡ ተግባቦታዊ ችሎታ ቢያንስ አራቱን የዕውቀትና የክሂል ዘርፎችን እንደሚካተት ይገልፃል፡፡ እነሱንም ሰዋሰዊ ችሎታ ማህበረ ስነልሳናዊ ችሎታ የዲስኩር ችሎታ እና ብልሃታዊ ችሎታ ናቸው፡፡

ሰዋሰዋዊ ችሎታ የቋንቋን ባህሪያትና ህጎች ማለትም ቃላት፣ የቃላት አመሰራረት፣ የዓረፈተ-ነገር አወቃቀር፣ ንበት፣ የቃላት አፃፃፍ እና ስነልሳናዊ ትርጉም የመሳሰሉትን ማወቅን ያካትታል (Canale1983) ፡፡ ማህበረ-ስነ ልሳነዊ ችሎታ ደግሞ የተለያዩ አውዳዊ አጋጣሚዎችን ማለትም ስምምነቶችን መሰረት በማድረግ በትክክለኛ ንግግርን የማፍለቅና የመረዳት ችሎታን ነው (Canale1983) እንዲሁም የዲስኩር ችሎታ አንድ ወጥ የሆነ ንግግር ወይም ጽሁፍ ለማግኘት የሚያስችለውን የቋንቋውን ሰዋሰውና ፍች የማቀናጀት ችሎታን ይመለከታል (Canale 1983)፡፡

Tarone እና Yule (1989) እንደፃፉት ብልሃታዊ ችሎታ የሚለካው በትክክለኝነት ደረጃ አይደለም ነገር ግን በተግባት ወቅት ውጤታማ ከመሆን አንፃር ነዉ፡፡ በርግጥ ግለሰቦች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰው በትክክል ሳይጠቀሙ ማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልዕክት በሚገባ ሊያስተላለፉ ይችላሉ፡፡በተጨማሪም የተለያዩ ሥልጠናዎች ቅርፆች በተለያዩ አጋጣሚዎች በተለያዩ አድማሎች ዘንድ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ Brown (1994) እንዳለው ብልሃቶች አንድን ችግር ለመፍታት የምንጠቀምባቸው የተወሰኑ ዘዴ ቴክኒኮች ናቸው ፡፡ ስለሆነም በሁለተኛ ቋንቋ ግብአት ወቅት ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ለመሻት ተግባራዊ የሚሆኑ ቅጽበታዊ ቴክኒኮች ናቸው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ጥናት መስክ በአብዛኛው ሁለት አይነት ዋና ዋና ብልሃቶችን ለመለየት አስችሏል፡፡ እነሱም የቋንቋ መማሪያ ብልሃቶች እና ተግባቦታዊ ብልሃቶች ናቸው Cook, 1993; brown, 1994] ፡፡

የቋንቋ መማሪያ ብልሃቶች ጥቅል በሆነ አገላለጽ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ያላቸውን እውቀትና በቋንቋው ለመጠቀም ያላቸውን ችሎታ ለማሳደግ በዓላማ የሚያከናውኗቸው የተወሰኑ ተግባራት ናቸው (Green and oxford, 1995፡262; Tudor 1996:10) በተመሳሳይ ሁኔታ Oxford (1990, Bremner 1999 እንደተጠቀሰው)፣ "የመማሪያ ብልሃቶች ተማሪዎች የራሳቸውን የመማር ሂደት ለማጠናከር ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ደረጃዎች ናቸው" ይገልጻሉ፡፡

አብዛኛውን ጊዜ የቋንቋ መማሪያ ብልሃቶችና ተግባቦታዊ ብልሃቶች የተለያዩ እንደሆኑ ይነገራል (Ellis, 1994; Brown, 1994; singleton 1999)፡፡ለዚህ ሀሳብ ማጠናከሪያነት የሚቀርቡት ሀሳቦችን የቋንቋ መማሪያ ብልሃቶች ተቀባይ የሆኑትን አእምሮአዊ ተግባራት ማለትም መቀበል፣ ማስታወስ፣እና ማጠራቀም የመሳሰሉትን) ለማከናወን የሚረዱ ሲሆኑ በአንጻሩ ተግባቦታዊ ብልሃቶች ለተግባቦታዊ አገልግሎት መረጃዎችን ለማፍለቅ የሚያስችሉ ልሳናዊና ኢ-ልሳናዊ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ ናቸው (Brown1994:118)፡፡ እንዲሁም፣ተማሪዎች የቋንቋ መማሪያ ብልሃቶችን የሚጠቀሙባቸው ዘላቂ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር ሲሆን ተግባቦታዊ ብልሃቶችን የሚጠቀሙባቸው ግን ወቅታዊ የተግባቦት ችግራቸውን ለመፍታት ነው (Cook,1993፡ Ellis, 1994፡ Tudor, 1996) የሚሉት የመከራከሪያ ነጥቦች ናቸው፡፡

## 2.1.4 በተግባቦታዊ ብልሃቶች ላይ የተሰነዘሩ አመለካከቶች

የተግባራዊ ስነልሣን ተመራማሪዎች በተግባቦታዊ ቋንቋ ማሰተማር ላይ ያላቸው ፍላጎት በሁለተኛ ቋንቋ መማራቸው የተግባቦታዊ ብልሃቶች አጠቃቀም ላይ እንዲያተኩሩ

አድርጓቸዋል (Littlemore 2001):: በተግባቦታዊ ብልሃቶች ላይ የሚደረግ ጥናት ተማሪዎች መልዕክትን ለማስተላለፍ ሁለተኛ ቋንቋ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ስለሚያጠና ጠቃሚ ነው፡፡

ተግባቦታዊ ብልሃቶች በአንዳንድ ምሁራን ዘንድ የማካካሻ ብልሃቶች በመባል ይታወቃሉ (Littlemore 2001)::እስካሁን ድረስ ስለተግባቦታዊ ብልሃቶች ምንነት ሁለት ዋና ዋና ንደፌ-ሃሳባዊ ስልተ-ትወራዎች ተሰንዝረዋል (Cook, 1993; Ellis, 1994)፡፡ እነሱም መስተጋብራዊ ስልተ ትወራ እና ስነ ልቦናዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ስነልሳን ስልተ-ትወራ ናቸው፡፡

በመስተጋብራዊ /ማህበራዊ መስተጋብር/ ስልተ-ትወራ አመለካከት ተግባቦታዊ ብልሃቶች በተግባቦት ወቅት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱትን ቃላት የውውይቱ ተሳታፊዎች በጋራ የሚያውቁበት አጋጣሚ ሲከሰት ሁለቱም ተሳታፊዎች የጋራ ግንዛቤ ለመጨበጥ የሚያደርጓቸው የወል ጥረቶች ናቸው Tarone (1981) Ellis (1994) እንደተጠቀሰው፡፡ ተግባቦታዊ ብልሃቶች  መስተጋብራዊ ናቸው የተባሉበት ምክንያት የቋንቋ ተማሪዎች ከእነርሱ ጋር በመግባባት ላይ ያሉ ሰዎች  ሃሳባቸውን እንድረዱላቸው የሚያደርጓቸውን ሙከራዎች ስለሚያንፀባርቁ ነው፡፡ ስለሆነም ተግባቦታዊ ብልሃቶች ማህበራዊ ብልሃቶች በመባል ይታወቃሉ (Cook1993)፡፡ ይሁን እንጂ Cook (1993) (Tarone) እምነት ማህበራዊ ብልሃቶችን ለማጥናት ተነጋጋሪውንና አድማጩን ማሳተፍ ስለሚያስፈልግ በእያንዳንዱ ተግባቦታዊ ብልሃት ብያኔ ሲሰጥና ወደ ጽሁፍ የተለወጠው ንግግር ሲተነተን በመግባባት ላይ የነበሩትን ሰዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡አንዱ ተሳታፊ (ተናጋሪ) ተግባቦታዊ ብልሃት ስለተጠቀመ ብቻ በመግባባት ላይ በነበሩ ሰዎች መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር ብለን ለመደምደም የሚያስችለን ምን ማረጋገጫ አለ? ስለዚህ ከኢ-አፍ ፊቱ ንግግር ይበልጥ እርስ በርስ አለመግባባት መኖሩን የሚያረጋግጥ ሌላ ማስረጃ ያስፈልጋል፡፡ በማለት መስተጋቢራዊ ስልተ ትወራ ይተቻል፡፡

በCook (1993) እና Ellis (1994) እንደተጠቀሰው ለተግባቦታዊ ብልሃቶች ስነ-ልቦናዊ (ስነልቦናዊ-ስነልሳን) ብያነ ከሰጡት ምሁራን መካከል Faerch እና Kasper (1983) እና የኒጅሜገን ፕሮጀክት ተመራማሪዎች (The Nljmegn project researchers 1990) ይገኙበታል፡፡

ለተግባቦታዊ ብልሃቶች ከስነ ልቦናዊ ስልተ ትወራ አንፃር ብያኔና ትንታኔ ከመስጠት አኳያ ቀዳሚ ተጠቃሽ ስራ የእነ Faerch እና Kasper (1983 Cook 1993) እንደተጠቀሰው) ነው፡፡ Cook (1993) ,Faerch Kasper (1983) ጠቅሶ እንደፃፈው ተግባቦታዊ ብልሃት አንድ ግለሰብ በተግባቦት ወቅት የሚያጋጥመውን የተወሰነ ችግር ለመፍታት ሆን ብሎ (consciously) ተግባራዊ የሚያደርገው ዕቅድ ነው፡፡ በዚህ አመለካከት መሰረት ተግባቦታዊ ብልሃት አንድ ግለሰብ ለአንድ የተወሰነ ችግር የሚሰጠው አዕምራዊ ምላሽ እንጂ ሁለት ሰዎች በጋራ የሚሰጡት ምላሽ አይደለም (Cook, 1993; Ellis, 1994)፡ ፡

ከላይ የተጠቀሰው Faerch እና Kasper ለተግባቦታዊ ብልሃቶች የሰጡት ብያኔ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ይዟል ፡፡ እነሱም፣ ተግባቦታዊ ብልሀቶች

ሀ. ችግር - ተኮር (problem oriented) እና

ለ. በንቃተ - ህሊና ላይ የተመሰረተ (potentially conscious) የሚሉት ሃሳቦች ናቸው ፡፡

የኒጅሜገን ፕሮጀክት ተመራማሪዎችም ለተግባቦተዊ ብልሃቶች የሰጡት ብያኔ ከFaerch እና Kasper ብያኔ ጋር ይቀራረባል፡፡Ellis (1994) ከፕሮጀክቱ ተመራማሪዎች አንዷ የሆነችውን Poulisse (1990)ን ጠቅሶ እንደፃፈው ተግባቦታዊ ብልሃቶች አንድ የቋንቋ ተጠቃሚ ንግግርን ለማፍለቅ ሂደት የዕቀዳ ደረጃ (planning phase) ወቅት በቋንቋ ችግር (linguistic shortcomings) ምክንያት የተከሰቱትን እክሎች በመገንዘብ ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በተሳካ ሁኔታ ማስተላለፍ እንዲችል ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ብልሃቶች ናቸው ፡፡ ይሁን እንጂ Ellis (1994) ለተግባቦታዊ ብልሃቶች ስነልቦናዊ ብያኔ በመስጠት ረገድ በተመራማሪዎች መካከል ልዩነት እንደሚታይ ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም Ellis (1994) እንደተጠቀመው Bialystok (1990) Faerch እና Kasper (1983) ተግባቦታዊ ብልሃቶች ለመበየን የተጠቀሙባቸውን መስፈርቶች (ማለትም ችግር-ተኮር እና በንቃተ-ህሊና ላይ የተመሰረቱ የሚሉትን ፅንሰ-ሀሳቦችን ተችታለች ፡፡

Ellis (1994) Bialystok (1990)ን ጠቅሶ እንደፃፈው በ Faerch እና Kasper ሞዴል ውስጥ ከተጠቀሱት ሁለት ዓይነት ዕቅዶች ማለትም ችግር- ተኮር እና በንቃተ- ህሊና ላይ የተመሰረቱ የሚሉትን ፅንሰ-ሀሳቦች/ ትተቻለች፡፡ Ellis (1994) Bialystok (1990)ን ጠቅሶ እንደፃፈው በ Faerch እና kasper ሞደል ውስጥ ከተጠቀሱት ሁለት ዓይነት እቅዶች ( ማለትም ብልሃታዊ እቅዶች እና አፍላቂ እቅዶች መካከል ብልሃታዊ እቅዶች ችግር-ፈቺ አለመሆናቸው እንዴት ይታወቃል? የሚል ጥያቄ በተግባቦታዊ ብልሃቶች ችግር-ፈቺ ላይ ይሰነዝራል፡፡በተጨማሪም Bialstok (1990) Ellis (1994) እንደተቀሰው

ሆን ተብሎ ተግባራዊ የሚደረጉ ተግባቦታዊ ብልሃቶችን ሆን ተብሎ ተግባራዊ ከማይደረጉ ተግባቦታዊ ብልሃቶች ለመለየት የሚያስችል አስተማማኝ ዘዴ ስለሌለ ተግባቦታዊ ብልሃቶች ሆን ተብሎ ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው፡፡ የሚለውንም ሀሳብ ትቃወማለች። በእሷ እምነት ይህ አስተሳሰብ ሁሉም ብልሃቶች ሆን ተብሎ ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው ወደሚል ድምዳሜ ይወስዳል። ከላይ ለማየት እንደተሞከረው Ellis (1994) Bialystok (1990) ጠቅሶ እንደፃፈው Bialystok በ Faerch Kasper ላይ ያነሳቻቸውን የተቃውሞ ነጥቦች መሰረት በማድረግ ስለ ልቦናዊ ስነ ልሳንን መሰረት ያደረገ የራስዋን ብያኔ ለመስጠት ሞክራለች። ብያኔዋ በትንተና ወይም በእውቀት እና በቁጥጥር መካከል ባለው ልዩነት ላይ የተመሰረተ ነው። Bialystok (1990) በ Ellis (1994) እንደተቀሰው፣ ተግባቦታዊ ብልሃቶችን፣ እውቀት ተኮር ቁጥጥር -ተኮር በማለት በሁለት ትከፍላቸዋለች።እውቀት ተኮር ተግባቦታዊ ብልሃቶችን ተናጋሪው ስለጽንሰ ሃሳቡ ያለውን እውቀት መሰረት በማድረግ የመልዕክቱን ይዘት እንዲያስተካክል የሚረዱ ናቸው።ምሳሌ ብያኔ ወይም ገለፃ የመሳሰሉትን ያካትታል። በቁጥጥር ተኮር ብልሃቶች ተናጋሪው ማስተላለፍ የሚፈለገውን መልዕክት ማስተላለፍ እንዲችል ከታላሚው ቋንቋ ውጭ ያሉትን ግብዓት (ማለትም እርካታ የአፍ-መፍቻ ቋንቋን መሰረት የሚያደርጉ ብልሃቶችን እና የሰውነት እንቅስቃሴን ይጠቀማል።አፍ ፈቶችም ቢሆኑ ማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልዕክት በተሻለ ሁኔታ ለማስተላለፍ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ Cook(1993 )፤Faerchእና Kasper ብልሃቶች በሁለተኛ ቋንቋ ለመግባባት ጥረት ሲደረግ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶች ምልክቶች ናቸው ይላሉ፡፡ይሁን እንጂ የብልሃቶች ዓይነቶች ከችግሩ ዓይነት ይልቅ የችግሩን መፍትሄ ዓይነቶች የሚጠቀሙ ስለሚመስሉ ችግርን ለመፍታት የሚደረግ ጥረት ስለመኖሩ አስተማማኝ የሆነ ማስረጃ የለም ይላል።

Ellis (1994) የBialystokን ሃሳብ በሚመለከት የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቷል። በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው በተግባቦት ብልሃቶች ላይ የሚያተኩሩ የሁለተኛ ቋንቋ ተመራማሪዎች ተግባቦታዊ ብልሃቶችን ለመበየን ከሚጠቀሙባቸው ንድፈ-ሃሳባዊ ስልተ-ትወራዎች አንፃር በሁለት ጎራ ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ። እነሱም ተግባቦታዊ ብልሃቶቹን ከማህበራዊ መስተጋብር አንፃር በማየት ማህበራዊ ስነልሳንን መሰረት የሚያደርጉ ተመራማሪዎች ምሳሌ፤በ Ellis (1994) እንደተጠቀሰው (Tarone 1977 Varadi 1980) እና ተግባቦታዊ ብልሃቶችን እንደ ስነልቦናዊ ሂደት በመቁጠር ስነልቦናዊ - ስነልሳንን መሰረት የሚያደርጉ ተመራማሪዎች (ምሳሌ፡-በ Ellis 1994 እንደተጠቀሰው Faerch and Kasper 1983; Bialystok 1990; Poulisse 1990) ናቸው።

የሁለቱም ጎራዎች ዓላማ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሊያገለግሉ የሚችሉ ብልሃቶችን መለየት ስለሆነ በአብዛኛው የሚጠቀሙበት ስነ ዘዴም ወደ ፅሁፍ የተገለበጠውን የተማሪዎች ንግግር በጥልቀት በመፈተሽ የብልሃት ዓይነቶችን የሚያስለይ ነው (cook 1993)፡ ፡

## 2.1.5 የተግባቦታዊ ብልሃቶች ምደባ

Dornyei (1995) እንደፃፈዉ እ.አ.አ.በ1970ዎቹ የተካሄዱ አራት ጥናቶች ለተግባቦታዊ ብልሀቶች ጥናት መሰረት ጥለዋል። እነዚህ ጥናቶች በተግባራዊ ሥነልሳን የጥናት ዘርፍ አንድ አዲስ የጥናት አቅጣጫን ያመላክቱ ነበሩ።Selinker (1972 በ Dornyei 1995 እንደተጠቀሰዉ) ስለዝንቅ ቋንቋ ባቀረበዉ ጥናታዊ መጣጥፍ በሁለተኛ ቋንቋ የመግባባት ሂደት ተግባራዊ የሚሆኑትን የብልሃት ዓይነቶች አስተዋዉቋል።Varadi (1973 በ Dornyei 1995) እንደተጠቀሰው እና Tarone (1977 በ Dornyei 1995) እንደተጠቀሰው እንዲሁም Tarone Cohen እና Dumas (1976 በ Dornyei 1995) እንደተጠቀሰው ተግባቦታዊ ብልሃቶችን ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ በመተንተን የSelinker'ን ሃሳብ አዳብረዋል (Dornyei 1995)። በተጨማሪም በተከታታይ በተካሄዱ ጥናቶች ጥቅም ላይ የዋሉ ምደባዎችን እና ሙያዊ ቃላትን አስተዋውቀዋል።ከነዚህ ቀደምት ጥናቶች ጀምሮ የተግባቦታዊ ብልሀቶችን ዓይነት ለመለየትና ለመመደብ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል።

በተግባቦታዊ ብልሃቶች ምድብ ረገድ በተመራማሪዎች መካከል ልዩነት ይታያል። ይህን ሃሳብ Singleton (1999) "የተግባቦታዊ ብልሀቶችን ምድብ በሚመለከት አንዳንድ ተመራማሪዎች ሰፋት ያላቸዉን ተዋረዳዊ ምደባዎች ሲያደርጉ ሌሎቹ ደግሞ የብልሃት ዓይነቶችን ወደ ሁለት ወይም ሶስት ዝቅ ለማድረግ ሞክረዋል"በማለት ይገልፀዋል።ስለሆነም በተግባቦታዊ ብልሃቶች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ከብልሃቶች ድልድል አንፃር በአብዛኛው በሁለት ዋና ዋና ምድቦች ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ። ይኸውም Dornyei (1995) እንደተፃፈው የመጀመሪያው ምድብ Varadi (1973)ን Tarone (1977)ን Faerch እና kasper (1983)ን እና Bialystok.(1990)ን መሰረት የሚያደርግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኔዘርላንድስ የሚገኘው የኒጅሚገን ፕሮጀክት (Nijmegen project) ተመራማሪዎች ምድብ ነው። በመጀመሪያው የምድብ ወገን ከተጠቀሱት ተመራማሪዎች መካከል በተለይ የ Tarone እና የ Faerch እና kasper ምደባዎች ይጠቀሳሉ።

የ Tarone (1977 በCook 1993 እንደተጠቀሰው) የተግባቦታዊ ብልሃቶች ምድብ

- መልዕክትን መተው - ማስወገድ ርዕስን ማስወገድ
- አሳጥሮ መናገር -ግመታ
  -ቃል-ፈጠራ
- ገለፃ - ልሳናት ቅልቀላ
- ማሸጋገር የቃል በቃል ትርጉም -ድጋፍ መጠየቅ
- የሠውነት እንቅስቃሴ

ሌላው ተጠቃሽ የተግባቦታዊ ብልሃቶች ምደባ የFaerch እና Kasper (1984 በCook 1993 እንደተጠቀሰው) ነው። ይህ ምደባ በርካታ ተግባቦታዊ ብልሃቶችን አካቷል። ምደባው በCook (1993) እንደተጠቀሰው እንደሚከተለው ቀርቧል።

የ Faerch እና Kasper (1984 በCook 1993 እንደተጠቀሰው) የተግባቦታዊ ብልሃቶች ምድብ

| | | |
|---|---|---|
| ኢ-ትብብራዊ-<br>(Non-cooperative)<br><br>ትብብራዊ-<br>(cooperative)<br>-የዝንቅ ቋንቋ ብልሃቶች-<br>(Interlanguage strategies)<br>-ኢ-ልሣናዊ ብልሃቶች-<br>(Non-linguistic strategies)<br>ድጋፍ(Appeals) | መደበኛ ቅነሳ-<br>(Format reduction)<br><br><br>አገልጋሎታዊ ቅነሳ-<br>(Functional<br>reduction) | ሥነ-ድምፃዊ(Phonological)<br>ሥነ-<br>ምዕላዳዊ(Morphological)<br>ሥነ-አገባባዊ(Grammatical<br>ተግባራዊ(Actional)<br>ሀሳባዊ.(Propositional)<br>ስሜት-ገላጭ (Modal<br>ልሳናት<br>ቅልቀላ(Codeswitching)<br>ማስመሰል (Foreignising)<br>ምትክ (substitution)<br>ማጠቃለያ (Generalisation)<br>ማመላከት (Exemplification)<br>ቃል-ፈጠራ (Wordcoining)<br>ዳግም<br>ማዋቀር(Restructuring) |

| | | |
|---|---|---|
| | | ማብራሪያ (Description)<br>የሰዉነት እንቅስቃሴ(Mime)<br>.መቅዳት (Limitation)፣ወዘተ |

Ellis (1994) እንደገለፀው፣ የ Faerch እና Kasper (1983) ምድብ ከ Tarone (1977) የተሻለ ነው፤ ምክንያቱም የተጠቀሙበት ሥነ-ልቦናዊ ሥነ-ልሣን ሞዴል ተግባቦታዊ ብልሀቶችን ዝም ብሎ ከመዘርዘር ይልቅ በአይነታቸው ለመመደብ ከመረዳቱ ባሻገር የለዩዋቸውን ብልሀቶች ከሁለተኛ ቋንቋ ንድፈ ሀሳብ አንፃር ለማየት ያስችላል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ምደባዎች መረዳት እንደሚቻለውና በ Dornyel (1995) እንደተጠቀሰው የመጀመሪያ ምድብ (varadi 1973: Taeone 1977; Farch and Kasper 1983; and Bialystok 1990) ከዚህ በታች የቀረቡትን ተግባቦታዊ ብልሃቶች ያካትታል፡፡

**1. የማስወገድ ወይም የመቀነስ ብልሀቶች (Avoidance or Reduction Strategies);** Byugate (1987) እንደጻፈው ተናጋሪዎች የማስወገድ ወይም የመቀነስ ብልሃቶችን የሚጠቀሙት በተግባቦት ወቅት ለሚያጋጥማቸው ችግር ከፊል መፍትሄ ሲያገኙለት ወይም ያለሙትን መልዕክት ሙሉ ለሙሉ ማስተላለፍ ሲሳናቸው ነው፡፡ ስለሆነም የማስወገድ ወይም የመቀነስ ብልሃቶች የሚከተሉትን የብልሀት አይነቶች ያካትታሉ፡፡

**ሀ. መደበኛ ቅነሳ (Formal reduction)**

ይህ ብልሀት ተማሪዎች አንድ የተወሰነ የታላሚውን ቋንቋ ቅርፅ ወይም ህግ ትክክለኛነት በሚመለከት እርግጠኞች ካልሆኑ ህጉን የማይጠቀሙበትን ሁኔታ ያመለክታል (Fasil) መደበኛ ቅነሳ ስነ-ድምፃዊ ስነ-ምዕላዳዊ እና ስነ-አገባባዊ ቅነሳዎችን ያካትታል (Faerch and kasper 1984 በCook 1993 እንደተጠቀሰው)፡፡

**ለ. መልዕክትን መተካት (Meaning replacement)**

ተማሪዎች ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት ለማስተላለፍ አንድ እክል ሲያጋጥመው መልዕክቱን ከናካቴው (ጭራሹን) ሳይተወው ሀሳቡን እጅግ በጣም አጠቃላይ በሆነ አባባል የሚገልጽበት ብልሃት ነው (Faerch and kasper 1983 በ Fasil 1992 እንደተጠቀሰው)፡፡

**ሐ. መልክትን መተው (Message abandonment);**

ይህ ብልሃት በቋንቋ ችግር ምክንያት መልክትን በተሟላ ሁኔታ ሳያስተላልፉ መተውን ያመለክታል፡፡ ተማሪው ስለአንድ ፅንስ-ሀሳብ መናገር ይጀምራል፣ ነገር ግን መቀጠል ያቅተውና ንግግሩ መካከል ላይ ያቋረጣል (Brown 1994) ፡፡

2. **ርዕስን ማስወገድ (Topic avoidance)**

የቋንቋ ችግር የሚያስከትሉትን ርዕሶችና ፅንስ-ሀሳቦች መተው ነው፡፡ ተማሪው በአዕምሮው ውስጥ ያለውን ነገር ባለመናገር በተግባቦት ወቅተ የሚያጋጥመውን ችግር የሚያስወግድበት ብልሃት ነው፡፡ (Cook 1993):: ተማሪው ይሄን ብልሀት የሚጠቀመው ስለአንድ ፅንስ ሀሳብ ለማውራት የሚያስፈልጉትን የታላሚውን ቋንቋ እና መዋቅሮች ሰያውቅ ሲቀር ነው፡፡ (Tarone 1981 በ Brown 1994 እንደተጠቀሰው)፡፡

- **የስኬት ወይም የማካካሻ ብልሃቶች (Achievement or compensatory strategies)** ተማሪዎች በተግባቦት ሂደት ችግር ሲያጋጥማቸው ችግሩን ለመቋቋም የሚያስችሉ አማራጭ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ Fail (1992) Corder (1983) ን ጠቅሶ እንደጻፈው እነዚህ ዘዴዎች ተማሪዎች ማንኛውንም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ዘዴ በመጠቀም ለመግባባት ያላቸውን እቅድ ለማሳካት ስለሚጠቀሙባቸው ድፍረትን የሚጠይቁ ብልሃቶች ናቸው፡፡

3. **በአፍ መፍቻ ወይም በሁለተኛ ቋንቋ ላይ የተመሰረቱ ብልሃቶች**

ሀ. **የቃል- በቃል ትርጉም**፡-አንድን ቃል ወይም ፈሊጣዊ አነጋገር ወይም ድርብ-ቃል ወይም ዓረፍተነገር ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ወደ ሁለተኛ ቋንቋ ቃል በቃል መተርጎም ነው (dornyei 1995)፡፡

ለ. **ማስመሰል፡-** ከአፍ- መፍቻ ቋንቋ የተወሰደ ቃልን ከሁለተኛ ቋንቋ ስነ ድምጽ (ምሳሌ ንበት እና ወይም ሥነ-ምዕላድ ጋር አስማምቶ መጠቀም ነው (Dornyei 1995)፡፡

ሐ. **ልሳናት ቅለቀላ** ፡-ከአፍ መፍቻ ወይም ከሦስተኛ ቋንቋ የተወሰደ ቃልን በየቋንቋዎቹ ንበት መሰረት ምንም አይነት ለውጥ ሳይደረግበት አድማጩ ቋንቋውን ቢያውቀውም ባያውቀውም የንግግሩን መሰረታዊ ሀሳብ ሊረዳ ይችላል ከሚል ግምት ቃሉን ወይም ሐረጉን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የቋንቋ ቅርጽ በሁለተኛ ቋንቋ መጠቀም ነው፡፡ (By gate 1987; Brown 1994; Dornyei 1995)፡፡

### 4. በሁለተኛ ቋንቋ ላይ የተመሰረቱ ብልሃቶች

ሀ. **ገለፃ** ትክክለኛ በሆነው የታላሚው ቋንቋ ቃል ወይም መዋቅር ምትክ የተተኳሪውን ቃል ወይም ተግባር ባህርያት (ማለትም፣ መልክ ቅርፅ መጠን ፣አገልግሎት ወዘተ) ወይም ክፍሎች መግለፅ ወይም በምሳሌ ማስረዳት ነው (Tarone and Yule 198; Tarone 1981 በ Brown`1994 እንደተጠቀሰው)፡፡

ለ. **ግመታ** ከሞላ ጎደል የተተኳሪውን ቃል ትርጉም ሊሰጥ በሚችል አማራጭ ቃል መጠቀም ነው (Dornyl 1995)፡፡

ሐ. **ሁለገብ ቃላትን መጠቀም** የተወሰኑ (Specific) ቃላትን ማፍለቅ ሲየቅት አጠቃላይና ትርጉም የለሽ በሆኑ ቃላት መጠቀም ነው (Dornyei 1995)፡፡

መ. **ቃል ፈጠራ** ፡-ይህ ብልሀት ተማሪው ማስተላለፍ የሚፈልገውን ፅንስ-ሀሳብ መግለፅ ይችል ዘንድ የሁለተኛውን ቋንቋ ህግ መሰረት በማድረግ አዲስ ቃል ፈጥሮ የሚጠቀምበት ነው (Tarone 1981 በ Brown 1994 እንደተጠቀሰው)፡፡

ሠ. **ዳግም ማዋቀር** ፡- አንድ የቋንቋ ተጠቃሚ በቋንቋ ችግር ምክንያት የጀመረውን ንግግር ማጠናቀቅ እንደማይችል ሲገነዘብ ንግግሩን ይገታና ማስተላለፍ የሚፈልገውን መልዕክት በተለየ መንገድ በመናገር ንግግሩን (መልዕክቱን ያስተካክለዋል (Faerch and kasper 1983 በFasil 1992 እንደተጠቀሰው)፡፡

### 5. ትብብራዊ ብልሃቶች

ድጋፍ መጠየቅ ተናጋሪው በቀጥታ (ምሳሌ ይሄ ምንድን ነው? ምንድን ነው የሚባለው? እንዲህ ተብሎ ነው የሚጠራው? በማለት) ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ (ምሳሌ የድምጽ አወጣጥን ጎላ በማድረግ ጥቂት ዝም በማለት ዓይን ላይን በመተያየት ግራ በተጋባ አተያይ ወዘተ.) አብሮት ከሚያወራው ሰው ድጋፍ የሚጠይቅበት ብልሃት ነው (Dornyel 1995)፡፡

## 6. ኢ-ልሳናዊ ብልሃቶች

ስነ-ልሳናዊ ባህርይ በሌላው ዘዴ መጠቀም ይህ ብልሃት ተናጋሪው ሊገልፀው የፈለገው ነገር ወይም ፅንስ-ሀሳብ የሰውነት እንቅስቃሴን የእጅ ወይም የጭንቅላት እንቅስቃሴን እና የፊት ገፅታን መለዋወጥ የመሳሰሉትን ዘዴዎች በቃላት ምትክ በመጠቀም የሚገልጽበት ነው (Tarone 1981 በ Brown 1994 እንደተጠቀሰው Dornyei 1995)፡፡

## 7. ማዘናጊያ ወይም ጊዜ-ማግኛ ብልሃቶች

ከአፍ-መፍቻ ቋንቋ ይልቅ ሁለተኛ ቋንቋን ማመንጨት ጊዜ የሚጠይቅ ሂደት በመሆኑ (Dornyei and Kormos 1998) የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሚፈለገው ፍጥነት ቋንቋውን አቀላጥፈው ላይናገሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ተናጋሪዎቹማ ዘናጊያ ወይም ጊዜ-ማግኛ ብልሃቶች ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

በማሚያዎች ወይም በመጠራጠሪያ ዘዴዎች መጠቀም ተናጋሪው ሀሳቡን ለመግለፅ ጥረት በሚያደርግበት ወቅት ተግታዎችን (ዝምታን) ለመሸፈንና የማሰቢያ ጊዜ ለማግኘት የማሚያ ቃላትን ወይም ብልሀቶችን (ምሳሌ፡ ያው፣ ደሞ፣ማለት፣ አሁን፣ በቃ፣አይ፣ኧ…፣እ…፣አው፣ያ…፣ልክ እና ወዘተ. የመሳሰሉትን) ይጠቀማል (ሰፉ 1995)

በአጠቃላይ፡ ከላይ በቀረበው የምደባ ሥርዓት መሰረት ተግባቦታዊ ብልሃቶች በሶስት ዓበይት ክፍሎች ተከፍለው ሊታዩ ይችላል፡፡ እነሱም የማስወገደስ ወይም የመቀነስ ብልሃቶች የስኬት ወይም የማካካሻ ብልሀቶች እና የማዘናጊያ ወይም ጊዜ-ማግኛ ብልሃቶች ናቸው፡፡

በሁለተኛው ወገን የሚጠቀሰው የተግባቦታዊ ብልሃቶች ምድብ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1980ዎቹ ወዲህ እውቅና እያገኘ የመጣው የኒጅሜገን ፕሮጀክት (Nijmegen project) ተመራማሪዎች ምድብ ነው፡፡ በ cook (1993)፡ በ Ellis (1994) እና በ Dornyei (1995) እንደተጠቀሰው ይህ ምድብ የተመሰረተው ቀድሞ የነበረውን ማለትም ከላይ በስፋት ለመቃኘት የተሞከረውን የእነ varadi (1973), Tarone (1977) እንዲሁም የ Faerch እና Kasper (1983) ምድብን በመተቸት ነው፡፡ በቀድሞው ምድብ ላይ ከተሰነዘሩት ትችቶች መካከል Kellerman (1991 በ Ellis 1994 እንደተጠቀሰው) የሰጠው የሚከተለውን ትችት ይገኝበታል፡

የስዕል ማሳያ አዳራሽን) የስዕል ቦታ ወይም ስዕሎችን የምትመለከቱበት ቦታ ብሎ መጥራት ሁለቱም አንድ አይነት ግንዛቤያዊ ሂደትን ያመለክታሉ፡፡ ስለዚህ በታሮን ምደባ (Tarone's Taxonomy) እንደታየው እነዚህ አገላለፆች "ቃል-ፈጠራ" እና ገለፃ ብሎ የተለያየ ስያሜ መስጠቱ አሳሳቢ ነው፡፡ አገላለፆቹ የተለያዩ ስነ ልሳናዊ መከሰቻዎች ስላሉዋቸው ብቻ የተለያዩ ብልሃቶች ተደርገው መቆጠር የለባቸውም፡፡ በአጠቃላይ ምደባዎቹ ቁጥብ) አይደሉም፡፡ ከኒጅሜገን ፕሮጀክት ተመራማሪዎች መካከል የ polisse (1989 በ Cook 1993 እንደተጠቀሰው ጥናት ይጠቀሳል፡፡ Cook (1993) እንደጻፈው፣ የ Poulisse ስራ የተመሰረተው የስነ ልቦናዊ ስነ ልሳን ምሁራን (በተለይም Levelt 1989)

ንግግርን ስለማፍለቅ ሂደት ሁለት ግንዛቤያዊ ክፍሎች አሉት፡፡የመጀመሪያው በአዕምሮአችን ወስጥ መልዕክትን የሚመነጨው ፅንስ-ሀሳብ መስራች ክፍል (Conceptualiser) ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ይህን መልዕክት ወደ ሰዋሰውና ስነድምጽ ልሳናዊ ቅርጾች የሚለውጠው ቀማሪ የሚባለው ክፍል ነው፡፡ ስለሆነም poulisse(1989 በ Cook 1993 እንደተጠቀሰው) እንደሚታምነው ሁለተኛ ቋንቋን የማፍለቅ ሂደት ተገቢ የሆኑትን ቃላት ባለማወቅ ምክንያት ሲቋረጥ ተናጋሪው ወደ ጽንስ ሀሳባዊ ደረጃ በመመለስ ወይም አማራጭ ስነ ልሳናዊ ቅርጾችን በመሞከር ችግሩን ያካክሳል፡፡

የኒጅሜገን ፕሮገፎ ተመራማዎች ከላይ የቀረቡትን መሰረታዊ ሀሳቦች መነሻ በማድረግ ያቀረቡትን ተግባቦታዊ ብልሃቶች ምድብ በ Dornyei (1995)፣ በEllis (1994) እና በCook (1993) እንደተጠቀሰው የሚከተለው ነው፡፡

ሀ. **ጽንሰ ሀሳባዊ ብልሃቶች**፡- ታላሚውን ሀሳብ ግልጽ ለማድረግ ባሉት ሥነ-ልሳናዊ ግብአቶች ለመጠቀም ያስችላሉ፡፡እነዚህ ብልሃቶች ተንታኝ እና ጥቅል ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

**ለ.ተንታኝ ብልሃቶች**፡- የፅንሰ-ሀሳቡን ወይም የነገሩን የተወሰነ ባህሪያት ይለያሉ (ምሳሌ፣ ገለፃ ማብራሪያ ፣ አሳጥሮ መግለፅ ፡፡

**ሐ. ጥቅለ ብልሃቶች**፡- ከታላሚው ነገር (ሀሳብ) ጋር የተወሰኑ ባህርያትን የሚጋሩ የተለየ ነገር ስያሜ በመጠቀም ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ (ምሳሌ ግመታ

**መ.ሥነ ልሳናዊ ብልከሃቶች**፡-ተናጋሪው ሥነ-ልሳናዊ እውቀቱ እንዲጠቀም ያስችሉታል፡፡

**ሠ.ሥነ-ምዕላዳዊ ፈጠራ** ፡- የሁለተኛውን ቋንቋ ሥነ-ምዕላዳዊ ህጎች በአንድ የሁለተኛ ቋንቋ ቃል ላይ ተግባራዊ በማድረግ አዲስ ቃል መፍጠር ነው፡፡

**ረ. ማሸጋገር** ፡- የአፍ-መፍቻን ወይም የሦስተኛን ቋንቋ ግብአት በመጠቀም መልዕክት ለማስተላለፍ የሚደረግ ሙከራ ነው፡፡ ልሳናት ቅልቀላ ማስመሰል እና የቃል በቃል ትርጉም ናቸው፡፡

## 2.1.6 በተግባቦታዊ ብልሃቶችና በቋንቋ መማር መካከል ያለው ግንኙነት

ከቅርብ አመታት ወዲህ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዘርፍ ከተደረጉ ለውጦች ዋነኛውና መሰረታዊው ከመምህሩ ከመማሪያ መጽሃፉና ከስነ ዘዴው ይልቅ ለተማሪውና ለቋንቋው ለመዳ ሂደት ትኩረት መስጠቱ ነው (Yule 1996):: ተማሪዎች ተገቢ የሆነውን የቋንቋ

አጠቃቀም ብቻ ሳይሆን ቋንቋውን ይበልጥ የሚያብሩበትን ሂደት ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ መሰረታዊ ሃሳብ ደግሞ የብልሃት ችሎታን ከማጎልበት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ብልሃት ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሊኖራቸው ከሚችለው ተሳትፎ ጋር ይቆራኛል፡፡ (Brown (1994) የተማሪዎችን የብልሃት ችሎት ማጎልበት ያለዉን ስነ-ትምህርታዊ ጠቀሜታ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ለመማር አመቺ እንዲሆን ተማሪዎችን እንዴት መማር እንደሚችሉ ማስተማር በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ በሰርካዊ የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ ብልሃቶችን በመጠቀም የመማር አቅምን በመፍጠር ላይ ማተኮር አለበት፡፡ይህ ተግባር ቀጣይነት ካለዉ ከተማሪዎች የጥናት ፕሮግራም ጋር ተቀናጅቶ የተማሪዎችን በራስ ጥረት የመማር አቅም ስለሚያሳድግ ብሎም የተማሪዎችን ችሎታ ለማጎልበት አስተዋጽኦ ስለሚኖረው የቋንቋ ትምህርት ተጨባጭ በሆነ መንገድ ተግባራዊ የሚሆንበት ነው፡፡

ተግባቦታዊ ብልሃቶች ከተማሪ ብልሃቶች መካከል አንዱ በመሆናቸዉ ተማሪዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚሄደዉን ችሎታቸዉን በሁለተኛ ቋንቋ ግልጽ መልእክት ለማስተላለፍ እንዲጠቀሙበት የሚያስችሏቸው ዘዴ ናቸው፡፡ እነዚህ ልሳናዊና ኢ-ልሳናዊ ተግባቦታዊ ብልሃቶች በሚከተሉት ሁለት አበይት ምክንያቶች ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1. ቋንቋውን በወጉ ካለማወቅ የተነሳ በተግባቦት ወቅት ችግር ሲያጋጥም የተግባቦቱ ሂደት እንዳይቋረጥ ችግሩን ለማካካስ እና
2. ተግባቦትን የበለጠ ስኬታማ ለማድረግ ናቸው (Canale 1983)፡፡

ተግባቦታዊ ብልሃቶች ተማሪዎች በቋንቋዉ እንዲለማመዱና ተገቢነት ያላቸውን አዳዲስ የቋንቋ አጠቃቀሞች እንዲቀስሙ እድል ይሰጣቸዋል (Dornyei 1995)፡፡በተጨማሪም በንግግር ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቅረፍ ስለሚረዱ የማሰቢያ ጊዜን ይቀንሳሉ፡፡ እንዲሁም የንግግር ቅልጥፍናን (አፈ-ተክነትን) ያሻሽላሉ፡፡

ይሁን እንጂ ተግባቦታዊ ብልሃቶችን በትምህርትነት ስለመስጠት በሚመለከት አሉታዊ አስተያየቶችም ይሰነዘራሉ፡፡ አንዳንድ የተግባራዊ ስነ-ልሳን ተመራማሪዎች (ለምሳሌ፡- Bialystok 1983,በ Ellis 1994 እንደተጠቀሰው፤እንደዚሁም Kellerman 1991,1993 በ Singleton 1999 እንደተጠቀሰው) የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪዎችና የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች ተመሳሳይ መሆናቸውን በጥናታቸው በማረጋገጣቸው የተነሳ ተማሪዎች ተግባቦታዊ ብልሃቶችን ከአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው ስለሚለምዱ ሁለተኛ ቋንቋቸውን ሲማሩ ተግባቦታዊ ብልሃቶችን መማር አያስፈልጋቸውም ይላሉ፡፡ ስለሆነም Kellerman (1991 በ Ellis 1994 እንደተጠቀሰው)

ይህን ሀሳብ "የማማካሻ ብልሃቶችን በትምህርትነት ለመስጠት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ስለሌለ ተማሪዎችን ቋንቋውን በሚገባ በማስተማር ብልሃቶችን ለእነሱ መተው ይሻላል፡፡
በመሆኑም ይህ ጥናት የተካሄደው ከላይ ከተጠቀሱት በርካታ ብልሃቶች ውስጥ የFaerch እና Kasper ምድብ ተከትሎ ነው፡፡

## 2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ይህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ጥናቶች የሚዳሰሱበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚው ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር በቀጥታና ኢ-ቀጥታ በሆነ መንገድ ቅርበት ያላቸው ጥናቶች ለማግኘት ችሏል፡፡ ጥናታዊ ፅሑፎቹ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረቡ ሲሆኑ እንደ ሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያ ጥናት ከተማሽ የወጉ(2014) ‹‹የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ (በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ ዞን በጉዳያ ቢላ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሦስት የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተተኳሪነት›› በሚል ርዕስ በ2014 ዓ.ም የ2ኛ ድግሪ ማሟያ ያደረገችው ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማም በኦሮሚያ ክልል በምሥራቅ ወለጋ ዞን ጉዳያ ቢላ ወረዳ የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበርን መፈተሽ ነው ፡፡ጥናቱ የተከተለው አይነታዊና መጠናዊ ምርምርን ዘዴ ሲሆን አቀራረቡም ገለጻዊ ዜደ ነው፡፡በዚህ መሰረት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት በመምህራን ላይ ትኩረት ያደረገ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ምልከታ ተከናውኗል፡፡

የጥናቱ አቅራቢዋ በግኝቷ የተወሰኑ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ዓላማ በዝርዝር አለማቅረባቸውን፣ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ እንድታገዝ አለመሞከራቸውን፣በቋንቋው ተጠቅመው በንግግር ሀሳባቸውን በነፃ የሚገልጹበት ሁኔታ አለማመቻቸታቸውን፣የንግግር ማስተማሪያ ደረጃዎችን በተገቢው መንገድ አለማከናወናቸውን፣ከመማሪያ መጽሐፉ ጎን ለጎን የተማሪዎችን ፍላጎት ሊያነሳሳ የሚችል ክንውን በጥንቃቄ አለመመረጡ፣የዕለቱ የንግግር ክሂል ትምህርት ግልጽ በሆነና በማይረሳ መልኩ አለመቅረቡ፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የመናገር እድል አለመሰጠቱ እና ለመናገር ደፋር ያልሆኑ ተማሪዎችን ለማበረታታት ጥረት አለመደረጉን የጥናቱ መረጃ እንደሚጠቁም በማስረዳት ጥናቷን ቋጭታለች፡፡

ሁለተኛ ንጋቱ (2000) በሲዳምኛ አፍቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው የመማር ብልሀቶች ምርመራ በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ያደረገው ጥናት ነው፡፡የጥናት አላማም በሲዳምኛ አፍቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው የመማር ብልሀቶች መመርመር ነው፡፡ጥናቱ የተከተለው አይነታዊና መጠናዊ ምርምርን ሲሆን አቀራረቡም ገለጻዊ ዜደ ነው፡፡በውጤቱም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አዳዲስ ቃላትን በአዕምሯቸው መዝግበው የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር የሚያግዟቸውን የትውስታ ብልሀቶች በትምህርቱ ሂደት የሚሰማቸውን የፍርሀት፣የጭንቀት፣አሉታዊ አመለካከትና ዝንባሌ ለመቆጣጠር ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሀቶች እንዲሁም እየጠየቁ የመማር ማህበራዊ ብልሀቶችን እንደሚገለገሉባቸው ተገልፆል፡፡

ሶስተኛው ዘርሁን (2010) በከፊኛ አፍቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ስናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች ትንተና በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ያደረገው ጥናት ነው፡፡የጥናቱ አላማም በከፊኛ አፍቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች መመርመር ነው፡፡ጥናቱ የተከተለው አይነታዊና መጠናዊ ምርምርን ሲሆን አቀራረቡም ገለጻዊ ዜደ ነው፡፡በጥናቱ ውጤትም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የማስወገድ ፣ የስኬት እና የማዘናጊያ ዋና ዋና ብልሀቶች መገልገላቸውን አመላክቷል፡፡

ጥናቶቹ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ዋና ጉዳይ የመማርና ተግባቦታዊ ብልሀቶች ላይ የትንተና ጥናት ሲሆን ለጥናቱም መነሻ በመሆን የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ጥናቶች በሸክኛ አፋቸውን የፈቱና አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተመሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ሲያደርጉ የሚያጋጥማቸውን የቋንቋ ችግር ለመፍታት የሚጠቀሙባቸውን ተግባቦታዊ ብልሀቶች አያሳዩም፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናትም የተጠናው ይህን ክፍተት ለመሙላት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

በምዕራፍ አንድ ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ትኩረት በሽክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸውን ተግባቦታዊ ብልሀቶች መለየት ነው፡፡፡ በመሆኑም የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የመረጃ ምንጮች አመራረጥ፣የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነትና አደረጃጀት፣የመረጃ አሰባሰብ ሂደትና የጥናቱ አጠናን ስልት በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ጥናቱም የተከተለው አይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴ ሲሆን አቀራረቡም ገለፃዊ ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ይህ ንድፍ የተመረጠበትም ምክንያት ጥናቱ በደለጻ መልክ የሚቀርብ በመሆኑ ነው፡፡

## 3.2 የጥናቱ አካላይ

ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል ሸካ ዞን በየኪ ወረዳ በሚገኘው ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ነው፡፡ጥናቱ ያተከረውም በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ በሚማሩ ሽክኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ 16 ምድቦች ይገኛሉ፡፡ አጠቃላይ የተማሪዎች ብዛት 1037 ናቸው፡፡በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም ይገኛሉ፡፡በአጠቃላይ በወረዳው የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም የዚህ ጥናት አከላይ ናቸው፡፡

## 3.3 የናሙናዎች አመራረጥ

### 3.3.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ዉስጥ ከሚገኙ አራት (4) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ የኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አላማ ተኮር ናሙናነት ተመርጧል።ምክንያቱም የታላሚዉን ናሙና አባላትን የአፍ-መፍቻ ቋንቋ የሚናገሩ ተማሪዎች ከሌሎች ትምህርት ቤቶች የበለጠ በብዛት የሚማሩበት ትምህርት ቤት በመሆኑ የተለያየ የንግግር ብቃት ደረጃ ያላቸዉን ተማሪዎች ለማግኘት ሰፊ ዕድል ይሰጣል ተብሎ ስለተገመተና በአብዛኛዉ አፋቸዉን በአማርኛ ያልፈቱ ተማርዎች የሚማሩበት በመሆኑ ትምህርት ቤቱ ለጥናቱ አስፈላጊ ሆኗል።

### 3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው የተማሪዎች የክፍል ደረጃ ዘመነኛ ክፍል ነው፡፡ ክፍሉ የተመረጠው በዓላማ ተኮር ናሙና ሲሆን የዘጠነኛ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ክፍል መሆኑና በዚህ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎቹም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በገጠራማ ቀበሌ የሚያጠናቅቁ በመሆናቸው ለዚህ ጥናት በቂ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለ ታመነ ነው፡፡በተጨማሪም ተማሪዎቹ እስከ ትምህርት ዘመን ማብቅያ ከለሎች የክፍል ደረጃ በተሻለ በትምህርት ቤት ስለሚቆዩ መረጃ ለመሰብሰብ አመቺ የክፍል ደረጃ በመሆኑ ነው፡፡

### 3.3.3 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

የጥናቱ ተተኳሪዎች የትምህርት ቤቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ የጥናቱ አካላት እንዲሆኑ የተፈለገውም ተማሪዎቹ ከአንድ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ገጠራማ ቀበሌ ውስጥ ስለሚያሳልፉ በይበልጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስለሚጠቀሙ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲመጡ ለቋንቋው አዲስ በመሆናቸው ከሌሎቹ የክፍል ደረጃዎች የተሻለ መረጃ ያስገኛሉ ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡በተጨማሪም እስከ ትምህርት ዘመኑ ማብቂያ ድረስ በትምህርት ቤቱ ስለሚቆዩ አስፈላጊውን የጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብ ስለ ምያመች ነው፡፡

የኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አፋቸውን በሸክኛ ቋንቋ የፈቱ 196 (102 ወንድ 94 ሴት) ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከነዚህ ተማሪዎች መካከል የስብጥር ወይም ሽንሽን የንሞና ዘዴን በመጠቀም በትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ መንፈቀ-ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና ውጤት ደረጃ (range) መሰረት ስልሳ(60) ተማሪዎችን በመምረጥ የንግግር ብቃት ደረጃ መለኪያ ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም ውጤታቸውን መሰረት ማድረግ የተፈለገው በቋንቋው የተለያየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በጥናቱ ሊሳተፉ የሚችሉበትን ዕድል ለማስፋት ነው፡፡ ፈተናውን የሚወስዱት ተማሪዎች በ ስልሳ የተገደበበት ምክንያት እጅግ ሰፋ ባለ መልኩ የንግግር ፈተና መስጠት ከጊዜ፣ ከገንዘብና ከሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች አንፃር አሰቸጋሪ ስለምሆን ነው፡፡

### 3.3.4 የመምህራን አመራረጥ

ጥናቱን ከግብ ማድረስ ይቻል ዘንድ በጠቅላይ ናሞና ስልት በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

### 3.5.1 የንግግር ፈተና

ይህ ጥናት በዋናነት የመረጃ መሰብሰቢያ ያደረገው ፈተና ነው፡፡ እንደሚታወቀው የንግግር ብቃት ደረጃ መለኪያ ፈተና የተማሪውን አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ያለውን የመናገር ብቃት ለመለካት ያገለግላል (ሰፋ1995 ስለሆነም የፈተናው ይዘት የተመሠረተው ፈተናውን የሚፈትኑትን ግለሰቦች በመከታተል ላይ ባሉት የቋንቋ ትምህርት ይዘት ላይ ሳይሆን ግለሰቦቹ በቋንቋው ብቃት ያላቸው ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሚያስችሉት ቋንቋውን በመጠቀም ሊያከናዉኗቸው በሚገባቸው ይዘቶች ላይ ነው( ሰፋ 1995 Hughes 1989)፡፡ ፈተናውም ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡እነሱም ቃለ መጠይቅና ያልተሟላውን መረጃ መሙላት ነው።ቃለ መጠይቅ የንግግር ችሎታን ለመለካት ከሌሎች ዘዴዎች እጅግ የተሻለና የተለመደ የንግግር ፈተና ዓይነት መሆኑን (Brown and Yule 19 83) ይገልፃሉ። በንግግር ፈተናው የመጀመሪያ ክፍል ተማሪዎቹ ራሳቸውን እንዲገልፁ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ሌላው ተማሪዎቹ ፈታኞቻቸዉን በመጠየቅ የሚያሟሉት ያልተሟላ ሰንጠረዥ በፈተናው ሁለተኛ ክፍል ቀርቧል። ፈተናውም በሰዓት የተገደበ ነው።

### 3.5.2 ቃለ መጠይቅ

እንዴ Dorneyei (2007) አገላለፅ " ቃለ መጠይቅ አንድ ተመራማሪ መረጃ ከሚያገኝባቸው መሳሪያዎች ውስጥ አንደ ሲሆን ከባለ ጉዳዮቹ ጋር በግንባር በመገኘት በቃል የሚደረግ ጥያቄ ነው፡፡" በማለት ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ቃለ መጠይቅ ለዚህ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተመረጠ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን ቃለ መጠይቁ የተደረገው ለጥናቱ በተመረጡት የዘጠነኛ ክፍል የሸክኛ ቋንቋ አፈ ፈት ተማሪዎች እና መምህራን ጋር ነው፡፡አጥኚው መረጃውን ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ የተጠቀመበት ምክንያት ተማሪዎቹ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች የትኞቹ

እንደሆነ በተግባር ስያከኛውኑ ለመለየት ስለሚያስችልና ከመምህራንም ስለ ተማሪዎች ትግባቦት ችሎታ ፊት ለፊት ለመጠየቅ ስለ ሚረዳ ነው፡፡

### 3.5.3 የክፍል ውስጥ ምልከታ

በተጠኚ ተማሪዎች የሚተገበረውን የክፍል ውስጥ የተግባቦት ብልሃቶች አተገባበርን ለመገምገም ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በጥቅም ላይ ውሏል፡፡የተግባቦት ብልሃት ክንዉኖችን ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ እንዴት እየተገበሩት እንደሆነ ለማየት የክፍል ዉስጥ ምልከታን በደጋፍ የመረጃ መሰብሰቢያነት ለጥናቱ ተመርጧል፡፡ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ የክፍል ዉስጥ ምልከታ ማረጋገጫ ዝርዝር (check list) ተዘጋጅቷል፡፡የክፍል ዉስጥ ምልከታ ማረጋገጫ ዝርዝሩ የተዘጋጀዉም ተዛማጅ ጥናቶች የተጠቀሙባቸዉን መሰረት በማድረግ፣የማረጋገጫ ዝርዝሮች በአማካሪ ከታዩ በኋላ የማሻሻል ስራ ተደርጎበት በስራ ሊይ ዉሏል፡፡

ሁለም የምልከታ ነጥቦች ዝግ መጠይቆች ናቸው፡፡ይህ የሆነበት ምክንያት Dornyei (2007, 163) እንደሚለት የተደራጀ ምልከታ በክፍል ዉስጥ የሚከናወኑ የተወሰኑ የትኩረት አቅጣጫዎችና የምልከታ ነጥቦች ላይ በማተኮር የሚከናወን በመሆኑ ነዉ፡፡ ስለዚህ የተጠኚ ተማሪዎች ክፍሌ ጊዜ በማመቻቸት ለአምስት ጊዜ ምልከታ ተደርጓሌ፡፡

## 3.6 የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓትና ተግባራት

ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በዋናነት የተሰበሰቡት የድምፅ መቅረጫ መሳሪያ በመጠቀም ነው፡፡ ይሁን እንጂ በድምጽ መቅረጫ መሳሪያ የተሰበሰውን መረጃ የበለጠ ለማጠናከር ጠቃሚ መረጃዎችን ማግኘት ይቻል ዘንድ የመማሪያ ክፍል ምልከታ እና ከመምህራን ጋር በተማሪዎች የንግግር ችሎታ በተመለከተ አጭር ቃለ መጠይቅ ተካሂዷል፡፡በመማሪያ ክፍል ምልከታ ወቅት መረጃዎች የተሰበሰቡት የምልከታ ቅጽ በመጠቀም ሲሆን ከቃለ መጠይቁ መረጃዎች የተሰበሰቡት ማስታወሻ በመያዝ ነው፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ዋና መረጃዎች የተሰበሰቡት ግን ተተኳሪዎቹ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በማድረግ ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ለማጥናት ተግባር ተኮር ስነዘዴን መጠቀም ይቻላል (በዘርሁን 2010) እንደጠጠቀሰው፡፡

ይህ ስነ ዘዴ ከተማሪዎቹ የወዲያውነት ባህርይ ያለው ንግግር ለማመንጨት እንደሚረዳ ይገመታል (Tarone and Yule 1989)፡፡ ስለሆነም፣ በተለያዩ ተግባቦታዊ አውዶች

ተተኳሪ አባላት በተለይም ከመምህራኖቻቸውና ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በአማርኛ በሚያደርጉት ቃላዊ መሰተጋብር የሚጠቀሙባቸውን ተግባቦታዊ ብልሃቶች ዓይነትና የተለያዩ የንግግር ብቃት ደረጃ ባላቸው ተማሪዎች መካከል ያለውን የተግባቦታዊ ናሙና አባላት በነፍስ ወከፍ ሦስት የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በማድረግ ክንውኖቹ በድምጽ መቅረጫ መሳሪያ እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡

ተማሪዎቹ ያከናወኗቸው ተግባራት ተግባር አንድ (ቃለመጠይቅ)፣ ተግባር ሁለት (የስዕል ገለፃ) እና ተግባር ሶስት (ትርጎማ) የሚሉ ናቸው፡፡ በአፍላቂ ክሂሎች ላይ ለሚደረጉ ጥናቶች ከአንድ የበለጡ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም የጥናቱን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት የበለጠ ከፍ ስለሚያደርገው (Nunan 1992) ተማሪዎቹ እነዚህን ሶስት የተለያዩ ተግባራት እንዲያከናውኑ ተደርጓል፡፡

## 3.6.1 ተግባር አንድ (ቃለመጠይቅ)

ተተኳሪዎቹ በቅድሚያ ያከናወኑት ተግባር ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ቃለ መጠይቁ ለ15 ደቂቃ ያህል የተካሄደ ሲሆን ይህም በተማሪዎቹ የህይወት ገጠመኝ ላይ የሚያተኩሩ ጥያቄዎችን የያዘ ነበር፡፡ ቃለ መጠይቅ ተማሪዎቹ ተግባቦታዊ በሆነ መልኩ ሀሳባቸውን ወዲያው አፍልቀው እንዲናገሩ እድል የሚሰጥ በመሆኑ በተግባቦዊ ብልሃቶች ላይ ምርምር ለማካሄድ የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በስፋት ጥም ላይ ይውላል፡፡

## 3.6.2 ተግባር ሁለት (የስዕል ገለፃ)

ተማሪዎቹ ሁለት ዓይነት ስዕሎችን እንዲገልፁ ተደርጓል፡፡ ስዕል አንድ ተማሪዎቹ የተለያዩ የሽካ ባህላዊ እቃዎችን ምንነት እንዲገልፁ የሚጠይቅ ሲሆን ስዕል ሁለት ደግሞ ስዕሉ የሚገልፀውን ታሪክ አብራርተው እንዲናገሩ ያዛል፡፡ በስዕል አማካኝነት የቀረቡትን ባህላዊ ዕቃዎች ተማሪዎቹ በቅርበት የሚያውቋቸውና የሚገለገሉባቸው ቢሆኑም የአንዳንዶቹን እቃዎች ስሞች በአማርኛ እንደማያውቋቸው ይገመታል፡፡ ተማሪዎቹ ሁለቱን ስዕሎች በጊዜ ሳይገደቡ ሽክኛ ለማይችል ቢጤአቸው ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳ ይሁኔታ በተግባቦታዊ ብልሃቶች ላይ የሚያተኩሩ ሌሎች ጥናቶችም ከናሙናው ታላሚ አባላት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የስዕል ገለፃን ተጠቅመዋል፡፡

### 3.6.3 ተግባር ሶስት (ትርጎማ)

በዚህ ተግባር ተተኳሪዎቹ የሽክኛ በቃል የተነገሯቸውን ታሪኮች ወደ አማርኛ ተርጉመዋል፡፡ ታሪኩ ሰፋ ያለ ሲሆን ይዘቱም ስለ ሽካ ንጉስ የቀብር ስነ ስርዓት የሚያወሳ ነው፡፡ ተተኳሪዎቹ በተለያየ አጋጣሚ በእለታዊ ኑሯቸው ከአማርኛ ወደ ሽክኛ ለዘመዶቻቸው እንደሚተረጉሙ ይገመታል፡፡ ስለዚህ ለዚህ ተግባር ብዙም እንግዳ አይደሉም፡፡ ተማሪዎቹ በዚህ ተግባር የሽክኛ አፍ-ፈት የሆነ ቢጤአቸው በሽክኛ የነገራቸውን ታሪክ ሽክኛ ለማይችለው ቢጤአቸው ተናግረዋል፡፡

ትርጎማ የሚተረጎመውን ነገር ማዳመጥንና የተደመጠውን ነገር ደግሞ መልሶ በታላሚው ቋንቋ መናገርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ተማሪዎቹ የሚፈጽሙት ተግባር ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ቋንቋን ከማፍለቅ ሂደት ጋር እንደሚቀራረብ ይገመታል ስለዚህ ትርጎማ በተግባቦታዊ ብልሃቶች ላይ ምርምር ለማካሄድ በአንዳንድ የተግባራዊ ስነ ልሳን ምሁራን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በድምጽ መቅረጫ የተካሄደው እያንዳንዱ ተሳታፊ አባል በነፍስ ወከፍ በአንድ የተለየ መጠነኛ ስፋት ባለው ክፍል ውስጥ ከቢጤአቸው ጋር በመሆን ተግባራቱን ሲያከናውኑ ነው፡፡ የሚሰበሰበው መረጃም የበለጠ አስተማማኝ ይሆን ዘንድ ሁለት መምህራን ተማሪዎቹ ተግባራቱን ሲያከናውኑ የተማሪዎቹ ቢጤ ሆነው እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ አንደኛው መምህር በአማርኛ አፋን የፈታና የሽክኛ ቋንቋ የማይችል በመሆኑ በተግባር 1 በጠያቂነት በተግባር 2 ፣ እና በተግባር 3 ደግሞ በአድማጭነት ተሳትፏል፡፡ ሁለተኛው መምህር የሽክኛ አፍ ፈት በመሆኑ ተማሪዎቹ ተግባር 3 ን ብቻ ሲያከናውኑ የሚተረጎመውን ነገር ለተጠኝዎቹ በቃል በመንገር ተሳትፏል፡፡ እነዚህ መምህራን የተመረጡትና መረጃው በሚሰበሰብበት ጊዜ የተሰጣቸው ድርሻ የተሳታፊው ማንነት በተማሪዎቹ የተግባቦታዊ ብልሃቶች አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድር ታስቦ ነው፡፡ መምህራኑ ተማሪዎቹን የሚያስተምሩ በመሆናቸውና ተማሪዎችም ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት ምንነት ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ ተመሳሳይ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በማድረግ አጭር ስለጠና ለአንድ ሰዓት ያህል ስለተሰጣቸው ተማሪዎቹ ሶስቱን ተግባራት እምብዛም ሳይቸገሩ አከናውነዋል፡፡

በተግባር ተኮር ሥነ ዘዴ አማካይነት ለተሰበሰቡት መረጃዎች አጋዥነት የመማሪያ ክፍል ምልከታና ቃለ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ጥቅም ላይ መዋላቸውን ቀደም ሲል መጠቆሙ ይታወሳል፡፡ የመማሪያ ክፍል ምልከታው ዓላማ

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙን ተግባቦታዊ ብልሃቶች መለየት ስለሆነ የክፍል ምልከታ ቅፁ የተዘጋጀው Domyei (1995) የተለያዩ የተግባራዊ ሥነ-ልሳን ምሁራንን (Varadi 1973; Tarone 1977, Faerch and Kasper 1983 እና Bialystok 1990) በተጨማሪም Bygate (1987) ያቀረቧቸውን የተግባቦታዊ ብልሃቶች በማቀናጀት ነው (አባሪ 5ን ይመልከቱ)፡፡ እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ተማሪዎቻቸው በአማርኛ ሲናገሩ ስለሚጋጥሟቸው ችግሮች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

## 3.7 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

በድምፅ መቅረጫ መሳሪያ ምዝግብ አማካይነት በተግባር ተኮር ሥነ ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎች በጽሁፍ በወጉ ከተመዘገቡ በኋላ ዓይነታዊ እና መጠናዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ ተተኳሪዎቹ ሶስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ የትኞቹን ብልሀቶችና ብልሃቶቹ በቋንቋው ያላቸውን ችሎታ እንዲያሻሽሉ የሚረዱ ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የተገኘው ውጤት በዓይነታዊ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ እንደዚሁም በደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ጥቅም ላይ በዋሉት የክፍል ምልከታና ቃለ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎችም እንዳስፈላጊነታቸው በትንተናው ውስጥ ተካተዋል ፡፡

# ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ የጥናቱን የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ እንደቅደም ተከተላቸው ማቅረብ ነው፡፡ የጥናቱ ጥያቄዎች የሸክኛ አፍ-ፈት የዘጠኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች የትኞቹ ናቸው? እና ተተኳሪዎቹ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች በቋንቋው ያላቸውን ችሎታ እን ድያሻሽሉ የሚረዱ ናቸው? የሚሉት ሲሆኑ ትንተናው የጥናቱን ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ በቅደም ተከተል ቀርቧል፡፡

## 4.1 የመረጃዎች ትንተና

### 4.1.1 አፋቸውን በሸክኛ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች የትኞቹ ናቸው?

ከዚህ ጥናት ማረጋገጥ እንደተቻለው ተተኳሪዎቹ ሶስቱን ተግባራት (ቃለ-መጠይቅ፣ የስዕል ገለጻና ትርጎማ) ሲያከናውኑ ተግባቦታዊ ብልሃቶችን ተጠቅመዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ ተማሪዎቹ ሶስቱን ተግባሮች ሲያከናውኑ የተጠቀሙባቸውን የተግባቦታዊ ብልሃቶች አይነቶችን የአጠቃቀም ድግግሞሽ መጠን ያመላክታል፡፡

## ሠንጠረዥ4.1. የተጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶችና የድግግሞሽ መጠን

| ተ.ቁ | የተግባቦታዊ ብልሃት ዓይነት | የአጠቃቀም ድግግሞሽ መጠን | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ተግባር 1 | ተግባር 2 | ተግባር 3 | ብዛት | % |
| 1 | የማስወገድ ወይም የመቀነስ ብልሃቶች | | | | | |
| | 1.1 መደበኛ ቅነሳ | 35 | 27 | 74 | 136 | 13.23 |
| | 1.2 መልእክትን መተካት | 55 | 32 | 110 | 197 | 9.17 |
| | 1.3 መልእክትን መተው | 4 | 3 | 7 | 14 | 0.45 |
| | 1.4 ርዕስን ማሰወገድ | 4 | 1 | 6 | 11 | 0.35 |
| | ድምር | 420 | 243 | 397 | 1060 | 33.97 |
| | % | 13.46 | 7.79 | 12.72 | | |
| 2 | የማካካሻ ብልሃቶች | | | | | |
| | 2.1 የአፍ-መፍቻ/ ሦስተኛ ቋንቋ-ተኮር ብልሃቶች) | | | | | |
| | 2.1.1. የቃል በቃል ትርጉም | 3 | 2 | 91 | 96 | 3.08 |
| | 2.1.2. ማስመሰል | 9 | 4 | 31 | 44 | 1.41 |
| | 2.1.3. የልሣናት ቅልቀላ | 32 | 46 | 37 | 115 | 3.68 |
| | ድምር | 44 | 52 | 159 | 255 | 8.17 |
| | % | 1.41 | 1.66 | 5.09 | | |
| | 2.2 ሁለተኛ ቋንቋ ተኮር ብልሃቶች | | | | | |
| | 2.2.1. ገለጻ | 22 | 31 | 1 | 54 | 1.73 |
| | 2.2.2. ግመታ | 66 | 68 | 72 | 206 | 6.60 |
| | 2.2.3. ሁለገብ ቃላትን መጠቀም | 113 | 92 | 8 | 213 | 6.83 |
| | 2.2.4. ቃል-ፈጠራ | 13 | 20 | 9 | 42 | 1.35 |
| | 2.2.5. ዳግም-ማዋቀር | 105 | 68 | 83 | 256 | 8.20 |
| | ድምር | 319 | 279 | 173 | 771 | 24.71 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | % | 10.22 | 8.94 | 5.54 | | |
| | 2.3. ድጋፍ መጠየቅ | 1 | 8 | 3 | 12 | 0.39 |
| | % | 0.03 | 0.25 | 0.09 | | |
| | 2.4. የሰዉነት እንቅስቃሴ | 72 | 64 | 13 | 149 | 4.78 |
| | | | | | | |
| | % | 2.3 | 2.05 | 0.41 | | |
| | ድምር | 436 | 403 | 348 | 1187 | 38.05 |
| | % | 13.97 | 12.92 | 11.15 | | |
| 3 | ማዘናጊያ ወይም ጊዜ-ማግኛ ብልሃቶች | | | | | |
| | 3.1. ማሚያዎች /መጠራጠሪያ ዘዴዎች | 510 | 277 | 86 | 873 | 27.98 |
| | % | 16.34 | 8.87 | 2.75 | | |
| | ጠቅላላ ድምር | 1366 | 923 | 831 | 3120 | 100 |
| | % | 43.78 | 29.58 | 26.63 | | |

በሰንጠረዥ 4.1 የቀረበው መረጃ እንደሚጠቁመው ተተኳሪዎቹ ሦስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ 33.97% የማሰወገድ ብልሃቶችን ፣38.05% የማካካሻ ብልሃቶችንና 27.98% የማዘናጊያ ብልሃቶችን ተጠቅመዋል፡፡ ከሦስቱ ዋና ዋና የተግባቦታዊ ብልሃቶች መካከል ተማሪዎቹ በአብዛኛው የተጠቀሙት የማካካሻ ብልሃቶች ነው፡፡

ከሦስቱ ዋና ዋና ተግባቦታዊ ብልሃቶች አንዱ የማስወገድ ብልሃት ነው፡፡ ተተኳሪዎቹ ሦስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ 26.86% መደበኛ ቅነሳ፣ 6.31% መልዕክትን መተካት፣ 0.45% መልዕክትን መተው እና 0.35% ርዕስን ማሰወገድ በሚባሉት ብልሃቶች ተጠቅመዋል፡፡ ይህ አሃዛዊ መረጃ እንደሚጠቁመው ከአራቱ የማስወገድ ብልሃቶች መካከል ተማሪዎቹ በይበልጥ የተጠቀሙት መደበኛ ቅነሳን ነው፡፡

የተማሪዎቹ የማሰወገድ ብልሃቶች አጠቃቀም ከአከናወኗቸው ተግባራት አንጻር ብንመለከት ተግባር አንድን ሲያከናውኑ 13.46%፣ ተግባር ሁለትን ሲያከናውኑ 7.79%፣ ተግባር ሶስትን ሲያከናውኑ ደግሞ 12.72% የማሰወገድ ብልሃቶችን በብዛት ተጠቅመዋል፡፡ ከእነዚህ ሶስት ተግባራት መካከል ተማሪዎቹ በርካታ የማስወገድ

ብልሃቶችን የተጠቀሙት በተግባር አንድ ላይ ነው፡፡ ተማሪዎቹ በተግባር አንድ ከተጠቀሙባቸው የማስወገድ ብልሃቶች መካከል በአብዛኛው (85%) የተጠቀሙት በመደበኛ ቅነሳ ነው፡፡ ይህ መረጃ ተማሪዎቹ በአብዛኛው ቋንቋን በመጠቀም መግባባት እንደሚችሉ ቢጠቁሙም ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን ሲጠቀሙ ድምጸ-ልሣን፣ ሥነ-ምዕላድና ሥነ-አገባብ በአግባቡ በመጠቀም በኩል ጎላ ያለ ችግር እንደሚታይባቸው ይጠቁማል፡፡

በሰንጠረዥ 4.1. እንደሚያመለክተው የናሙናው ታላሚዎች ሦስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ በተለያዩ የስኬት ብልሃቶች ዓይነቶች ተጠቅመዋል፡፡ መረጃው ተማሪዎቹ 8.17% የአፍ-መፍቻ ቋንቋ-ተኮር ብልሃቶችን፣ 24.71% ሁለተኛ ቋንቋ ተኮር ብልሃቶችን፣ 0.39% ድጋፍ የመጠየቅ ብልሃትንና 4.78% የሰዉነት እንቅስቃሴ ብልሃቶችን እንደተጠቀሙ ይጠቁማል፡፡ ከእነዚህ ከአራቱ ማካካሻ ብልሃቶች መካከል ተጠኚዎቹ የተገለገሉት በአብዛኛው በሁለተኛ ቋንቋ-ተኮር ብልሃት ነው፡፡

በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተኮር ረገድም ተማሪዎቹ 3.08% በቃል በቃል ትርጉም፣ 1.41% በማስመሰል እና 3.68% በልሣናት ቅልቀላ ተግባቦታዊ ብልሃቶች ተጠቅመዋል፡፡ ተማሪዎቹ በአብዛኛው የተጠቀሙት በልሣናት ቅልቀላ ብልሀት ነው፡፡ በተጨማሪም ከየተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ-ተኮር ብልሃቶች አጠቃቀም በቅደም ተከተል ዳግም-ማዋቀር 8.2%፣ ሁለገብ ቃላትን መጠቀም 6.83% ግመታ 6.6% ገለጻ 1.73% እና ቃል-ፈጠራ 1.35% በድግግሞሽ መሆኑን በሰንጠረ 4.1. የቀረበው መረጃ ያመለክታል፡፡

ከእነዚህ ውሱን ሁለተኛ ቋንቋ ተኮር ብልሃቶች መካከል ተማሪዎቹ ይበልጡን የተጠቀሙት በዳግም ማዋቀር ብልሃት ነው፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ንግግርን በማፍለቅ ሂደት ችግር ሲያጋጥማቸው ሃሳባቸውን በተለየ መንገድ ለመግለጽ የሚያደርጉትን ጥረት ይጠቁማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ተግባር አንድን ሲያከናውኑ 13.97% ፣ተግባር ሁለትን ሲያከናውኑ 12.92% ፣ተግባር ሶስትን ሲያከናውኑ 11.15% የማካካሻ ብልሃቶችን ተጠቅመዋል፡፡ ይህ መረጃ እንደሚያመለክተው ተማሪዎቹ በርካታ የስኬት ብልሃቶችን የተጠቀሙት ተግባር አንድን በማከናወን ነው፡፡ በዚህ ተግባር ተማሪዎቹ በርካታ የስኬት ብልሃቶችን የተጠቀሙበት ምክንያት ከሌሎቹ ተግባራት የበለጠ ጊዜ ወስደው እንዲናገሩ እድል ስለሰጣቸው ሊሆን ይችላል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች የተጠቀሙበት ሦስተኛው ዋና የብልሃት ዓይነት የማዘናጊያ ብልሃት የተሰኘውን ነው፡፡ በዚህ ዋና የተግባቦታዊ ብልሃት ዓይነት ሥር ተማሪዎቹ የተጠቀሙት፣ ማሚያዎች ተብለው በሚታወቁት ተግባቦታዊ ብልሃቶች ነው፡፡ በሰንጠረዥ 4.1. የናሙናው ታላሚዎች ተግባር አንድን ሲያከናውኑ 16.34% ፣ ተግባር ሁለትን ሲያከናውኑ 8.88%፣ ተግባር ሶስትን ሲያከናውኑ ደግሞ 2.76%፣ በአጠቃላይ ሦስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ 27.98% ማሚያዎችን እንደተጠቀሙ ይጠቁማል፡፡

በሰንጠረዥ 4.1. እንደሚያመለክተው የናሙናው ታላሚዎች በርካታ (43.78%) የብልሃት ዓይነቶችን በድግግሞሽ የተጠቀሙት ተግባር አንድን ሲያከናውኑ ሲሆን በተከታታይ ተግባር ሁለትን ሲያከናውኑ 29.58% ፣ተግባር ሶስትን ሲያከናውኑ ደግሞ 26.63% ተግባቦታዊ ብልሃቶችን በድግግሞሽ ተጠቅመዋል፡፡

በተጨማሪም በሦስቱ ተግባራት መካከል የተግባቦታዊ ብልሃቶችን አጠቃቀም በሚመለከት ያለው ልዩነት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የአንድዮሽ ወገን ልዩነት ትንተና (one-way ANOVA) ስሌት ተሰርቷል፡፡ በዚህ ስሌት አማካኝነት የተገኘው ውጤት በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

## ሠንጠረዥ4. 2 በተግባራት መካከል ጉልህ የአጠቃቀም ልዩነት የታየባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች

| ተ.ቁ | የተግባቦታዊ ብልሃቶች ዓይነቶች | የ F ዋጋ (Fcal) |
|---|---|---|
| 1 | ትርጉምን መተካት | 5.7 |
| 2 | የቃል በቃል ትርጉም | 57.78 |
| 3 | ማስመሰል | 6.82 |
| 4 | ገለጻ | 5.42 |
| 5 | ሁለገብ ቃላትን መጠቀም | 9.91 |
| 6 | ቃል-ፈጠራ | 5.47 |
| 7 | ማሚያዎች | 24.08 |

ሠንጠረዥ 4.2. እንደሚያመለክተው ከተራ ቁጥር 1-7 የተዘረዘሩት ተግባቦታዊ ብልሃቶች የ F ዋጋዎች (Fcal) በ $\alpha=0.05$ የጉልህነት ደረጃ በ Fሥርጭት ሠንጠረዥ

(F distribution table) ውስጥ ከተሰጠው የ F ዋጋ ማለትም $F_{(2.6)}$ =5.14 ስለሚበልጡ በሦስቱ ተግባራት መካከል የተጠቀሱትን ብልሃቶች አጠቃቀም በሚመለከት ያለው ልዩነት ጉልህ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

### 4.1.2. ተማሪዎቹ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች በቋንቋው ያላቸውን ችሎታ ለማሻሻል የሚረዱ ናቸው?

ሁለተኛ ደረጃ ይህ ምርምር ለመመለስ የሚሞክረው ጥያቄ የሸክኛ አፍ ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች ተማሪዎች በቋንቋው ያላቸውን ችሎታ ለማሻሻል የሚረዱ ናቸው?" የሚል ነው

በርግጥ ሁሉም ተግባቦታዊ ብልሃቶች በተግባቦት ወቅት የሚያጋጥሙ የቋንቋ ችግሮችን ለመፍታት ተግባራዊ ከሚሆኑበት ተግባቦታዊ አውድ አኳያ የበኩላቸውን አስታዋፅኦ ቢኖራቸውም የቋንቋ ተማሪውን ተግባቦታዊ ችሎታ ለማጎልበት ካላቸው አቅም አንጻር ግን ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት የናሙናውን ታላሚዎች የተግባቦታዊ ብልሀቶች አጠቃቀም ሰንጠረዥ 4.1ን መሰረት በማድረግ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

ተማሪዎቹ ሦስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ 38 .05% የማካካሻ ብልሀቶችን፣ 33.97% የማስወገድ ብልሃቶችንና 27.98% የማዘናጊያ ብልሃቶችን ተጠቅመዋል፡፡ በዚህም መረጃ መሰረት ተማሪዎቹ ሶስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ በአብዛኛው ማካካሻ ብልሃቶች መጠቀማቸው ተማሪዎቹ የተግባቦታዊ ብልሃቶች አጠቃጠም በጥቂቱም ቢሆን የሚያበረታታ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች ከተጠቀሙባቸው የማስወገድ ብልሃቶች መካከል 79.05% የሚሆኑት መደበኛ ቅነሳዎች ናቸው:: በሌሎቹ የማስወገድ ብልሃቶች (ማለትም መልዕክትን መተካት መልዕክትን መተው እና ርዕስን ማስወገድ በሚባሉት ብልሃቶች) ተማሪዎቹ የተጠቀሙት 20.95% ብቻ ነው፡፡ በመደበኛ ቅነሳ ብልሃት መጠቀም ተማሪውን ከመግባባት የሚያግደው ባለመሆኑ በተግባቦት ሂደት የሚያሳድረው ተጽዕኖ እምብዛም ነው፡፡የተቀሩት ሦስቱ የማስወገድ ብልሃቶች ግን መልዕክቱን የማዛባት የማደብዘዝ የመለወጥ የመቀነስና የመተው ባህርይ ስላላቸው በተግባቦት ወቅት ተገቢ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ስለሆነም ሰንጠረዥ 4.1 እደሚጠቁመው ተማሪዎቹ ከሌሎቹ የማስወገድ ብልሃቶች ይልቅ በመደበኛ ቅነሳ ይበልጥ መጠቀማቸው በቋንቋው ያላቸውን ተግባቦታዊ ችሎታ ለማዳበር ጠቀሜታ ይኖረዋል ፡፡

ይሁን እንጅ ተማሪዎቹ ሦስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ (33.97%) የማስወገድ ብልሃቶችን መጠቀማቸው በቋንቋው በአግባቡ የመጠቀም ችግር እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከተተረገው ምልከታና ከተማሪዎቹ መምህራንም ጋራ ከተደረገው ቃል-መጠይቅ በርካታ ተማሪዎች በማስወገድ ብልሃቶች በተደጋጋሚ እንደሚጠቀሙ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በክፍል ምልከታ ወቅት ከተመዘገቡት ተግባቦታዊ ብልሃቶች መካከል አብዛኛዎቹ ማለትም (44.4 %) የሚሆኑት በእነዚህ ብልሃቶች ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ እንዲሁም ከመምህራን ጋራ በተደረገ ቃል-መጠይቅ በርካታ ተማሪዎች ፡-

- ✓ ሀሳባቸውን በቋንቋው አብራርተው መግለጽ እንደማይችሉ
- ✓ እሳሳታለሁ በሚል ፍራቻ የተነሳ በመማረያ ክፍል ውስጥ በጓደኞቻቸው ፊት የሚያውቁትን ነገር እንኳን ለመናገር ፍቃደኛ እንደማይሆኑ
- ✓ የተቆራረጠ ንግግር እንደሚናገሩ
- ✓ መናገር ጀምረው መሀል ላይ እንደሚያቋርጡ መረዳት ተችሏል ፡፡

በተጨማሪም የናሙናው ታላሚዎች ሦስቱን ተግባራት ሲያከናኑኑ በአጠቃላይ ከተጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች መካከል (26.86%) መደበኛ ቅነሳዎች መሆናቸው ከንግግር ቅልጥፍና (fluency) አንፃር ብዙም ተጽዕኖ ባይኖረባቸውም ከትክክለኛነት (accurancy ) እና ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ አንጻር ጎላ ያለ ችግር ይፈጠራሉ፡፡ መደበኛ ቅነሳ በክፍል ምልከታ ወቅት ከተመዘገቡት ብልሀቶች መካከል በድግግሞሽ መጠን (34.8) ቀዳሚ ነው፡፡ በተጨማሪም ከናሙናው ታላሚዎች መምህራንም ጋር በተደረገ ቃል -መጠይቅ በመበደኛ ቅነሳ ብልሃቶች ውስጥ የሚካተቱ በርካታ የቋንቋ አጠቃቀሞች

- ✓ የጾታ አመልካች ቅጥያዎች በአግባቡ ያለ መጠቀም
- ✓ የአንቱታ አገላለጽ ችግር
- ✓ በአንድ ዓረፍተ-ነገር ውስጥ የሚገኙትን ሐረጎች ያለማመጣጠን
- ✓ ሆሄያትን መግደፍ
- ✓ የድምጽ አወጣጥ ችግር
- ✓ የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላትን መለየት አለመቻል
- ✓ የቀጥተኛ ተሳቢ አመልካች ቅጥያ የሆነውን /-ን/ በአብዛኛው በማያስፈልግበት ቦታ የመጠቀምና በሚያስፈልግበት ቦታ ደግሞ የማስወገድ የመሳሰሉትን ችግሮች በተማሪዎቹ ላይ እንደሚታዩ መረዳት ተችሏል ፡፡

ተማሪዎቹ የማካካሻ ብልሀቶችን አጠቃቀም ስንመለከት ከአፍ- መፍቻ ቋንቋ- ተኮር ብልሃቶች ይልቅ በአብዛኛው የተጠቀሙት በሁለተኛ ቋንቋ-ተኮር ብልሃቶች ነው፡፡ ሰንጠረዥ 4.1. እንደሚያመለክተው ተተኳሪዎቹ ሦስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ ከተጠቀሙባቸው ብልሀቶች መካከል 8.17% የአፍ መፍቻ ቋንቋ-ተኮር ሲሆኑ 22.38% ደግሞ ሁለተኛ ቋንቋ ተኮር የማካካሻ ብልሃቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ ከተመዘገቡት ተግባቦታዊ ብልሃቶች መካከል 8.4% የሚሆኑት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተኮር ብልሃቶች ሲሆኑ 39.6% የሚሆኑት ደግሞ ሁለተኛ ቋንቋ ተኮር ብልሃቶች ናቸው፡፡ ሁለቱም የመረጃ ምንጮች ተማሪዎቹ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተኮር ብልሀቶች ይበልጥ በሁለተኛ ቋንቋ-ተኮር ብልሃቶች እንደሚጠቀሙ ያረጋግጣል፡፡

ሠንጠረዥ4.1. እንደሚያመለክተው የናሙናው ታላሚዎች ሶስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ ከተጠቀሙባቸው የስኬት ብልሃቶች አይነቶች መካከል በአብዛኛው የተጠቀሙት ዳግም ማዋቀር (8.2%)፣ ሁለገብ ቃላትን መጠቀም (6.83%)፣ ግመታ (6.6%) እና የሰውነት እንቅስቃሴ (4.78%) በሚሰኙት ውሱን የተግባቦታዊ ብልሃቶች አይነቶችን ነው፡፡ ሆኖም እጅግ ጠቃሚ ናቸው ከሚባሉት የማካካሻ ብልሃቶች መካከል ዋነኛው ገለፃ ነው፡፡ ነገር ግን ተማሪዎቹ ሶስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ የተጠቀሙት (1.73%) በድግግሞሽ መሆኑን ያመለክታል፡፡

## 4.2. የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ

በምዕራፍ አንድ ላይ እንደ ተገለጸው ይህ ጥናት የተካሄደው ሁለቱን የምርምር ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ነው፡፡ስለሆነም በተደረገው ጥናት ሁለቱም ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል፤የተገኘውም ከቃለ መጠየቅ፣ከስዕል ገለጻ፣ ከትርጎማ በተጨማሪ ከምልከታና ከፈተና የተገኙ የመረጃ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡በተገኘው የመረጃ ውጤት ትንተና መሰረት የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ቁልፍ ጥያቄዎች ጥናቱ ሊመልሳቸው የሚገባቸው የምርምር ጥያቄዎች ሲሆኑ ጥያቄዎቹም የሸክኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት በአማርኛ ሲናገሩ የቋንቋ ችግር ሲያጋጥማቸዉ የሚጠቀሙባቸዉ ተግባቦታዊ ብልሀቶች የትኞቹ ናቸዉ? እና የናሙና ታላሚዎች የሚጠቀሙባቸዉ ተግባቦታዊ ብልሀቶች በቋንቋዉ ያላቸዉን ችሎታ እንዲያሻሽሉ የሚረዱ ናቸዉ? የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ

ለማግኘትም ተግባር ተኮር ዘዴ መሰረት ያደረገ መረጃን የመሰብሰብ ሥራ ተከናውኗል፤እንዲሁም የክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለመከታተል የምልከታ መከታተያ ቅጽ እና ለመምህራን ቃለ መጠየቅ ጥያቄዎች ተዘጋጅቷል ስለሆነም በቃለ መጠይቅ፣ በስዕል ገለጻ፣ በትርጎማ እና በክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ትንተናው ተከናውነኗል፡፡የጥናቱም ግኝትም በሸክኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶችን በተመለከተ የተለያዩ የጥናት ውጤት መገኘታቸውን አመልክቷል፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ የሸክኛ አፍ ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸውን ተግባቦታዊ ብልሃቶች የትኞቹ ናቸው የሚል ነው? ተማሪዎቹ የተጠቀሙባቸውን ተግባቦታዊ ብልሃቶች እንደሚከተለው ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የሸክኛ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማረኛ ሲናገሩ የሚያጋጥሟቸውን የቋንቋ ችግሮች ለመፍታት የማስወገድ፣ የማካካሻ፣ የማዘናጊያ ብልሃቶችን እና በእነዚህ ዋና ዋና ብልሃቶች ሥር የሚካተቱትን መደበኛ ቅነሣ፣ መልዕክቱን መተው፣ ርዕስን ማስወገድ፣ የቃል በቃል ትርጉም፣ ማስመሰል፣ ልሣናት ቅልቀላ፣ ገለፃ፣ ፈጠራ፣ ዳግም ማዋቀር፣ እርዳታ መጠየቅ፣ የሰውነት እንቅስቃሴና ማሚያዎች የሚሰኙትን ውሱን ተግባቦታዊ ብልሃቶች እንደሚጠቀሙ የዚህ ጥናት ግኝቶች ይጠቁማሉ፡፡

ይህ ጥናት አብዛኞቹ የሸክኛ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከሌሎቹ ዋና ዋና ተግባቦታዊ ብልሃቶች ይበልጥ በተደጋጋሚ የሚጠቀሙት በማካካሻ ብልሃቶች እንደሆነና ከአፍ-መፍቻ ቋንቋ-ተኮር ብልሃቶች ይልቅ በሁለተኛ ቋንቋ ተኮር ብልሃቶች እንደሚጠቀሙ ያመለክታል ፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚጠቁመው ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች ዓይነቶችና ብዛት አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቹ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ባህርያት ይወስናሉ፡፡ ይህ ግኝት የተግባሩ ዓይነት በብልሃት ምርጫ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ አለው ከሚለው ከ (Poulisse, 1989 በ ሰፉ 1995 እንደተጠቀሰው) ግኝት ጋሪ ይጣጣማል፡፡በዚህ ጥናት መሰረት ይህን ዓብይ ግኝት የሚያጠናክሩ የሚከተሉት ንውሳን ግኝቶች ይጠቀሳሉ፡፡

ተማሪዎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ የሚጋበዙ ተግባራት ተማሪዎቹ በርካታ የተግባቦታዊ ብልሃቶች ዓይነቶችን በተደጋጋሚ እንዲጠቅሙ እድል ይሰጣሉ ፡፡

ትርጎማ ከለሎች ተግባራት ይበልጥ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተኮር ብልሃቶች እንዲጠቅሙ ይገፋፋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቃለ መጠይቅ የስዕል ገለፃ ተማሪዎች በይበልጥ ሁለተኛ ቋንቋ- ተኮር ብልሃቶች ዕድል ይሰጣል፡፡

ተማሪዎቹ በርካታ የማዘናጊያ ብልሃቶችን የሚጠቀሙት ሃሳብን በስፋት ለማፍለቅ በሚረዱ ተግባራት ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ተግባራት በተደጋጋሚ ጊዜ ወስዶ ማሰብን ይጠይቃል፡፡

ሁለተኛ የዚህ ጥናት የምርምር ጥያቄ የናሙና ታላሚዎች የሚጠቀሙባቸዉ ተግባቦታዊ ብልሀቶች በቋንቋዉ ያላቸዉን ችሎታ እንዲያሻሻሉ የሚረዱ ናቸዉ? የሚሉ ጥያቄ ነው፡፡የጥናቱ ግኝት የሸክኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በቋንቋው ያላቸውን ችሎታ ለማሻሻል በሚያግዙ ተግባቦታዊ ብልሃቶች እንደሚጠቀሙ ያሳያል፡፡ ነገር ግን በርካታ ተማሪዎች እምብዛም በቋንቋ ያላቸውን ችሎታ ለማሻሻል በማይረዱ የማስወገድ ብልሃቶች (በተለይ መልዕክትን መተካት መልዕክት፣ መተውና ርዕስን ማስወገድ) በተደጋጋሚ እንደሚጠቀሙ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ እጅግ ጠቃሚ ናቸው ከሚባሉት ተግባቦታዊ ብልሃቶች መካከል አንዱ በሆነው የገለፃ ብልሃት የአብዛኛዎቹን ውስን ተግባቦታዊ ብልሃቶች ተማሪዎቹ እምብዛም በተደጋጋሚ እንከ2ደማይጠቀሙበት ያመለክታሉ፡፡

የማስወገድ ብልሃቶች የተማሪውን የቋንቋ ችሎታ ለማሻሻልም ሆነ ቋንቋውን በመጠቀም የሚፈለገውን መልእክት ለማስተላለፍ እምዛም አስተዋጾ ስለሌላቸው የተማሪዎቹን የማስወገድ ብልሀቶች አጠቃቀም ለመቀነስ ጥረቶች መደረግ እንዳለባቸዉ ይህ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ (ሰፋ 1995, Dornyei 1995) ይህ ብልሃት በአብዛኛው እጅግ ጠቃሚ የማካካሻ ብልሃት ተደርጎ ስለሚወሰድ በአሁኑ ወቅት የሚካሄዱ አብዛኛዎቹ የተግባቦታዊ ብልሃቶች ስልጠናዎች በዚህ ብልሃት ላይ ያተኩራሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት የሸክኛ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በተግባቦታዊ ብልሃቶች የሚጠቀሙት በተግባቦት ወቅት የሚያጋጥሟቸው የወድያውነት ባህርይ ያለባቸውን ችግሮች ለመፍታት ብለው እንጂ ችግር-ፈቺ ዘዴዎች መሆናቸውን አውቀው እንዳልሆነ ይጠቁማሉ፡፡በዚህ የተነሳም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በተግባቦታዊ ብልሃቶች ሲጠቀሙ

ስህተት የሚሰሩ መሰሏቸው ብዙን ጊዜ ይሸማቀቃሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ጠቃሚ ተግባቦታዊ ብልሀቶችም ስርዓታዊ በሆነ መንገድ የመጠቀም ልምድ የላቸውም፡፡

# ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ የጥናቱን መደምደምያና አስተያየት ማቅረብ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ከአከናወኗቸው ሶስት ተግባራትና ከሌሎችም ደጋፊ ምንጮች የተሰበሰቡት መረጃዎች በጥናቱ ቁልፍ ጥያቄዎች መሰረት ከተተነተኑ በኃላ የተገኙትን ውጤቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት መደምደምያና አስተያየት ተሰቷዋል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሸክኛ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የተጠቀሙበትን ተግባቦታዊ ብልሃቶችን በመተንተን መግለፅ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ሁለት ጥያቄዎችን ቀደም ብሎ አንስቷል፡፡ጥያቄዎቹን ለመመለስ ተተኳሪዎቹ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ተደረጎ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ ስለዚህ የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን መደምደምያ ተሰጥቷል፡፡

በትንተናው ግኝት ማብራሪያ እንደታየው ተማሪዎቹ ሶስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ በርካታ የተግባቦታዊ ብልሀት ዓይነቶችን ማለትም የማስወገድ የማካካሻና የማዘናጊያ ብልሃቶች በሚሰኙት ዋና ዋና ብልሃቶችን ተጠቅመዋል፡፡ እንዲሁም ደግሞ መደበኛ ቅነሳ፣ መልዕክትን መተካት፣ መልዕክትን መተው ፣ርዕስን ማሰወገድ፣ የቃል በቃል ትርጉም፣ ማስመሰል፣ ልሣናት ቅልቀላ፣ ገለጻ፣ ግመታ ፣ሁለገብ ቃላትን መጠቀም፣ ቃል ፈጠራ፣ ዳግም ማዋቀር፣ ድጋፍ መጠየቅ፣ የሰውነት እንቅስቃሴና ማሚያዎች በሚባሉት ዉሱን ብልሃቶችን መጠቀማቸውንና በተጨማሪም በክፍል ምልከታ ወቅት ከተገኙት መረጃዎች መረዳት በመቻሉ፣ ይህ ጥናት በተለይም የሸክኛ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ምናልባት በአጠቃላይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ በተለያዩ የተግባቦታዊ ብልሃት ዓይነቶች እንደሚጠቁሙ በዚህ ጥናት ተረጋግጧል፡፡

ከላይ እንደቀረበው ተማሪዎቹ ሶስት ዋና ዋና ተግባቦታዊ ብልሃቶችንና አስራ አምስት ውስን ተግባቦታዊ ብልሃቶችን ሶስቱን ተግባራት ሲያከናውኑ በድግግሞሽ ተጠቅመዋል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ተጠኚዎቹ የተጠቀሙባቸው ብልሃቶች በታላሚው ቋንቋ ያላቸውን ችሎታ እንዲያሻሽሉ የሚረዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

በትንተናው እንደታየው በርካታ ተማሪዎች እብዛም በቋንቋው ያላቸውን ችሎታ ለማሻሻል በማይረዱ ብልሃቶች ተጠቅመዋል፡፡

ተማሪዎቹ ከተጠቀሙባቸው ብልሃቶች ውስጥ በማስወገድ ብልሃት በተለይም መልዕክትን መተካት፣መልዕክትን መተውና ርዕስን ማስወገድ በሚባሉት ብልሃቶች በተደጋጋሚ ተጠቅመዋል፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎቹ ሦስቱን ተግባራት ሲያከናዉኑ በርካታ ማሚያዎችን መጠቀማቸው በዕለታዊ ኑሯቸውም ውስጥ በቋንቋው ሲገለገሉ በማሚያዎች እንደሚጠቀሙ ያሳያል:: ስለዚህ በማሚያዎች የመጠቀም ልምድ ማዳበራቸው፣ በቋንቋው በመጠቀም ሃሳባቸውን ለመግለፅ ለሚያደርጉት ጥረት እገዛ ይኖረዋል:: ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት እንደታየው ማሚያዎች ሲደጋገሙ ንግግሩን አሰልቺ የሚያደርግ ባህርይ ስላላቸው ተማሪዎቹ ማሚያዎችን (እንደ ማዘናጊያ ብልሃቶች) አጠቃቀም ግንዛቤ ማስጨበጥ እንደሚያስፈልግ ይገልፃል፡፡

## 5.2 አስተያየት

የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በተለይም በሸክኛ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚገለገሉባቸዉን ተግባቦታዊ ብልሃቶች አጠቃቀም ለማሻሻል ይረዱ ዘንድ ለሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

- **ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን**

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተግባቦታዊ ብልሃቶች ለተግባቦታዊ ቋንቋውን ማስተማር ዘዴ ያላቸውን ጠቃሚ ሚና ከግምት ወስጥ በማስገባት ስለብልሃቶቹ አጠቃቀም ያላቸውን እውቀት በማስፋት፣ ተማሪዎቻቸው የተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራትን ሲያከናዉኑ እንዲጠቀሙባቸው ለማስቻል ለተማሪዎቻቸው ስለተግባቦታዊ ብልሃቶች አጠቃቀም ግንዛቤ ማስጨበጥና በተግባርም እንዲጠቀሙባቸው ማበረታት ይጠበቅባቸዋል፡፡

እንዲሁም ቋንቋዉ ካለዉ ሰፊ ጠቀሜታ አኳያ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ከመማሪያ ክፍል ውጭ በአማርኛ እንዲናገሩ መበረታታት አለባቸው፡፡ በመሆኑም መምህራን በተለይ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአማርኛ ሲናገሩ ጓደኞቻቸው እንዳይስቁባቸው የመማሪያ ክፍሉን ሁኔታ በመቆጣጠር ተማሪዎቹ

ያላቸውን ውሱን የቋንቋ እውቀት በመጠቀም እንዲናገሩ እድል መስጠትና ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስህተቶች ካሉም የተማሪዎቹን ስሜት (ሞራል) በማይጎዳ መንገድ በጥንቃቄ ተማሪዎቹ እንዲያርሙ መሞከር አለባቸዉ፡፡

➢ **ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት**

የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት እጩ መምህራን ስልጠና ወቅት በቋንቋው ያላቸውን ችሎታ እንዲያዳብሩ ከሚረዷቸው የትምህርት ይዘቶች ጎን ለጎን ተማሪዎቻቸው በተግባቦት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን የቋንቋ ችግሮች ለመፍታት ስለሚያስችሏቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች እውቀት እንዲኖራቸውና ስለ ብልሃቶቹ ትምህርት አሰጣጥ ተማሪ-ተኮር ለማድረግ ካላቸው ጠቀሜታ አኳያ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ትኩረት እንዲሰጧቸው ግንዛቤ ማስጨበጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

➢ **ለመማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች**

ተግባቦታዊ ብልሃቶች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪውን ችግሮች ለመቅረፍ ከሚረዱ ችግር-ፈቺ ዘዴዎች መካከል አንዱ በመሆናቸው ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት ቋንቋውን እንዲማሩ እገዛ ያደርጋል፡፡ ይህን ሃሳብ መሰረት በማድረግ የስርዓተ-ትምህርት ባለሙያዎች በማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ወቅት የተማሪዎቹን ተግባቦታዊ ችሎታ ለማሻሻል ለሚረዱ ጠቃሚ ተግባቦታዊ ብልሃቶች (ምሳሌ፡ ገለፃ፡ ግመታ፡ ዳግም  ማዋቀር የሰውነት እንቅስቃሴ ማሚያዎች) በትምህርት ይዘቶች መረጣ  ወቅት ትኩረት ቢሰጡ ተማሪዎች በእነዚህ ብልሃቶች ለመለማመድ የተሻለ እድል ሊያገኙ ስለሚችሉ ለቋንቋው ትምህርት ስኬት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

➢ **ለጥናት አድራጊዎች**

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሰፊ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች ይህ ጥናት እንደመነሻ በመሆን የራሱን ድርሻ በመወጣት ያገለግላል፡፡

# ዋቢ ፅሑፎች


ሰፋ መካ፡፡ (1995)፡፡ *የጉመር ጉራግኛ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች ትንተና*፣ (ያልታተመ)፡፡ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፡፡ አዲስ አበባ የኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ *በስነ-ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር*፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ተክሌ ሻሊጊቶ፡፡ (1987)፡፡ *ሸኪቾና ታሪኳ*፡፡አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት፡፡

ንጋቱ አሰፋ፡፡ (2000)፡፡ *በሲዳምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሀቶች ምርመራ፣ (ያልታተመ)፡፡ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትሰምህርት ቤት፡፡

አላዩ ደሳልኝ፡፡(2014)፡፡ *በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች አተገባበር ግምገማ ፤(ያልታተመ)፡፡* ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፡፡ ባህር ዳር የኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡

ከተማሽ የወጉ፡፡(2013*)፡፡ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ፣(ያልታተመ)፡፡*ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፡፡ ባህር ዳር የኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡

ዘርሁን ጌትነት፡፡(2010)፡፡ *የከፊኛ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች ትንተና*፣ (ያልታተመ)፡፡ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፡፡ ደብረ ብርሃን የኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የተወካዮች ምክር ቤት፡፡ (ነሃሴ 15 ፤1986)፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አዋጅ፡፡ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፡፡ ቁጥር 1፤አንቀፅ 5፤3፡፡

Anderson, A. and Lynch T. (1991). *Listening*. Oxford:Oxford university press.

Bachman,L.(1990).*Fundamental considerationsin language testing*.Oxford:OUP.

Bongaerts, T. and Poulisse,N.(1998). *Communication Strategies in L1 and L2 Same or Different? Applied Linguistics*.10/3:253-268.

Bremner, (1999). *Language Learning Strategies and Languag proficiency: Investigating Relationship* inHong Kong. The Canadian Modern Language Review.55/3:490-514.

Brown, G. et al (1984).*Teaching talk: Strategies for production and assessment*. Cambride: university press.and Yule,G. (1983).*Teaching the Spoken Language*. Cambridge Cambridge university press.

Brown, H. (1994). *Principles of language learning and teaching*. Englewood Cliffs: Prentice Hall Regents.

Byrne, D.(1986). *Teaching Oral English*. London: Longman.

Canale, M. (1983). *From Communicative Competence to Communicative Language Pedagogy*.in J.Richards and R. Schmidt (eds). Language and Communication London:Longman.

Cook,V.(1993).*Linguistic and second language acquistion*. London: MacMillan.

Corder, P.(1983).Strategies of Communication. In C.Faerch and G. Kasper (eds).Strategie interlanguage Communication. England :Longman.

Dornyei, Z. (1995).“ On the Teachability of Communication Strategies.” tesolquarterly. 29/1:55-85.and K0rmos, J.(1998). Problem-solving Mechanisms in L2 Communication psycholinguistic Perspective.SSLA. 20:349-385.

Dryanan, L.(2011). *Communication clash*.New york, NY.

Ellis R. (1985). *Understanding Second Language*. Acquisition.Oxford :Oxford university Press.(1984).*The study of Second Language Acquisition*. Oxford: Oxford University Press.

Faerch, C. and Kasper, G. (1980).“ Processes and Strategies in Foreign Language learning and Communication.” Interanguage Studies Bulletin5:47-118.and Kasper, G. (1983). *“On Identifying Communication Stratyegies in Interlanguage production,*” In C. Faerch and G. Kasper (eds.) Strategeiesin Interlanguage Communication. England: Longman. and Kasper, G.(1986). *“Cognitive Dimensions of Language Transfer*”.in

E. Kellerman and M. Sharwood Smith (eds.). Crosslinguistic influence in Second Language Acquisition. New York: Pergamon.

Fasil Demissie (1992).Communication strategies Employed by senior High

school student in oralproduction of English (M.A Thesis,unpublished) Addis Ababa: Addis Ababa university.

Griggin, E. (2009). A first look at communication theory launching your study of communicationtheory. New York,

Halliday, M. (19989). *Spoken and Written Language*. Oxford:Oxford university Press.

Hughes, A.(1989). *Testing for Language Teachers*. Cambridge: Cambridge university press.

Krashen, S. (1985).The Input Hypothesis Issues and Implications. New York:Longman.

Larsen-Freeman, D. and Long, M. (1991). An Introduction to Second Language Acquisition Research.London: longman.

Lier,L.(1988).*The Classroom and the Language Learner*. London: Longman.

Littlemor,J .(2001). An Empirical Study of the Relationshp Berween Cognitive Style and use of Communication Strategies.Applied Linguistics. 22/2 241-265.

Littlewood, W. (1984). *Foreign and Second Language Learning*.Cambride: Cambride university Press.

Mackey, W. (1965).*Language Teaching Analysis*. London: Longman.

Madsen, H. (1983). *Techniques in Testing*. Oxford: Oxford university press.

Nunan, D. (1989). *Designing Tasks for the communicative Classroom*. Cambride:Cambrideuniversity press.

Richards, J. (1985). *The Context of language Teaching*. Cambride: Cambride university Press.

Rivers, W.(1998).*Communicating naturally in second Language*. Cambride: CUP.

Tarone, E. (1977).Conscious Communication Strategies in I nterlanguage: A.Progress Report TESOL.77:149-203.(1980). Communication Strategies, Foreigner Talk and Repair in Interlanguage. Languag Learning. 30:417-431. and Yule, G. (1989). *Focus on the Language Learner*. Oxford: oxford university press.

Tudor. I. (1996). *Learner centedness as Language Education*. Cambridge: Cambridge university press.

Yule, G. (1996). *The Study of Language*. Cambride: Cambride university press.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡- የንግግር ፈተና

### ጅማ ዩኒቨርሲቲ

### ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

### የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ክፍል

### የድህረ ምረቃ ፕሮግራም

"በሸክኛ አፍ ፊት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች ትንተና" በሚል ርዕስ ለሚደረገው ጥናት አጋዥነት የተዘጋጀ የንግግር ፈተና

**የትምህርት ቤቱ ስም፡-** ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**የተማሪው(ዋ) ስም፡**-----------------------------------------------------

**ሴክሽን**---------------------------------------------------------

**የክፍል ቁጥር**---------------------------------------------------

ውድ ተማሪ የምርምሩን ጠቀሜታ በመረዳት ፈተናውን በጥንቃቄ ለመስራት ለምታደርገው(ለሚታደርጊው)ቀና ትብብር በቅድሚያ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

**አጠቃላይ መመሪያ**

ይህ ፈተና ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ በእነዚህ ሁለት ክፍሎች የቀረቡትን ተግባሮች እያንዳንዳቸው በተሰጠው መመሪያ መሠረት ከፈታኝህ(ሽ) ጋር በመሆን እንድታከናውን(ኚ) ሃያ ደቂቃ ተሰጥቶሃል(ሽ)፡፡ በተጨማሪም ፈተናውን መስራት ከመጀመሪህ(ሽ) በፊት በፈተናው ውስጥ ስለቀረቡት ተግባሮች በቂ ግንዛቤ ይኖርህ(ሽ) ዘንድ የፈተናውን ወረቀት በጥሞና እንድታነበው(ቢው) 10 ደቂቃ ተሰጥቶሻል(ሃል)፡፡

## ክፍል አንድ

*መመሪያ*

በዚህ ክፍል የምታከናውነው(ኚው) ተግባር ቃለ መጠየቅ ነው፡፡ ቃለ መጠይቁ የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ችሎታህ (ሽን) ለመለካትየሚያገለግል ነው፡፡ በመሆኑ በተረጋጋ መንፈስ እንደሚታከናውን(ኚው)ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም እባክህ(ሽ) በቅድሚያ ጥያቄዎቹን አንብባቸው(አንብቢያቸው)፡፡

ከዚህ በኋላ ፈታኝ(ሽ) በሚጠይቁህ(ሽ) መሰረት ጥያቀዎችን በቃል አብራርተህ(ሽ) መልስ(ሽ)

**ጥያቄዎች**

1. እንደምን አለህ(ሽ)?

-----------------------------------------------------------------

------------------------------------------

2.ቤተሰቦችሽ(ሀ) ማለትም(አባት(ሽ)፣እናትህ(ሽ)፣ወንድምህ(ሽ)፣እህትህ(ሽ) ወዘተ የት ነው የሚኖሩት በመካከላችሁ ስላለው ቤተሰባዊ ግንኑት ስለ ኑሮአቸው ሁኔታና ስለመሳሰሉት አንዳንድ ነገሮችን ብታ ጫውተን(ችን)?

--------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------

3. በጉጉት የሚትጠብቂው(ቀው) በዓል (አረፋ፣መስቀል፣ፋሲካ፣ኢድ አልፈጥር ወዘተ የትኛው ነው ለምን ይህን በዓል በአለፈው አመት እንደት እንዳከበርከው(ሽው) አብራርተህ(ሽ) ግለጽልኝ፡፡

---------------------------------------------------------------------------------------

4. ከምትማራቸው(ከሚትማሪያቸው) የትምህርት ዓይነቶች አንዱ አማርኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ አማርኛን መማርህ(ሽ) ለምን የሚጠቅምህ(ሽ) ይመስልሻል?

------------------------------------------------------------------------------------------

5. ከትምህርት ቤት ውጭ በአማርኛ ትናገራለህ (ሽ) የት? በምን አጋጣምዎች?

------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------

6.የአማርኛ ቋንቋ ችሎታህ(ሽ) ለማሻሻል የምታደርጋቸውን(ውን) ትረቶች ብትገልጽልኝ?

-----------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------

7. ስለ አማርኛ ቋንቋ ችሎታህ(ሽ) ምን አስታየት አለህ(ሽ)?

------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------

# ክፍል ሁለት

በዚህ ክፍል የቀረበው ተግባር ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሰንጠረዥ የተሟላ መረጃ የያዘ አይደለም፡፡ መረጃ የጎደለባቸውን ቦታዎች ለማማልከት ሁለት የጥያቄ ምልክቶች(??) በክፍት ቦታዎች ላይ ተደርጓል፡፡

ስለሆነም በፈታኝህ(ሽ) እጅ የተሟላ መረጃ የያዘ ሰንጠረዥ የሚገኝ በመሆኑ ያልተሟላ መረጃዎችን ከእሳቸው በመጠየቅ ማሟለት ትችላለህ(ሽ) እባክህ(ሽ) በቅድሚያ ሰንጠረዡን በእርጋት አንብበውና(አንብቢውና) የጎደሉትን መረጃዎች ለይታቸው ከተረዳህ በኋላ ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ስድስት ጥያቄዎችን ፈታኝህ(ሽ)ን በመጠየቅ ሰኝጠረዡን አሟሉ

ለምሳሌ፡- ተፈታኝ፡- የክንፌ ገዛኸን እድሜ ስንት ነው?

ፈታኝ፡-የክንፌ ገዛኸን እድሜ 16 ነው፡፡

| ተ.ቁ | የተማሪው(ዋ) ስም | የእናት ስም | የተማረ በት ቦታ | ዕድሜ | ት/ት የጀመረች በት ዘመን | የክፍል ደረጃ | የሚወደው የት/ት ዓይነት | ት/ቱን የሚወድበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ክንፌ ገዛኸን | አደረት | አመሮ | ?? | 1994 | 11 | እንግሊዘኛ | ?? |
| 2. | ማቲየስ ተረፈ | አስካለ | ?? | 17 | 1996 | 9 | ?? | ሀኪም ለመሆን |
| 3. | አደን ተረፈ | ?? | ማሻ | 17 | ?? | 9 | ሲብክ | ዳኛ ለመሆን |
| 4. | ዳዊት ለማ | አለምቱ | ኩቢጦ | ?? | 1995 | 10 | ፊዚክስ | ?? |
| 5. | እሸቱ ወዳጆ | ?? | በሆ | 17 | 1994 | ?? | አማርኛ | መምህር ለመሆን |

## አባሪ ሁለት፡- የንግግር ፈተናውን ማረሚያ መስፈርቶች

### ክፍል አንድ

**መመሪያ ፡-**

የተከበሩ ፈታኝ በዚህ ክፍል የተማሪውን(ዋን) የንግግር ችሎታ ከአራት መስፈርቶች አንጻር ለመለካት ይሞከራል፡፡ እነዚህ መስፈርቶችንበት፣ሰዋሰዋዊ ትክክለኛነት፣የቃላት አጠቃቀም እና አንደበተ ርቱዕነት ናቸው፡፡ ስለሆነም በእነዚህ መስፈርቶች መካከል ያለዉን ልዩነት በሚገባ ካጤኑ በኃላ መስፈርቶቹ አኳያ የእያንድአንዱን ተማሪ ችሎታ ሦስት ነጥቦች ባሉት ስኬል ያመለከቱ፡፡ የነጥብ አሰጣጡም የሚከተለውን ደንብ የሚከተል ይሆናል ፡፡

ከፍተኛ = 3

መካከለኛ= 2

ዝቅተኛ = 1

በግምገማዎ ሂደት የተማረውን (ዋን) ትክክለኛ ችሎታ የሚገልጸውን መለያ ነጥብ በመክበብ ያመልክቱ፡፡

**ሀ.<u>ንበት</u>** (የድምጽ አወጣጥና ቅላጼ)

3. እንደ አፍ-መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪ ባይሆንም ፣ ግልጽ የሆነ የንበት ፣ የድምጽ አወጣጥ የቅላጼ ስህተት የማይታይበት ፡፡

2. የድምጽ አወጣጥ ፣ቅላጼውና የአነጋገር ሰልቱ በጥሞና ማድመጥን የምጠይቅ ቢሆንም ለመረዳት ብዙም አስቸጋር ያልሆነ፡፡

1.በንብት፣ በድምጽ አወጣጥና በቅላጼ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚታይበት፣ አንዳንድ ጊዜ በድጋሚ እንድናገር ካልተደረገ በሰተቀር ለመረዳት አሰቸጋሪ የሆነ፡፡

## ለ. <u>ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት</u>

3. ከሞላ -ጎደል ምንም ሰዋሰዋዊ ስህተት የማይሰራ ቢሆንም አልፎ አልፎ እጅግ ጥቂት በሆኑ ሰዋሰዋዊ ጉዳዮች ላይ ችግር የምታይበት ፡፡

2. አንዳንድ ሰዋሰዋዊ ስህተት የሚታይበት ፣ የቋንቋውን ዋና ዋና ስርዓቶች ቢያውቅም አልፎ አልፎ ሃሳቡን በተሟላ ሁኔታ አብራርቶለመግለጽ ሲሞክር የሰዋሰው ስህተት የሚታይበት ፡፡

1.ተደጋጋሚ ሰዋሰዋዊ ስህተት ፣ የተቆራረጠ ንግግርና ሰዋሰዋዊ ጉዳዮችን ማምታታት የምታይበት ፡፡

## ሐ. ለተፈለገው ግብ በበቂ ቃላት ስለመጠቀም፣

3. ባከናወነው ተግባር ውሰጥ አልፎ አልፎ በነገሮች ሰያሜ ምትክ እነሱን ሊገልጽ የሚችል ማብራሪያ ከመጠቀሙ በሰተቀር ከሞላ ጎደል የቃላት እጥረት ወይም የቃላት አጠቃቀም ስህተት የማይታይበት ፡፡

2. ጎላ ያለ ሃሳብን የመግለጽ ችግር ባይኖሪበትም አልፎ አልፎ የቃላት እጥረትና የቃላት አጠቃቀም ስህተት ፣ እንዲሁም በተደጋጋሚ የድፍረት ማጣትና ነገሮችን በስያሜያቸው ከመጥራት ይልቅ የማብራራት ባሕርይ የሚታይበት፡፡

1. ቀላሉን ነገር ለመግለጽ እንኳ የቃላት ችግር የሚታይበት ፣ በቃላት እጥረት ምክንያት ብዙም የማይናገረና የቃላት አጠቃቀም ሰህተት የሚታይበት ፡፡

## መ. አንደበተ -ርቱዕነት (አፌ-ትካነት)፣

3. አልፎ አልፎ በነገሮች ሰያሜ ምትክ ነገሮቹን ሊገልጽ የሚችል ማብራሪያ በመጠቀሙ የንግግሩን ፍሰት ቢገታውም ዓረፍተ-ነገሮቹ እርስ በርሳቸው የተያያዙ ከመሆናቸውም ባሻገር እምብዛም በንግግሩ ፍጥነትና ርዝመት ረገድ ችግር አይታይም፡፡

2. ዓ/ነገሮችን እርስ በርስ ለማያያዝ ሚደረግ ሙከራ ቢኖርም በንግግር ፍጥነትና ርዝመት ረገድ ችግር ይታያል፡፡

1.አብዛኛውን ጊዜ ንግግሩ ያልተሟላ ነው ዓ/ነገሮቹ እርስ በርስ ያልተያያዙና አጫጭር ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

***መመሪያ***

ይህ ክፍል ተማሪዎች ያቀረበላቸውን የመረጃ ምንጭ መሠረት በማድረግ ጥያቄዎችን የሚጠይቁበት ነው፡፡ ተማሪዎቹ የሚያከናወኑት ተግባር ጥያቄ የመጠየቅ ችሎታቸውን ለመለካት የቀረበ ነው ፡፡ስለሆነም ፣በክፍል አንድ እንዳደረጉት ሁሉ ፣ በዚህም ክፍል የተማሪዎቹን ጥያቄ የመጠየቅ ችሎታ ፣ከዚህ በታች የቀረበውን ሦስት

ነጥቦች ያሉትን ስኬል በመጠቀም የተማሪውን (ዋን) ችሎታ የሚገልጽወን ቁትር በመክበብ ያመልክቱ፡፡

ሀ. የመረጃ ምንጭን መሠረት በማድረግ ጥያቄ ስለመጠየቅ፡

3. መረጃዎችን ይረዳል ፤ጥያቄዎችንም በሚገባ መጠየቅ ይችላል፡፡

2. መረጃዎችን ይረዳል ፤ጥያቄዎችንም መጠየቅ ይችላል፡፡

1. መረጃዎችን በከፊል ቢረዳም ጥያቄዎችን በአግባቡ የመጠየቅ ችግርይታይበታል፡፡

የተከበሩ ፈታኝ !

ተማሪው(ዋ) ለሚጠይቅዎት (ለምትጠይቅዎት) ጥያቄ መልስ መስጠት ይችሉ ዘንድ የሚከተለውን የተሟላ መረጃ የያዘ ሰንጠዥ ይጠቀሙ ፡፡

| ተ.ቁ | የተማሪው(ዋ) ስም | የእናት ስም | የተማሪ በት ቦታ | ዕድሜ | ት/ት የጀመረች በት ዘመን | የክፍል ደረጃ | የሚወደው የት/ት ዓይነት | ት/ቱን የሚወድበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ክንፌ ገዘኸን | አደረት | አመሮ | 18 | 1994 | 11 | እንግሊዘኛ | መምህር ለመሆን |
| 2. | ማቲየስ ተረፈ | አስካለ | ኩቢጦ | 17 | 1996 | 9 | ባዮሎጅ | ሀኪም ለመሆን |
| 3. | አደን ተረፈ | ቦጋለች | ማሻ | 17 | 1996 | 9 | ሲብክ | ዳኛ ለመሆን |
| 4. | ዳዊት ለማ | አለምቱ | ኩቢጦ | 18 | 1995 | 10 | ፊዚክስ | መሀንድስ |
| 5. | እሸቱ ወዳጆ | አስተር | በሆ | 17 | 1994 | 9 | አማርኛ | መምህር ለመሆን |

# አባሪ ሶስት ፡- ንግግር ፈተናውን ውጤት ማጠናቀሪያ ቅጾች

## የፈተናውን ውጤት መመዝገቢያ ቅጽ

| ተ/ቁ | የተማሪዉ(ዋ) ስም | ሴክሽን | የክፍል ቁጥር | ክፍል አንድ | | | | ክፍል ሁለት | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሀ | |
| 1 | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | | |
| 11 | | | | | | | | | |
| 12 | | | | | | | | | |
| 13 | | | | | | | | | |
| 14 | | | | | | | | | |
| 15 | | | | | | | | | |
| 16 | | | | | | | | | |
| 17 | | | | | | | | | |
| . | | | | | | | | | |
| . | | | | | | | | | |
| 60 | | | | | | | | | |

## አባሪ አራት፡- ተማሪዎቹ ያከናወኗቸው ተግባራት

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ ኮሌጅ

## የድህረ ምረቃ ፕሮግራም

## የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ክፍል

**ውድ ተማሪዎች ፣**

የሽከኛ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሃቶች ትንተና ›› በሚል ርዕስ ለሚደረገው ጥናት የሚያስፈልጉትን ጠቃሚ መረጃዎች መሰብሰብ ይቻል ዘንድ እያንዳንዳችሁ (በነፍሰ-ወከፍ) ሦስት ሦስት ዓይነት ተግባሮችን ታከናውናላችሁ፡፡እነዚህም ተግባሮች ፣

1. ተግባር 1----------ቃለ መጠይቅ ፣
2. ተግባር 2--------- የሥዕል ገለጻ፣ እና
3. ተግባር 3---------- ትርጎማ

ናቸው:: እነዚህ ሦስት ተግባሮች ለእያንዳንዳቸው በተሰጠው መመሪያ መሠረት በጥንቃቄ እንድታከናውኗቸው በትህትና እየጠየቅሁ ጥናቱ ውጤታማ እንዲሆን ለምታደርጉት ቀና ትብብር ምስጋናዬን በቅድምያ አቀርባለሁ፡፡

### ተግባር 1 (ቃለ-መጠይቅ)

**ጥያቄዎች**

1. ከአንድኛ ሴምስተር ፈተና በኋላ ት/ቤት ለአንድ ሳምንት ያህል መዘጋቱ ይታወቃል ፡፡
   ሳምንቱን ምን እያደረግህ (ሽ) እንዳሳለፍከ(ሽ)ው ግለጽልኝ (ግለጪልኝ)፡፡

   ______________________________

2. በዕረፍት ጊዜህ (ሽ) ምን ማድረግ ትወዳለህ (ትውጂያለሽ) ?ለምን ?

   ______________________________

3. ከ1ኛ -8ኛ ክፍል የተማርክ (ሽ) ው የት ነው ሰለ ት/ቤት ጓደኞችህ (ሽ) ባህርያት ፣ በመካከላችሁ ሰለነበርው ግንኙነትና ስለት/ቤቱ ትዝ የሚሉህ (ሽ)ን ነገሮች አጫውተኝ (ችኝ)፡፡

---

4. በጣም የምትውዳቸውን (የምትውጂያቸውን) የሸካ ባህላዊ የምግብ ዓይነቶች ከጠቀሰክ (ሽ) በኋላ ምግቦቹ እንዴት እንደሚዘጋጁ አብራራልኝ ፡፡

---

5. የወደፊት እቅዶችህ (ሽ) ምን ምን ናቸው ፣ እነዚህን እቅዶች ለማሳካት ምን ለማድረግ አስበሃል (ሻል)


---

6. አንተ(ቺ) እና የትምህርት ቤት ጓደኞችሁ (ሽ) ስለ እንቅርት በሽታ ያላችሁን ግንዛቤ በሚመለከት ምን አስተያየት አለህ (ሽ) ከዚህ ጋር አያይዘህ (ሽ) ፣ በሽታውን ለመከላከል በት/ቤትህ (ሽ)ና በምትኖረበት አካባቢ እየተደረገ ያለውን ጥረት አብራራልኝ (ልኝ)፡፡


---

7. በመጨረሻ የትምህት ቤት ጓደኞችህ(ሽ)ን ምን ልትመክራቸው (ልትመክሪያቸው) ትፈልጋለህ (ለሽ)? ለምን ?


**ተግባር 2 (የሥዕል ገለጻ)**




1



2



3




4

ተክሌ(1987)



1



2



3



4

(Byrne, 1967 Hughes, 1989 )

## ተግባር ሶስት (ትርጎማ)

***መመሪያ፡-***

**በዚህ ተግባር ሥር ሁለት የሸክኛ ታሪኮችን ወደ አማርኛ በቃል ትተረጉማለህ (ያለሽ)፡፡**

**ከጓደኛህ(ሽ) ታሪኮቹን በሸክኛ ቋንቋ ሲነግርህ (ሽ) ሸክኛ ለማይችል ሰው መልዕክቱን ሊረዳ በሚችልበት ሁኔታ ወደ አማርኛ ተርጉመህ(ሽ) ትነግረዋለህ (ለሽ) ፡፡ የተናጋሪውን ሃሳብ መቀነሰም ሆነ አዲስ ሃሳብ መጨመር አይፈቀድም፡፡ ወደ አማርኛ መተርጎም ከመጀመርህ(ሽ) በፊት ጓደኛህ (ሽ) ታሪኮቹን ሲያነብልህ(ሽ) በጥሞና አድምጥና (አድምጭና) አንተ (ች) ራስህ(ሽ) ታሪኮቹን አንድ ጊዜ ደግመህ(ሽ) አንብባቸው (አንብቢያቸው)፡፡**

**ከዚህ በኋላ ከጓደኛህ(ሽ) በሸክኛ የሚነግርህ(ሽ)ን ታሪኮች በተረጋጋ መንፈስ ወደ አማርኛ ተርጉመህ (ሽ) አጠገብህ (ሽ) ለተቀመጠው ሸክኛ ለማይችል ሰው ንገረው(ሪው)፡**

## Shekkekitaatee k'itoona duukke sheeroo

Taato k'itigaata “Geedaami giyiyoone” hette gettiyabeeto tunayona haniyoo menokisse hettoomone.haniyo aache guriye.taato biijjagaa kataraasho k'ottona taatoge yegibbeeto bitunato gira boo womiiyoni biariiga mikire kere naayinoshini c'eegiye.book'k'ito bi gettiyeyo gish kere ashossi baachi bi tunoni gaboogeddona et'e mit't'oosse goono hachi k'annona gatte gook'k'ona kaafe aashona bikaneyoomossi tuniyaye. Haniyo bitunabeeto taate k'itoni asho k'ebiye kaaro, shottono boono tuniitachewomossiye.

Hani dakko abi taateyaana echiyabee yegiyeete.iraashewoni boono tooc'ite bekki are iraashe asho baa taatosse k'ittoni musho yechoyissi gijjiyaye.aree bekki k'itti taatosse duukee sheere aaboni mac'c'o k'ebiye biwoyee shiicha katinoo beeti ashoiida yet'iibeeti k'ano gede shichi dukkiyaye.bi duukkiyate guri genige shhahoomona giishabehettigaata keejja meetiri beddo gabinibeet kero hagiyaye.keree dukkosse ikka meetiri bedda taaossi oppo iiyena bic'eeneyoomossi tuniyaye.cheeniye maachi bikinidiyo beddo netibeetena giishi goore kero “geedaame-kero” shahiye.biciirate bekki gaasho bi toomo shokkona beshitoni kookiye.hani duuhe taaye shigoo “gedaamo” hette arijjaye.

“Geedaamo” hani duuke sheero aashona giishi ashona bi tunaate guri gettiyeyei getto beeto shahite eefo gettiyati aabooba gishosse kessi oogo beddo koni bola essaye hettena kiciyaki bi mikire kere yaarona doojji iibiite keyiyeete.maadi goono koyena iraashati taato taato k'ittoni gettona musho yechiye.konibulli shicha bibeeti sheeroosse bikeyacheyomosi bulla moyo bulli bishuuniyeyo sheerona baachiye.

Taano ittoshino yeeri iiwona kote.bara erimona nodenawo beddoni diggona itto keroo wottabote hettona mushona bi iraashononi ikkoche bottiye. K'ititi ashisse dubano yego bifakkeyo taatosso baachiye.haniyee maachi geddikki denato beegaata bigaano bi gijjo shotiyabeetone.

***(Tuup'o N. Abari Bacuri ( 2013) shekkachosse keemona goorono)***

## ታሪክ አንድ (የአማርኛ ትርጉም)

### የሸካ ንጉስ ሞትና የቀብር ስነስርዓት

ነገስታት ሲሞቱ geedami giyiyoone ተብሎ የሚነገር ሲሆን ይህም መነኮሱ እንደማለት ነው፡፡ይህም በምስጢር ቆይታ በኃላ ነው፡፡ንጉስ ሲታመሙ ካታራሻ በአስታማምነት በንጉስ ዘንድ የሚቆይ ስለነበረ መዳከማቸውን ሲረዱ የምክርቤት አባላትን ያስጠራል፡፡መሞታቸው የሚነገረው ለጥቂት የቤተሰብ አባላት መሆኑን ታሳብ በማድረግ የሾላ ዛፍ ቦረቦር ሳጥን ”goono” በማዘጋጀት ሙሉ በሙሉ ከቆዳ ተሸፌኖ ሊሰነብት የሚችለውን በምስጢር እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ይህም የሚሆነው የንጉስ መሞት ሰዎች ከሰሙ ረብሻና ዘረፋ እንዳይፈጽሙ ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ማን መንገስ እንዳለበት ሲወያዩበት ይቆያል፡፡ በደረሱት ስምምነት መሰረት የሚነግሰው ሰው ብቻ  የንጉሱን መሞት እንድረዳ ወደ እነርሱ ያስገባሉ፡፡ ከዚያም የሟች ንጉስ ቀብር ስነ ስርዓት ሕዝብ ሰምቶ ለለቅሶ የሚቀርብበት ቀን ጥቂት አስቀድመው በዚያ አከባቢ ከሚገኙ ሰዎች ጋር አስፈላጊ ነው የተባለውን ዝግጅት ተደርጎ ይቀበራል፡፡ ከተቀበረ በኃላ በክብ ደረጃ ዙሪያውን ቢያንስ የሦስት ሜትር ስፋት ያለው በማድረግ በጥልቀት ዙሮገጠም ጎጆ ወይም ሰስኖ እንደቤት ግድግዳ ይማገራል፡፡ከግድግዳው ቢያንስ አንድ ሜትር ርቀት በማስቀረት ስፋትና ጥልቀት ያለው ጉድጓድ እየተቆፈረ ወደ ውስጥ እየተወረወረ ይሞላል፡፡ ሞልቶ ወደ

ውጭ እስከ ወርድ ድረስ እየተረገጠና እየተጠቀጠቀ መለሰተኛ ባህላዊ ቤት"geedame kero" ይመስላል፡፡ሲያበቃም ጤፍ በላዩ ላይ ተዘርቶበት የበለጠውን ጥንካሬ ያገኛል፡፡የዚህ ቀብር ጥቅል ስሙ geedaamo በመባል ይታወቃል፡፡

Geedaamo ይህ ቀብር ሥርዓት በምስጥር በተወሰኑ ሰዎች ከተፈጸመ በኃላ የሚነገር አዋጅ እንዳለ ተመስሎ በተባለው ቀን ቀጠሮ ከህጻናትና አቅመ ደካሞች በስተቀር ማንም እንዳይቀር እየተባለ ሕዝብ ቀርቦ በየ ምክር ቤት ምድብተኛ እየሆነ በደንብ ተስተናግዶ ያድራል፡፡ በጧት ነጋሪት ተጎስሞ አዲሱ ንጉስ ለህዝብ መርዶ ይነግራቸዋል፡፡ማንም ሆነ ማን በፊት ከነበረበት የአኗኗር ሁኔታ አፈነግጣለሁ እንዳይል ማንኛውም ጉዳይ የሚሰተናገደው ደንብና ሥርዓት በሚፈቅደው መሰረት ብቻ ነው፡፡ እኔንም እናንተንም አምላክ ይጠብቀን፡፡በሕይወት ዘመን በሌላ የደስታ መስተንግዶ እስክንገናኝ በሰላም ወደየ ቤታችሁ ግቡ በማለት መርዶና ንግስኛውን በአንድነት ህዝቡ እንድሰማ ይደረጋል፡፡የሞተ ሰው አስከሬን ማደርና መሰንበት የሚችለው የምጉስ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ አድርጎ የተገኘ ሀብት ንብረት ይወሰድ ነበር፡፡አበራ(2013)

## አባሪ አምስት:- የተማሪዎች ንግግር የፅሁፍ ምዝግቦች ማስታወሻ

ተተኳሪዎች ሦስቱን ተግባራት(ቃለ መጠይቅ የሥዕል ገለፃና ትርጎማ) ሲያከናወኑ የተሰበሰቡትመረጃዎች እጅግ በርካታ በመሆናቸው ይህ ጥራዝ ሁሉም እንድያካትት ማድረግ አልተቻለም፣ ይሁን እንጂ ከሁሉም የጥናቱ ተሣታፍዎች መካከል ሦስቱንም ተግባራ የያዘ ከየብቃት ደረጃች መካከል የጽሁፍ-ምዝግቦች ለናሙና ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በተጨማሪም፣ በጽሁፍ ምዝግቦችቹ ውሰጥ ከዚህ በታች የቀርቡት ትዕምርቶች (symbols) ጥቅም ላይ ውለዋል፡-

መ = መምህር
ተማ = ተማሪ
- - - = አጥኚው ሆን ብሎ ያሰቀረው

. . . = የድምፅ መቆራረጥ
x-x = ለመረዳት ወይም ለመለየት አሰቸጋሪ የሆነ ቃል፡፡
\+ = አጭር ተግታ
++ = ረዥም ተግታ
* * * = ያልተሟላ የዓ/ነገር ክፍል

( ) = የሰውነት እንቅሲቃሴን (mime) በተመለከተ ማብራሪ መስጫ

/ / = የተማረውን የይደገምልኝ ጥያቄ ለመለየት

ከላይ ከቀርቡት ትዕምርቶች መካከል አንዳንዶቹ ከ BROWN እና YULE (1983) እንዲሁም ከ ALL WRIGHT እና BAILEY (1994) የተወሰዱ ናቸው፡፡

## ተግባር አንድ (ቃለመጠይቅ)

### ተማሪ አንድ

መ ፣ በቅድሚያ ስምህንና የክፍል ደረጃህን አስተዋውቀኝ

ተማ፣ ስሜ------------ ይባል የክፍል ደረጃዬ ዘጠኝ ነው

መ፣ የመጀመሪያ ሰሚስተር ዝግ መዘጋቱ ይታወቃል ምን ስትሰራ አሳለፍክ?

ተማ፣ እ… ቤተሰቦቼ ጋ ሄጄ ነው ማሻ እዛ ሄጄ ቲንሽ ስራ ሰርቼ እዛ እንትን ብዬነው የመጣሁት ያሳለፍኩት ማለት ነው ያው ተማሪ ስለሆንኩ(የእጅ እንቅስቃሴ)

መ፤ - - - በዕረፍት ጊዜህ ምን ማድረግ ትወዳለህ?

ተማ፤ + በእረፍት ጊዜዬ ቤተሰቦቼን መርዳት ስራ ካለ አብሬ በቃ ከነሱ ጋር

አብሬ መስራት ደስ ይለኛል፡፡

መ፤ ከአንድ እስከ ስምንት የት የተማርከው የትምህርት ቤት ትዝታህን

አጫውተኝ?

ተማ፤ ከአንድ እስከ ስምንት የተማርኩት መንድራሻ ነው ደስ የሚል ቦታ እንትን

ጊዜ ነው ያሳለፍነው እዛ ... ቦታ አለ ትዝታ የለም ትዝታ በቃ ደስ የምል ጊዜ ነው ያሳለፍነው፡፡

መ፤ ከሸካ ባህላዊ ምግብ ውስጥ የምትወደው የትኛውን ነው አሰራሩን ንገረኝ?

ተማ፤ ከሸካ ባህላዊ ምግብ ውስጥ ቆጮ ነው ደስ የሚለኝ ቆጮ ደሞ ሚሰራው

ከ...እንሰትነው እንሰቱ ካደገ በኃላ ለመፋቅ እንደደረሰ ይፋቃል ጉድጓድ ተቆፍሮ ለአስራ አራትቀን በሙሉ እዛ እንትን ተከድ እንትን ከተባለ በኋላ ይረገጣል፡፡በተረገጠበት በአምስተኛው ቀን ያወጡና ይቆርጡታል ከዚያን እንትን በቂጠል ላይ ያደርጉና ይጠፈጥፋሉ እ... ምጣድ አለ እዛ ላይ ይጋግሩና ጋግሮ ያወጣሉ ማለት ነው፡፡

መ፤ ስለ የእንቅር በሽታ ያለህ ግንዛቤና አመለካከት ምን ይመስላል በሽታውን

ለመከላል በአከባቢህ ምን እየተሰራ ነው

ተማ፤ እ በፊት በብዛት ... በፊት እንትን ጨው አዮዲን ያለው ጨው አይጠቀሙም ነበረ ስለዚህ ለዛኔ በብዛት የሰው ልጅ በብዛት ሴቶች ላይ ነው

መሰለኝ በብዛት እንትን ይላል፡፡ እሱ በሽታ እዚህ አንገት ላይ ይወጣል አሁን ግን የኤዲን ያለው ጨው በጣም ስለሚጠቅም በብዛት...ስለሚጠቀሙ አሁን እየቀረ በሽታው እየጠፋ ነው፡፡

መ፤ የወደፊት እቅድህ ምንድነው?

ተማ፤ ወደፊት መሆን ምፈልገው መካኒክ ብሆን መኪና የተበላሸ መስራት የወደቀ መኪና ምናምን ማስተካከል በቃ እሱ ላይ መስራት ነው የምፈልገው

መ : እሽ ተማሪ --- ምን ማድረግ አለብህ ከአሁኑ

ተማ፤ ከአሁኑ ማድረግ ያለብኝ ስለሱ እሱ ስራ ላይ የሚያስፈልገው ነገር ምን

አይነት ሳብጀክት ነው እ የተለያየ ስለሱ ስለመካኒክነት የሚያገለግለውን ነገር

በሙሉ ማንበብ ነው

መ፤ ለጓደኞችህ ምን ትመክራቸዋለህ?

ተማ፣ + የምመክረው ምክር አሁን ግን ጊዜው እንትን ብሎአል ተበላሽቷል እንግዲህእንትን ትምህርታቸው ላይ እንትን ማለት ወሬ አለመስማት በቃ እ....እንትንትምህርት ላይ መከታተል ነገሮችን ማጣራት ማለት ነው እንዲህ ብዬ ነው ...የምመክረው፡፡

**ተማሪ ሁለት**

መ፣ አንደኛ ሲሚስቴር መዘጋቱ ይታወቃል እረፍቱን ምን በመስራት አሳለፍክ?

ተማ፣ ቤተሰቦቼን በስራ እረዳለሁ ከዚያ የተወሰነ ትምህርት የትምህርት ክፍለጊዜ አውጥቼ አነባለሁ፡፡ ከዚያ በትርፍ ጊዜ ደሞ እሱን ከጨረስኩ በኋላ ደሞ ኳስ...ከጓደኞቼ ጋር እንጫወታለን፡፤ www

መ፣ በዕረፍት ጊዜዬ ምን ማድረግ ያስደስትሀል?

ተማ፣ +...የተማርኩት ከ አንድ እስከ ስምንት ቆጫዎች ይባላል፡፡ ከጓደኞቼ ጋርም ቆንጆ ላይፍ ነው ያሳለፍኩት ከዚያ እንመካከራለን እንረዳለን ተራ በተራ እሱ ያስረዳል እኑም ወጥቼ + እናስረዳለን፡፡ማለት ነው፡፡

መ፣ ከሸካ ባህላዊ ምግብ ውስጥ የምትወደው የትኛን ነው አሰራሩን ብትነግረኝ?

ተማ፣ ቆጮ ነው የምወደው እንሰቱ በመጀመሪያ ይተከላል፣ ያድጋል ለመፋቅ ልጅ ሲወልድ ይፍቃል ከዚያ በኋላ የሆነ ጉድጓድ ውስጥ አንድ ለ አስራ አራት ቀን ውስጥ ይቆያል ይጨመቃል፡፡ ከዚያ ይቆረጣል ይጠፈጠፋል ከዚያ ይጋገራል፡፡

መ፣ ስለ እንቅርት በሽታ ያልህ አመለካከት ምን ይመስላል በሽታውን ለማጥፍት ምን እየተሰራ ነው

ተማ፣ የእቅርት በሽታ የዛሬ አምስት አመት + አካባቢ ቡዙ ሰዎች ጋ ይታይ ነበር የአዮዲን እጥረት የተበከለም ውሃ አሁን እየጠፋ ስለሆነ አሁን አዮዲን ጨው በየቤቱ... አለ አሁን እየጠፋ እየቀነሰ መጥቷል፡፡

መ፣ የወደ ፊት እቅድህ ምድነው?

ተማ፣ እኔ የወደፊት እቅዴ መካኒክነት ነው፡፡

መ፣ እሱን ለማሳካት ምን ማድረግ አለብህ?

ተማ፣ ያው ትምህርቴን ጠንክሮ መማር አለብን፡፡ እ ቤተሰቦቼም እየረዱኝ ነው እንደዛ ለመሆን...ነው፡፡

መ፣ ለጓደኞችህ ምን ትመክራቸዋለህ?

ተማ፣ ያው ... እንዲያነቡት ነው ትምህርቱን ማለቴ ነው በቃ ያው ነው

## ተማሪ ሶስት

መ፣ ስምህንና የትምህርት ደረጃህን ንገረኝ?

ተማ፣ ስሜ----------- ነው ሚባል ክፍሌ ያው ዘጠኝ ነው

መ፣ የአንደኛ ሲ/ተር ዝግ ነበር ምን ስታሳልፍ ነበር እስቲ አጫውተኝ?

ተማ፣ እ… እናቴን በማገዝ ምናምን ደሞ እራሴን በማዝናናት ያው በጥሩ ነው

መ፣ ምን እየሰራህ?

ተማ፣ ዝምታ… ሁሉንም ነው ማግዘው

መ፣ በእረፍት ጊዜ ምን ማድረግ ትፈልጋለህ?

ተማ፣ በእረፍት ጊዜዬ እ… ማጥናት በቃ አጥንቼ ከደከመኝ ፊልም ምናምን በማየት

መ፣ ከ1 እስከ 8 የት ነው የተማርከው እዛ ያለህን ትዝታ ንገረኝ እስቲ?

ተማ፣ መንድራሻ ነው

መ፣ ምን ትዝታ አለህ?

ተማ፣ የለኝም …ያው እንደሁሉም ነው

መ፣ ከሸካ ባህላዊ ምግብ ውስጥ የምትወደው የትኛውን ነው?አሰራሩስ እንዴት ነው?

ተማ፣ እኔ ከባህላዊ ምግብ ውስጥ ቆጮ ወዳለሁ

መ፣ አሰራሩ እንዴት ነው

ተማ፣ + ቆጮ የሚሰራው መጀመሪያ ይተከላል ዘሩ ማለት ነው ከተተከለ በኋላ ያዘረዝራል ከዚያ ይፋቃል ከዚያ እ… አንድ ሀያ ቀን ምናምን ሲቆይ አራት ቀን ሲቆይ ይረገጣል ከዚያ በኋላ ከተረገጠ በኋላ ስበስል እዛው ስበስል ማለት ነው ይወጣል ከዚያ ይቆረጣል ይበስላል ከዚያ ይበላል፡፡

መ፣ ስለ የእንቅርት በሽታ ያለህ አመለካከት ምን ይመስላል በሽታውን ለመከላከል ምን እየተሰራ ነው በአካባቢህ?

ተማ፣ ያው አዮዲን በአዮዲን እጥረት ነው እሱ ነገር የሚመጣው እና እቅዱን እንዲጠቀሙ ይመከራል፡፡ የአዮዲን ጨው ማለት እንዲጠቀሙ ይመከራል በቃ እንዲህ ነው

መ፣ የወደፊት እቅድህ ምንድነው?

ተማ፣ ለወደፊት እንጂነር መሆን ነው

መ፣ ለማሳካት ምን ጥረት ታደርጋለህ?

ተማ፣ በደንብ ማጥናት… ነው እንግዲህ

መ፣ ለጓደኞችሽ ምን ትመክራለህ?

ተማ፣ እንዲያነቡ እበፀባያቸውም ጥሩ ተማሪ እንዲሆኑ አስተማሪን እንዲያከብሩ በቃ…

**ተማሪ አንድ**

መ፣ ስምህ ማን ነው ስንተኛ ክፍል ነህ?

ተመ፣ ምን ስሜ ----------- ነው …

መ፣ እሽ አብረሀም የአንደኛ ሲ/ተር ዝግ ለአንድ ሳምንት ያህል ነበር ምን ስሰራ አሳለፍክ

ተማ፣ በአንድ ሳምንት ውስጥ ፣ የእረፍት ጊዜ፣ ያው አባቴ ገበሬ ነው አሁን ከሱጋራ ስራ ሰራለሁ እያረስን ማሳው ውስጥ ቆጮ ምናምን ውስጥ ገብተን እንትን እያልን ሳር ምናምን ለበሬ ወይ ለላም እንሴጣለን ከዚያ ስራምናምን እንሰራለን፡፡

መ፣ በእረፍት ጊዜህ ምን ማድረግ ያስደስትሀል?

ተማ፣ በእረፍት ትምህርት ቤት እያሌን ነው ወይስ

መ፣ በሁለቱም ቦታ

ተማ፣ ትምህርት ቤት ኳዋስ እንጫዌታለን ከጓደኞቼ ጋር እስፖርት ምናምን እንሴራለን፡፡

መ፣ ከ1 እከ 8 የት ተማርክ ምን ትዝታ አለህ?

ተማ፣ ቦባ በላ ነው እዛ

መ፣ ምን ትዝ አለህ

ተማ፣ ቦባ በላ ውስጥ ከጓደኞቼ ጋር እጫወታለሁ ከዚያ ስራ እንሰራለን

+ ዲፓርትመንት ገብተን አስተማሪዎች የጠየቁት ጥያቄ እንመልሳለን ላይብረሪ ገብተን ከዚያ ጥናት ምናምን እናረግና…

መ፣ ሽካ ባህላዊ ምግብ ምግብ ውስጥ የቱን ትወዳለህ አሰራሩ እንዴት ነው?

ተማ፣ ቆጮ አዎ አሰራሩ ያው ከእንሰት ይሰራል ተፍቆ ምናምን ከተሰራ በኃላ እንበላሌን፡፡ያው ሁሌ ነው . . .የሚሰራው

መ፣ ስለ አንቅርት በሽታ ምን ያህል ታውቃለህ?

ተማ፣ ጨው መብላት ችግር ይመጣል ጨውን ወይ ማብዛት አይደለም ወይ ማነስ አይደለም መካከለኛ መካከለኛ አድርጎ መብላት ይጠበቃል፡፡

መ፣ ለወደፊቱ ምን መሆን ትፈልጋለህ?

ተማ፣ ለወደፊቱ እንትን ደክተር መሆን ይችላል

መ፣ እንዴት መሆን ትችላለህ ምን ማድረግ አለብህ?

ተማ፣ ሰዎችን ለማከም መዳን እፈልጋለሁ፡፡

መ፣ ለጓደኞችህ ምን ትመክራለህ?

ተማ፣ ምን ለጓደኞቼ ይሄ የ.. መጥፎ ነገር አትስራ ፣ አትስረቅ አትመን ብዬ

ነው እንትን እላለሁ፡፡

ተማሪ ሁለት

መ፣ ስምህንና የትምህርት ደረጃህን ንገረኝ?

ተማ፣ ስሜ ስሜ -------- አባላለሁ

መ፣ የመጀመሪያ ወሰነ ት/ት መዘጋቱ ይታወቃል ምን ስትሰራ አሳለፍክ?

ተማ፣ ቤተሰቦቼን እየረዳሁ ከዚያ በትርፍ ሰዓቴ ጥናት እያጠናሁ አሳለፍኩት

መ፣ በእረፍት ጊዜህ ምን ማረግ ያስደስትሀል?

ተማ፣ እሩቅ ቦታ ያሉትን ዘመዶቼን ይጄ አያለሁ ከዚያን በተረፈ እናት ኣቴን

ቤተሰቦቼንም እረዳለሁ መጠየቅ ደስ ይለኛል

መ፣ ከ1 እስከ 8 የት ተማርክ እዛ ምን ትዝታ አለህ?

ተማ፣ +ቆጫ ዎቻ ትምርት ቤቱ ያው ባያድግም ጥሩ ነው እዛ ነው

የተማርኩት

መ፣ ምን ትዝታ አለህ

ተማ፣ እረ ምንም የለም

መ፣ ስለ እንቅርት በሽታ ምን አመለካከት አለህ በሽታውን ለመከላከል ምን

እየተሰራ ነው?

ተማ. ….. አላውቅም ግን ያው ያው በሽታ ነው አይደል በቃ አንደሱ ነው

መ፣ የወደፊት እቅድህ ምንድን ነው?

ተማ፣ዶክተር

መ፣ እሱን ለማሳካት ምን ማድረግ አለብህ?

ተማ፣ በደንብ መማር . . . ነው

መ፣ ለጓደኞችሽ የምትመክረው ነገር ምንድ ነው?

ተማ፣ ወደ መጥፎ ቦታ እንዳሂዱ የልጅነት እድሜአቸውን በመጥፎ ነገር እንዳያሳልፉ በትርፍ ሰዓት እያጠኑ ቤተሰበቻቸውን እየረዱ እንዲያሳልፉ እመክራቸዋለሁ፡፡

**ተማሪ ሶስት**

መ፣ ስምሽንና የክፍል ደረጃሽን አስቲ ንገሪኝ?

ተማ፣ ስሚ ------- ስሆን ደረጃዬ ያው አንደኛ ነው

መ፣ አንደኛ ወሰነ ት/ት መዘጋቱ ይታወቃል ምን ስሰሪ ሰሳለፊሽ?

ተማ፣ አንድ ሳምንት ያው እንትን ግማሽ ሰአት ይሽራረፍና የሁለተና ሰሚስቴር እንትን ፈተና ምናምን ስላለ ሊኖርም ስለሚችል አስቢኝ ስላለ እስከዛ ድረስ ለመዘጋጀት ያህል እናጠናለን ከዛ ደሞ ከጓደኞቻችን ጋር ትንሽ እረፍት ምናምን ቤተሰብ ጥየቃ ሰዓት እንዲህ ከፋፍለን እ የህይማኖት ቦታዎች ላይ ትምህርት እየተማርን አሳልፈናል፡፡

መ፣ በዕረፍት ጊዜሽ ምን በማድረግ ያስደስትሻል፡፡

ተማ፣ በእረፍት ጊዜ ግቢ የትምህርት ግቢ ውስጥ ብሆን ላይብረሪ ማጥናት አእና . . . ከጓደኞች ጋር ጥያቄ መጠያየቅ የቡድን ሰራ በቡድን ሲሰጥ ሁሉ እሱንበእንትን በቡድን ይዞ አንድ ላይ መጠያቅ ከዛ ውጪ ሲሆን ደግሞ ውጪ ላይቤተክርስቲያን መማር እ እንዲሁም ከጓደኞች ጋር በቃ ጥያቄ መጠያየቅ እቤተሰብ መርዳት የመሳሰሉት ስራዎች ናቸው፡፡

መ፣ ከ1 እስከ 8 የት ነው የት ነው የተማርሽው ምን ትዝታ አለሽ?

ተማ፣ ያው ከ አንድ እስከ ስምንት ሎጭና 1ኛና መለስተኛ ደረጃ ነው የተማርኩት እዛ + ስማር ያው ከጓደኞች ጋር ከ1ኛ ክፍል እንደጀመርን ያው ቡድን ይኖረናል፡፡ በዛ ቡድን ውስጥ እየተወያየን ምን እያልን ሀሳብ እየተለዋወጥን ትምህርታችን እየተማርን እንገኛለን፡፡ ከዛ እንትን እ መምራኖቻችንም እዛ ያሉትም ያስተምራሉ እኛም ያልገባን ጥያቄ ካለ እየጠየቅን …

መ፣ የእንቅርት በሽታ በአካባቢያችን በብዛት ይገኛል ስለበሽታው ምን አመለካከት አለሽ በሽታውን ለማጥፋት ምን እየተሰራ ነው?

ተማ፣ + እ ኢሂ እንግዲህ የእንቅርት በሽታ የምንለው የአዮዲን ጨው እጥረት

የሚመጣ ነው፡፡ ይሄን ደሞ ይሄን ጨው በዙዎች ገጠር አካባቢ ሰላሉ ላያቁ ይችላሉ፡፡ኢሄን ደሞ እ'ሽ ጤና እንትኖች ሄደው ሊያስተምሩ ይገባል፡፡ ቢያንስ

ከተማዎች ሊያውቁ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ገጠር ከዚያ ስለሚያንስ ሂደው ማስተማር አለባቸው፡፡ እ'ሽ ደሞ ከጨውን ደግሞ በአግባቡ መጠቀምናየተመጣጠነ ምግብ . . .እንዲጠቀሙ ማድረግ ኢሄን ማስተማ አለባቸው፡፡

መ፣ የወደፊት እቅድሽ ምንድነው?

ተማ፣ ያው የወደፊት እቅዴ ዶክተር ለመሆነ እመኛለሁ

መ፣ አሱን ለማሳካት ምን ምን ነገሮችን ማድረግ አለብሽ?

ተማ፣ ዶክተር ለመሆን በርትቶ ማጥናት እ'ሽ በጥሩ ስነ-ምግባር ከትምህርት ቤት መለያየት እ'ሽ እነዚህን ትምህርቶችን ደግሞ ወደ. . . ዴና እንትን አለብኝ ብዬ አስባለሁ

መ፣ ለጓደኞችሽ ምን ትመክሪያለሽ

ተማ፣ ምከር ያው እኔ አሁን በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ የስነ-ምግባር ጉድለት ይኖራል፡፡ በዙን ጊዜ እነዚህን ተማሪዎች እንዲመክሩ እ ባለ የስራዎች ሀላፊነት ያለባቸው ሰዎች ደግሞ ቁጥጥሩን እንዲያበረታቱና ኢሄን መጥፎ ስነ-ምግባራቸውን አስወግደው ከእኔ ጋር እንዲያጠኑ ጥናቴ እነሱ ሲጠይቁኝ እኔስጠይቃቸው እንዲህ ሀሳብ ስንለዋወጥ እነሱም . . .ዴና ቦታ እንዲደርሱ እኔም ዴና ቦታ እንድደርስ እመኛለሁ፡፡

## ተግባር 2 (የስዕል ገለፃ)

### ተማሪ አንድ

#### ስዕል 1

እሄ ባህላዊ የጠላ መጥመቂያ እቃ ሲሆን፣ ሚሰራው መዋርካ እና ትላልቅ ዛፎች አሰራሩም በመጥረቢያ እንዲህ... ከመሀሉ ላይ ቅርፅ ያወጣና በመጥረቢያ ቆፍረው እንትን ነው... ይሄኛው ባህላዊ ቡና መጠጪያ ሲሆን ዶሎ ይባላል፡፡ በሸክኛ ከቀርከሀ ነው የሚሰራው ቀርከሀ ወዲያው እንደተቆረጠ ቅርፁን ያወጡና ፀሀይ ላይ እንትን

ይላሉ ያደርቃሉ፡፡ ከዚያ ቢያንስ እንድ ሳምንት ፀሀይ ላይ እንትን ከተባለ በኋላ… ቤት ውስጥ ቡና ተፈልቶ በዚህ ይጠጣል ማለት ነው፡፡ እሄ ጀበና ነው፡፡ + የራሱ የሆነ አሰራር አለው ከዛ የሚሰራ ነው ሲደርቅ ቡና ማፍያ እቃ ይሆናል ማለት ሰነው፡፡

**ስዕል 2**

*መጀመሪያ + ሌባው መጣ ሴትየዋ እየሄደች ነበረ ሌባ መቶ ቦርሳዋን ቀማ እየሮጠ ሲመጣ መንገድ ላይ የተቀመጠ ሰውዬ ነበረ በ…ያዘው ዱላ ጠለፈው ወደቀ ከዚያን ከወደቀ በኋላ ለሴትዬ ቦርሳዋን ከሰጡ በኋላ ለፖሊስ ነገሩ ፖሊሱ መቶ ሌባውን ወሰደ፡፡*

**ተማሪ ሁለት**

**ስዕል 1**

*እኔ የሸካ የመጠጫ ባህል የሚጠጣበት ቡና የሚሰራው ከቀርከሀ ተቆርጦ ነው የሚለው መጀመሪያ ይቆረጥና(የእጅ እንቅስቃሴ) ፀሀይ ላይ ደረቅ ሲል በገጀራ ነው ሚቆረጠው፡፡*

*እሱ የጠላ መጥመቂያ ባህላዊ የጠላ መጥመቂያ ስመ ጎኖ … የሚሰራው ከ… ከትላልቅ እንጨቶች ነው፡፡ ይሄ ጀበና ነው አሰራሩ ልዩ እንትን የራሱ አፈር አለው በአፈር አቡኩቶው ነው የሚሰሩት የሚያገለግለወ +ቡና ለመቅዳት ነው፡፡*

**ስዕል 2**

*በመጀመሪያ  ቦርሳዋን ሰርቃት ሮጣ እሽ የሆነ ሽማግሌ ቁጭ ብሎ ነበር ያለው ከዚያ እየሮጠ … እንትን… ከዘራውን ይዘው ጠለፈውና ወደቀ ከዚያ በኋላ ፖሊስ መጣ ሌባውን ያዘ ቦርሳዋን ለሴትዬ መለሰ…*

**ተማሪ ሶስት**

**ስዕል1**

*ይሄ የመጀመሪያው ከቀርከሀ ነው ሚሰራው ስሙ… በሸክኛ ደሎ ነው የሚባለው የሚያገለግለው ጠላ ለመጠጣት ነው፡፡ ይሄ ጀበና ነው የሚሰራው ከ… አፈር ነው የሚያገለግለው የቡና ለማፍላት ነው፡፡*

ስዕል 2

ቅደም ተከተሉ 1 ላይ ቦርሳዋን ቀማት 2 ላይ . . . ቦርሳውን ቀመዬ እየሮጠ ነው 3 ላይ የሆኑ ሰውዬ በእንትትን ጠላፉት እንደውደድቅ ከዚያ መጨረሻ ላይ ደግሞ በፖሊስ እንደያዘ ተደረገ በቃ...

ተማሪ አንድ

ስዕል1

ኢሂ ነኖ፣ ኢኔ የጠላ መጥመቅ የጠላ መጥመቂያ እቃ ውስጥ አንዱ የሸካዎች ባህል፣ እሺ. ኢሂ የአንድ ወይ የቤት ነገር ሌባ ከወሰዴ ኢኔ ይመታል፣ከዚያ ይጮሃል ከዚያ ሰው ይሜጣል፡፡ ኢሂ ጀበና ቡናን ሌማፍላት ይጠበቃል ወይ ይችላል፡፡ የሚሰራው ከመሬት፣ የመሚሰሩ መንጃ ናቸው ሰርቶ በገያ ነዶ ይወጣሉ ሰው ይገዛል፡፡ ነና የሚሰራው ከኢንጨት ዲኦ ከሚባለው እንጨት ነው፡፡ ዶሎ ዴሞ የሚሰራ ከቀርከሀ. . . ነው ሚሰሩ

ስዕል 2

በመጀመሪያ ሌባ እቃን+ ሰርቆ ዌስዶ ከዚያ በኋላ ሴትዬዋ ሮጠች ከዚያ በኋላ ሰውዬው ቤከዘራ ጠልፎ ያዜ፡፡ ከዚያ በኋላ ፖሊስ ጋር ወሰዱና አሰዙ ከዚያ በኋላ . . . ሴትዬዋ አመሰግናለሁ አለች

ተማሪ ሁለት

ስዕል 1

ከዲኦ የሚባል እንጨት የሚያገለግለው ጠላ ለመጥመቅ እ ለአንድ ችግር ከተጋጠመ ወቶ ለህዝብ ሲመታ ህዝቡ ይመጣል፡፡ ለዛ ይጠቅማል፡፡ ዶሎ የሚሰራው ከቀርከሀ የሚያገልግለው ጠላ ለመጠጣት ... ይሄ ጀበና የሚሰራው ከጭቃ የሚያገለግለው ቡና አፍልቶ ለመጠጣት፡

ስዕል ሁለት

በመጀመሪያ የሚቀድመው ሰላምታ ነው ቅደም ተከተሉ መጀመሪያ ሰረቀ ከዚያ ይዞ እሮጠ ከዚያ ሰውዬው በከዘራ መታ ከዛን ተያዘ ከዚያን ሰላምታ ሴትዬ ለሰውዬ.... ሰውዬው ለሴትየው ሰላምታ ሰጠ፡፡

**ተማሪ ሶስት**

**ስዕል አንድ**

ገንዳ ይባላል፣ ይሄኛው እንደ ገንዳ እንቀፎ አድርጎ የሚቀሙት ከእንጨት ነው የሚሰራው ከእንጨት ይሰራል ያኛው ደግሞ ይሄ እንትን ጠላ ምናምን የሚጠምቁበት ይሆናል ያኛው ማር የሚያመርቱበት ይሄኛው የከፋ ባህል ቡና የሚፈላበት ጀበና ይባላል የሚሰራው ይሄ መሬት አሸዋማ የሆነ መሬት አለ ሎቆ ይሉታል እነሱ እሄን + ይሰራሉ የሚሰሩት ደግሞ እነዚህ መንጃ ቤሄረሰብ አሉ ኢሄን ሰርተው ይጠቀማሉ፡፡ እሄ የከፋ ባህል እንትን ጠላ ምናምን የሚጠጣበት እሱ ነው ጠላ ምናምን ይጠጡበታል፡፡ እሄ ሲኒ ደግሞ አነስ ቢል እንደ ሲኒ ኪሱ ከቀርከሀ ነው የሚሰራው(የእጅ እንቅስቃሴ) ሲኒ አድርገው ኢሄ ቡናም . . . ይጠጡበታል ጠላም ይጠጡበታል፡፡

## ተግባር 3 (ትርጎማ)

**ተማሪ አንድ**

ንጉሱ ሲታመም ህዝቡ እንዳያውቅ ይደረጋል ከዚያ ሚክር ቤቱ ሚስጥር ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ከዚያ እንትን ሚስጥር ሆኖ ከቆየ በኋላ ሰዎቹ . . . ማለቴ ሚክር ቤቱ አንት ወላሹን ማለት ነው ለመምረጥ ሁሉም ወንዶችን በቁጥጥር ስር ያደረጓቸውና ይመርጣሉ፡፡ ንጉሱ ከሞት በኋላ ለስምንት ቀን ያህል ድብቅ ይደረጋል፡፡ ምርጫ የሚደረገው በነዚያ ቀናት ነው ማለት፡፡ ከዚያ ለህዝቡ ይፋ ይደረግና ህዝቡ ህዝቡ ለአንድ ቀን ሚሉ ምግብ አይበላም፡፡ ማለቴ ያው እንዳይበላ ይታወጃል ማለት ነው፡፡ ከዚያ የንጉሱ ጌጡ በሙሉ ወልቆ አስከሬኑ በቅቤ ታጥቦ ይገነዛል፡፡ ግን አንድ ምንድ ነው የሚባለው አዎ የጣት ወርቅ ቀለበት ማለት እሱ ብቻ ይቀራል፡፡ በመጨረሻ በሳጥን አድርገው ከፍተኛ ተራራ ላይ ተደርጎ ይቀብሩታል፡፡

ስነ ስርዓቱም ደሞ ሰባት ቄሶች ሆነው አስከሬኑን አጅበው በሬ እያረዱ ይሄዳሉ፡፡ አዲሱ ሰውዬ ማለትም ንጉሱም ልብሱን ለብሶ በወታደሮች ታጅበው በሰዎች ተከበው ይሄዳል ከዚያ ሁሉም ቄሶች በሬ አርደው መሰዋት በማድረግ ንጉሱን መንግስተ. . . ሰማያት እንዲገባ መሰለኝ ያርዳሉ፡፡ ግን ስጋውን ሰው አይበላውም. . . ለአሞራ ይሰጡታል በቃ እንደ ዚህ ነው፡፡

ተማሪ ሁለት

ታሪኩ. . . ስለ ሽካ ንጉስ ነው እና ንጉሱ ሲታመም ማለት ነው ለህዝቡ አይነግርም እንደገና ደሞ ሲሞትም ለህዝቡ አይነገርም ሰዎቹ ናቸው የሚያወሩት ምክር ቤቶቹ ማለት ከዚያ ሚስጥር አድርገው ይቆዩና እነዛ ሰዎች ማለት ነው ሌላ ንጉስ ይመርጣሉ ያው ሁሉንም ወንዶች ይሰበነስባሉ ማን እንደሆነ እንትን . . . አልጋ ወራሽ ከመረጡ በኋላ የሰውዬ… የንጉሱ ሞት ማለት ነው ለህዝቡ ይነግራሊ ከዚያ ህዝቡ ደግሞ ውሃም እንጀራም አይበሉም ለ…24 ሰአት ድረስ ከዚያ የንጉሱ ወርቃወርቁ + ያወልቁና ያጥቡታል በእንትን ነው የሚታጠበው በቅመም በቅቤ ነው ከዚያ አንድ ወርቅ ጣቱ ላይ አስቀርተው በሳጥን ውስጥ አድርገው ሰዎቹ ማለትም ንጉሶቹ የሚቀበሩበት ቦታ ይሄ… እሳ ይወሰዳሉ፡፡

ብዙ ቄሶች በመሆን በሬ እያረዱ በመንገዱ ያለውን … እንትን… እየባረኩ ከበሬው ደም ማለት ነው ይሄዳሉ አዲሱ ንጉስም በሰዎቹ ታጅቦ ነው የሚሄደው ንጉሱ እንተን እንዲል በማለት እዲፀድቅ ማለት ነው ቄሶቹ መስዋት የሚባል ያረጋሉ፡፡ ከዚያ ስጋውን ደግሞ ለመንጃዎች ና ለ… ይሰጣሉ ሰዎቹ አይበሉም ከዚያ በቃ ያው ያልቃል እ… ንጉሱ እንትኑን ሰዎቹ ይጠብቁታል፡፡

ተማሪ ሶስት

የሽካ ነገስታትና የቀብረር ስነ ስርአት ይሆናል ርዕሱ እንደዛ ሲል በሽካ…ንጉሶቹ ሲታመሙ ሚስጥር በሚስጥር እንትን ሚስጥር ይሆናል፡፡ ለህዝቡ. . . እንዳይነገር እሱን ደሞ የሚያከናውኑት ምክር ቤቶች ናቸው፡፡ እደ ከሞቱ ከ ስምንት ከስምነት ቀን በኋላ ና በሽምንጽ ቀን ውስጥ ሌላ ንጉስ ይመረጥና ከቤቱ ወንድ ልጆች ይመረጥና ከዚያ አንዲ ይመረጥና እ…የ እንትን በስምንት ቀን ውስጥ እሱ የሚከናወን ሲሆን …ከዚያ በኋላ ከስምንት ቀን በኋላ ነው ከተመረጠ በኋላ ነው ከስምነት ቀን በኋላ መሞታቸው የሚነገረው ለህዝቡ ከዚያ ከተነገረ በኋላ እ ህዝቡ ለሀያ አራት ሰአት ወይም ለአንድ ቀን ውሃ እንዳይጠጣ ይታወጃል፡፡ ከዚያ ሰውዬው የ እንትን ንጉሱ

ልብሳቸው ሙሉ ለሙሉ ከመጣ በኋላ ይገነዛሉ፡፡ የጣት ቀለበታቸው ለብቻ ይወጣና ከዚያ በቅመም የተነጠረ ቅቤ በሱ ይታጠባሉ ከዚያ መቃብር ስፍራቸው ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ +አድሶ እንትን ሰባት ቄሶች ናቸው እሱን እንትን የሚሉት ሽሻ ይባላል ሽሻ ማለት በአሁኑ ሰአት በጣሎ ወረዳ በሾዳ በሾዳ ቀበሌ የሚገኝ ቦታ ሲሆን የከፋ ነገስታት መቃብር የሚገኝበት ስፍራ ነው፡፡ በመሆን ይታወቃል፡፡ እ... ደሞ በቀብሩ እለት ሲሄዱ ሰባት ቄሶች አብሮ ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ በጓ በሬ ይታረዳል በመንገዱ በሚሄዱበት ቦታ ላይ ከዚያ ደሙ እየተረጨ ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ አዲሱ ተሿሚው እ እንትን አዲሱ ተሿሚው እንትን ይላል፡፡ እሱም ይሄዳል እንትኑ ቦታ ላይ ሌላ ቄሶችን ጨምሮ ይዞ ማለት ነው፡፡ ይሄድና ከዚያ እንድን ይደርሳሉ እዛ ቦታ ላይ ከዚያ እያንዳንዳቸው ቄሶቹ እያንዳንዳቸው በሪ.ኢ. እንትን በስለት መልክ ይሰጣሉ፡፡ ከዚያ አስራ አራት ሰንጋ ይታረዳል፡፡ ከዚያ የሰንጋውን ልብ አፈር ከመልበሱ የሰንጋው ልብ አብሮ እዛ እንትን ይባላል፡፡ ከዚያ. . . ስጋውን አሞራ ነው የሚባለው ሰው አይበላም፡፡

**ተማሪ አንድ**

እንግዲህ ያው *** ንጉሱ ሲሞት ህዝቡ አይሰማም እ... እነዚያ እንትኖቹ ሚኪሮቹ የሚባሉት ማለት ነው ይደብቃሉ፡፡ ከዚያ ከዚያ ቆይ መጀመሪያ እንትኑ ንጉሱ ሲታመም ህዝቡ አይሰማም፡፡ በጓ ስንት ቀን ነው ዝም ተብሎ ወንድ ወንድ ሰዎችን እነዚያ ሰዎቹ ስብስበው እንሊ ሰውዬ ይመርጣሉ፡፡ ማለት ንጉስ ማለት ነው፡፡ ከዚያ ንጉስ መሞቱን ለህዝቡ ይነገራል፡፡ ከዚያ ምግብም ውሃም እንዳይበሉ ሚኪሮቹ . . . እነሱ ሰዎቹ ይናገራሉ፡፡ ለሀያ አራት ሰዓት ማለት ነው እንግዲ ደግሞ ያው የሰውየው ማለት የንጉሱ እንትን ይሄ ወርቆቹም አብረው ይቀበራሉ አይደል እ ግን አንድ የጣት ወርቅ አብራ ነው የምትቀበረው፡፡ ሌላ ደሞ እንትኑ ደግሞ በቂቤ ነው እንትን የሚደረገው፡፡ ከዚያ ከፍ ያለ መቃብር ውስጥ ይቀበራል ማለት ነው፡፡

ከዚያ . . . ሰባት ቄሶች ናቸው መሰለኝ እነሱ እንትኑን ማለቴ አስከሬኑ በምሄድበት ቦታ ን... በሬ አርደው እንትን እያረጉ ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ ያ አዲሱ ሰውዬም እኮ ተሰዎቹጋ አብሮ እንትን አድርገውት አብረው መቃብር ያደርጋሉ፡፡ የታረደው በሬ ደግሞ + ሰው አይበላውም ለእንትኖቹ ይሰጣል፡፡ ለመንጃዎችና ለወፎች ማለት ነው፡፡ ከዚያ ንጉሱን የሚጠብቁ አሉ እስከ አንድ አመት እንትኑን ቦታ ማለት ነው፡

## ተማሪ ሁለት

አሁን በሸክኛ የሰማነው ታሪክ የሸካ ንጉስ ሞትና የቀብር ሥነ ስርአት ሲሆን በመጀመሪያ የንጉሱ መታመምም እንዳይታወቅ ሚስጥር ይሆናል ማለትም ሁሉም ነገር በምክር ቤቱ ሰዎች እንትን ይደረጋል፡፡ + . . . ያው መታመሙ ተደብቆ ከቆየ በኋላ ምክር ቤቱ የንጉሱን መሞት ለመግለፅ በመጀመሪያ የሚተካቸው እንዲመረጥ ያደርጋሉ ሌሉንም ወንዶች ማለትም የንጉሱ ቤተሰቦች የሆኑትን ማለት ነው + በአንድ ላይ ያደርጓቸውና ከነሱ ውስጥ አንዱን አልጋ ወራሽ ይመርጣሉ፡፡ ንጉሱ ከሞተ በኋላ ለስምንት ቀናት ያህል ነው የሚደበቀው እንትኑን የሚመጡትም ያው በዚያ ቀናቶች ነው ማለት ነው፡፡ ከዚያ ለህዝቡ ይነገርና ህዝቡ ለሀያ አራት ሰአታት ለአንድ ቀን ማለት ነው እህልና ውሃ እንዳይቀምሱ እንትን ይታወጃል፡፡ የሰውዬው ጌጣጌጦች ሁሉ ይወልቃሉ ከዚያ በቅቤ ቅመም ያ ሰውዬ ይታጠባል፡፡ ግን እ…አንድ የወርቅ ጣቱ ላይ ወርቅ ይቀራል ኪዚያ . . .ንጉሶቹ የሚቀበሩበት ቦታ አሌ እዛ ረጅም ተራራ ነው እዛ ነው የሚቀበረው

ስነ ስርአቱ ቄሶቹ ናቸው ማለትም ++ ሰባት ሆነው እንትኑ በሚሄድበት ይሄ ቦታ ማለት በሬ ታርዶ ደም የሚረጨው ቦታ እንትን ያደርጉታል ይሄ ይባርክዎታል፡፡ እናም ያ አዲሱ ንጉስም እነኚ ምንድነው የሚባለው እነሱ ማለት ነው፡፡ እንደገና ደሞ ህዝቡም ከቦት እዛ ቦታው ላይ ይሄዳሉ፡፡

ንጉሱ መንግስተ ሰማያት + . . . እንዲገባ ብለው እነዛ ቄሶች ብዙ በሬዎችን እያረዱ እንትን ያደርጋሉ፡፡ ስጋው ደግሞ ለአሞራና ለመንጃዎች ይሰጣሉ፡፡ ከዚያ በቃ ያው ንጉሱ መቃብር ቦታ ላይ ለስንት ጊዜ ነው… ይጠበቃል ቦታ ማለት ነው፡፡

## ተማሪ ሶስት

አሁን ያየነው ታሪክ ስለ ከፋ ንጉሱ መሞት ነው *** መጀመሪያ ንጉሱ ይታመማል ግን ለህዝቡ አይነግርም እነዚያ ሚኪሮቿ ማለትም ምክር ቤቱ ዝም ብሎ በውስጣቸው ይይዛሉ፡፡ ከዚያ ለሰሞን ቀን ዝም ከተባለ በኋላ እነዚያ ሰዎቹ ስብሰባ ጠርተው አዲ ንጉሱን ከወንዶች ይመርጣሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ሰውዬው መሞቱን ከህዝቡ ይነግራል ማለት ነው፡፡ህዝቡ ደግሞ እህል አይበላም ወሀም አይጠጣም ለአንድ ቀን ከዚያ እነዚያ ሚኪሮቿ ናቸው የሚናገሩት፡፡ ከዚያ የንጉሱ ወርቆች ሁሉም ያወልቃሉ ከዚያ ግን አንድ ይቀራል ጣት ላይ በኋላ ያ . . . አዲሱ እንትን ከወታደሮቹ ጋር እና ህዝቡ ጋር በመሆን እዛ ቦታ ላይ ይደርሳሉ፡፡

የሚቀበረው ደግሞ  ብዙ ቄሶች ሆነው ሰውዬው በመሄድበት ቦታ ሆነው በሬ እያረዱ ያ ቦታውን ማለት ነው ይባርካሉ ከዚያ ስጋውን ደግሞ ለወፎቹ ይሰጣሉ፡፡ መንጃዎችም ይሰጧቸዋል ሰው አይበላም ማለት ነው፡፡ ከዚያ ቄሶች ደግሞ ንጉሱ ሌላ አለም ይገባል ብለው

## አባሪ ስድስት፡- የክፍል ምልከታ ቅፅ

**ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸውን ተግባቦታዊ ብልሃቶች ለመመዝገብ የሚያገለግል የምልከታ ቅጽ**

| ተ.ቁ | የተግባቦታዊ ብልሃቶች አይነቶች | ምልከታ | የምልክቶቹ ድምጽ | መቶዮሽ (%) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ገለፃ | | | |
| 2. | ግመታ | | | |
| 3. | ቃለ-ፈጠራ | | | |
| 4. | ዳግም- ማዋቀር | | | |
| 5. | የቃል በቃል ትርጉም | | | |
| 6. | ማስመሰል | | | |
| 7. | ልሳናት ቅልቀላ | | | |
| 8. | የሰውነት እንቅስቃሴ | | | |
| 9. | ማሟያዎች ወይም መጠራጠሪያ ዘዴዎች | | | |
| 10. | ድጋፍ መጠየቅ | | | |
| 11. | መደበኛ ቅነሳ | | | |
| 12. | መልዕክትን መተካት | | | |
| 13. | መልዕክትን መተው | | | |
| 14. | ርዕስን ማስወገድ | | | |
| 15. | ሁለገብ ቃላትን መጠቀም | | | |
| 16. | ሌሎች ብልሃቶች | | | |
| . | | | | |
| | | | | |
| | | | | |